# ኢፕድ አዲስ ዘመን

ሰኞ 82ኛ ዓመት ቁጥር 030 መስከረም 30 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


# ጠቅሳይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ አገራዊ የበጋ ስንዴ ልማትን በሶማሌ ክልል በይፋ አስጀመሩ



ፎቶ - በሣሙኤል ተስፋዬ

**ጌትነት ምህረቴ**

ጅግጅጋ፡- ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ አገራዊ የበጋ ስንዴ ልማትን በትናንትናው እለት በሶማሌ ክልል በይፋ አስጀምረዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ትናንት በሶማሌ ክልል ፋፈን ዞን ቱሉጉሌት ወረዳ ኩሉሌ ቀበሌ በመገኘት አገራዊ የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ሲያስጀምሩ እንደገለጹት ፣ በእያንዳንዱ ፈተና ዕድልን ፈልቅቆ በማውጣት፣ እያንዳንዱን ችግር የሚያሻግር ስራ በመስራት የኢትዮጵያን ብልጽግና እናረጋግጣለን፡፡

ኢትዮጵያ እንኳንም ለራሷ ለሌሎች የሚተርፍ ስንዴ ማምረት ትችላለች ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ እያንዳንዱን ፈተና ወደ ዕድል በመቀየርና ለያንዳንዱ ችግር ዘላቂ መፍትሄ በመተግበር የኢትዮጵያን ብልጽግና ማረጋገጥ ይገባል ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉት እንኳን ለራሳችን ለሌሎች የሚተርፍ ስንዴ ማልማት እንችላለን፣ ይህን መንገዱን

ጠቅሳይ ሚኒስትር ዐቢይ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ - በሃዲስ አብርሃ

አቶ ታደሰ ከበደ

# 72 ተቋማት የኤሌክትሮኒክስ የመንግሥት ግዥ ሥርዓትን መጠቀም ጀመሩ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- በ2015 ዓ.ም በጀት ዓመት 72 የሚደርሱ መስሪያ ቤቶች የኤሌክትሮኒክስ የመንግሥት ግዥ ሲስተምን መጠቀም መጀመራቸውን በመንግሥት ግዥና ንብረት ባለሥልጣን የኤሌክትሮኒክስ የመንግሥት ግዥ ሲስተም ፕሮጀክት ማናጀር አስታወቁ፡፡

የባለሥልጣኑ የኤሌክትሮኒክስ የመንግሥት ግዥ ሲስተም ፕሮጀክት ማናጀር አቶ ታደሰ ከበደ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2015 ዓ.ም በጀት ዓመት 72 የሚደርሱ መስሪያ ቤቶች የኤሌክትሮኒክስ የመንግሥት ግዥ ሲስተምን መጠቀም ጀምረዋል፡፡

72 ተቋማት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የአሸባሪው ትህነግ መሪዎች ሥልጣናቸውን ለማስመለስ ሲሉ የትግራይን ወጣት እያስጨረሱ ነው

**መሰረት ገ/ዮሃንስ**

አዲስ አበባ፡- ጥቂት የአሸባሪው ትህነግ መሪዎች ሥልጣናቸውን ለማስመለስ ሲሉ የትግራይ ህፃናትና ወጣቶችን በጦርነት በመማገድ እያስጨረሱ ይገኛሉ ሲሉ የትግራይ ዴሞክራሲ ፓርቲ (ትዴፓ) መስራችና አማካሪ አቶ መኮንን ዘለለው ገለጹ፡፡

አቶ መኮንን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ሽማሌዎቹ የአሸባሪው ትህነግ መሪዎች ሥልጣናቸውን ለማራዘም ባላቸው ፍላጎት የትግራይን ወጣቶችና ህጻናት ለጦርነት እየማገዱ ነው የመጡት፣ አሁንም የቀረውን እድሜያቸውን ሥልጣን ላይ ለመቆየት የትግራይ ህፃናትና ወጣቶችን እያስጨረሱ ይገኛሉ ሲሉ ገልጸዋል፡፡

አሸባሪው ትህነግ ማለት በሥልጣኔ የማያምን በሃይልና በጦርነት ብቻ ሥልጣን መያዝ የሚፈልግ ነው ያሉት አቶ መኮንን፣ መሪዎቹም የትግራይ ሕዝብን ሳይጨቁኑ መኖር አይችሉም ብለዋል፡፡

የትግራይ ሕዝብ በአሸባሪው ሕወሓት ታፍኖ እየኖረ ነው ያሉት አቶ መኮንን ፣ ሕዝቡን ለህልውናቸው ጦርነት እየማገዱት ነው ብለዋል፡፡

የሚያሳዝነው ነገር የትግራይ ሕዝብ ልጆቹን ለጦርነት እየማገደ ያለው እና ንብረቱን እያጠፋ ያለው ለዚህ ቡድን መጠቀሚያ መሆኑ ነው ያሉት አቶ መኮንን ፣ የትግራይ ሕዝብ ከገባበት ችግር ሊወጣ የሚችለው ሕወሓት ሲጠፋ ብቻ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

አቶ መኮንን እንዳሉት፤ አሸባሪው ሕወሓት ሕዝብን ወደ ባሰ ዕልቂት እየመራው ይገኛል፤ ምክንያቱም ሕወሓት



አቶ መኮንን ዘለለው

ነገሮችን በሰላማዊ መንገድ የመፍታት ልምድ የለውም፡፡

ከዚህ በፊት በነበረው ትግል የትግራይን ሕዝብ መጠቀሚያ በማድረግ ሥልጣን ከያዘ በኋላ እንደረሳው የሚታወስ ነው ያሉት አቶ መኮንን፤ አሸባሪው ሕወሓት ያንን ታሪክ መድገም ነው የሚፈልገው ብለዋል፡፡

የአሸባሪው ትህነግ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል









# ተፈታኞች ከኩረጃ ነጻ ሆነው ፈተናውን እንዲወስዱ ጠቅሳይ ሚኒስትሩ አሳሰቡ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የ12ኛ ክፍል ተፈታኞች ከኩረጃና ከስርቆት ነጻ ሆነው ፈተናውን በተረጋጋ ሁኔታ እንዲወስዱ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ አሳሰቡ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተፈታኞቹን አስመልክቶ በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ባስተላለፉት መልዕክት “የኢትዮጵያ የነገ ተስፋዎች የሆናችሁ ተፈታኞች ኢትዮጵያ እናንተን ስታይ ተስፋ ነው የሚታያት” ሲሉ ገልጸዋል።

ተፈታኝ ተማሪዎች ፈተናው ለኢትዮጵያ እውነተኛ ተስፋዎች መሆናችሁን ልታሳዩበት ይገባል ብለዋል።

ወላጆች፣ መምህራንና መላው ማህበረሰብ እናንተን እዚህ ለማድረስ ለዓመታት ለፍቷል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተፈታኞች ከኩረጃና ከስርቆት ነጻ በመሆን እንዲሁም በራስ በመተማመን ፈተናውን በመፈተን ውጤታማነታቸውን ማሳየት እንደሚገባቸው ተናግረዋል።

ተፈታኞች የተሰጣቸውን መመሪያ በማክበርና ያለ ምንም መሸበር ፈተናቸውን መፈተን እንደሚኖርባቸው አመልክተዋል።

“ለ12ኛ ክፍል ተፈታኞች የኢትዮጵያ አምላክ ዕውቀቱን ይግለጥላችሁ” ብለዋል ጠቅላይ ሚኒስትሩ በመልዕክታቸው።

የ2014 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተናን ለመውሰድ የመጀመሪያ ዙር ተፈታኞች ከመስከረም 26 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ወደ ዩኒቨርሲቲዎች ገብተዋል።

ከዛሬ ጀምሮ ለሚሰጠው የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ከ975 ሺህ በላይ ተማሪዎች ፈተናውን ይወስዳሉ ተብሎ እንደሚጠበቅ ከትምህርት ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ ያመለክታል።







ዜና

# በግብዓት እጥረት ምክንያት ስጋት ላይ ወድቄያለሁ

## - ቱ ብራዘርስ ፉድ ኮምፕሌክስ

# ኤክስፖርት ለሚያደርጉት እንደየሁኔታው እየታየ ቅድሚያ ይሰጣል

## - ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- የቱ ብራዘርስ ፉድ ኮምፕሌክስ ፋብሪካ በማምረቻ መሳሪያ እና ጥሬ እቃዎች ችግር ምክንያት ስጋት ላይ መሆኑን አስታወቀ። ከውጭ ምንዛሬ ፍላጎት ጋር ተያይዞ ቅድሚያ ኤክስፖርት ለሚያደርጉት ቅድሚያ ለመስጠት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት መደረጉንና ለተግባራዊነቱም አቅጣጫ እስኪሰጥ እየተጠበቀ መሆኑን የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አስታውቋል።

ቱ ብራዘርስ ፉድ ኮምፕሌክስ ፕሮዳክሽን ኃላፊ አቶ አደም ከማል ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ፋብሪካው በተለያዩ ምክንያቶች በሙሉ አቅሙ እየሰራ አይደለም። በርካታ የማምረቻ መሳሪያ ጥሬ እቃዎች ከውጭ የሚገቡ ስለሆነ የውጭ ምንዛሬ እጥረቱ ሥራውን በአግባቡ እንዳይሰራ ከፍተኛ ተግዳሮት ሆኗል። ይህንንም በተቻለ መጠን የሚመለከተው የመንግሥት አካል ትኩረት እንዲሰጠው ጠይቀዋል።

እንደ አቶ አደም ገለጻ፤ ፋብሪካው 34 የብስኩት አይነቶችን የሚያመርት ሲሆን፤ ብስኩቶችን አገር ውስጥ ለማምረት የሚያስችል ማሽነሪዎች ቢኖሩትም፤ በተፈጠረው የዶላር ችግር ምክንያት ከውጭ የሚያስፈልጉ ጥሬ ዕቃዎችን ማስገባት ባለመቻሉ ከፍተኛ የሆነ ተግዳሮት አጋጥሟል።

አቶ አደም፤ ምርትን ወደ ውጭ ለመላክ አቅምና ተነሳሽነቱ እንዲሁም ዝግጅቱ እንዳለ ጠቅሰዋል። በተለያየ ጊዜ ይህን ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ቢደረግም መንግሥት እስካሁን በድርጅቱ የሥራ ተሳትፎና በያዘው የሠራተኛ ልክ የሚያደርገው ድጋፍ ብዙም አይደለም ብለዋል።



ማሽነሪዎች በሙሉ በአውሮፓ የተሰሩ፤ ብስኩቶችን በማምረት ለአገር ውስጥና ለውጭ ለመላክ ትልቅ አቅም ያላቸው እንደሆኑ ጠቅሰዋል። ይህ ከተቀረፈ ወደ ውጭ ለመላክም ሆነ ከውጭ የሚገቡትን ብስኩቶች ለማስቀረት ከፍተኛ የሆነ ዝግጅት መደረጉን ገልጸዋል።

ማሽኖቹ የገቡት የብስኩት ምርቱን ወደ ደቡብ ሱዳን፣ ሱዳን፣ ኬንያ፣ ሱማሊያ ለመላክ የሚያስችሉ እንደሆኑም አቶ አደም ጠቁመዋል። የማሽን የማምረት አቅሙ ከፍተኛ ቢሆንም ፤ ከውጭ የሚገቡ ጥሬ ዕቃዎችን እንደ ልብ ማግኘት ባለመቻሉ አሁን ላይ 50 በመቶውን ያህል ብቻ እያመረተ መሆኑን አስታውቀዋል።

ባለፉት አራት ዓመታት ውስጥ ችግሩ እንዲቀረፍ ትግል ላይ ነን ያሉት አቶ አደም፤ ችግሩ በዚሁ የሚቀጥል ከሆነ ፋብሪካው አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሊገባ ይችላል በማለት ስጋታቸውን ተናግረዋል።

በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የወጪ ምርቶች መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ዘሪሁን አበበ በበኩላቸው፤ የውጭ ምንዛሬ ፍላጎቱ ከአጠቃላይ አገራዊ ጉዳይ ጋር ተያይዞ የመጣ ተጽእኖ መሆኑን ተናግረዋል።

የውጭ ምንዛሬ እጥረቱ በአገር ደረጃ ያለ ነው ያሉት አቶ ዘሪሁን፤ ከውጭ ምንዛሬ ፍላጎት ጋር ተይይዞ የቱ ብራዘርስ ፋብሪካን ጨምሮ በርካታ ኢንዱስትሪዎች ጥያቄ እንዳላቸው ገልጸዋል። ፍላጎታቸው በልዩ ሁኔታ እንዲታይ ከብሔራዊ ባንክና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት መደረጉን አንስተዋል። ነገር ግን ካለው ነባራዊ ሁኔታ በሚፈልጉት ልክ ማቅረብ እንዳልተቻለ፤ ይህም የቱ ብራዘርፍ ብቻ ሳይሆን የሌሎችም ጥያቄ እንደሆነ አመላክተዋል።

አቶ ዘሪሁን፤ በዋናነት በአገር ውስጥ ግብዓት እንዲጠቀሙ ትስስሩን የማጠናከር ስትራቴጂዎች እየተዘጋጁ እንደሆነ ጠቅሰዋል። ከውጭ ምንዛሬ ፍላጎት ጋር ተያይዞ ቅድሚያ የሚሰጣቸው እንዳሉ ጠቁመው፤ በዚህም ኤክስፖርት የሚያደርጉ እንዱስትሪዎችና ስትራቴጂ ተኪ ኢንዱስትሪዎች እንደየሁኔታቸው እየታየ ቅድሚያ የሚያገኙበት ሁኔታ ለማመቻቸት ውይይት መደረጉንና አቅጣጫ እስኪሰጥበት እየተጠበቀ መሆኑን አስታውቀዋል።

ፋብሪካው ሰባት ቅርንጫፎች እና አራት ሺህ ሠራተኞች ያሉት ሲሆን፤ የምርት መዳረሻው በመላው ኢትዮጵያ እንደሆነ ተገልጿል። የማምረት አቅሙም በወር እስከ አስር ሺህ ቶን እንደሚደርስ ያገኘነው መረጃ ያሳያል።

# የቢዝነስ አዘጋገብን ሙያዊ ክህሎት ለማሳደግ የሚያስችል የአቅም ግምባታ ሥልጠና ተሰጠ

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- የቢዝነስ አዘጋገብ ላይ የሚታዩ ክፍተቶችን ለመፍታትና የዘጋቢዎችን አቅም ለማጎልበት የሚያስችል ሥልጠና ተሰጠ፡፡

ሰሞኑን የፕላንና ልማት ሚኒስቴር ከአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ጋር በጋራ በመሆን ባዘጋጁት ሥልጠና ላይ የፕላንና ልማት ሚኒስትር ዶክተር ፍጹም አሰፋ እንደተናገሩት፤ መንግሥት ለመገናኛ ብዙሃን አቅም ለመገንባትና የተሻለ ሁኔታን ለመፍጠር እየሰራ ነው፡፡

ዶክተር ፍጹም እንደተናገሩት፤ ጋዜጠኞች በዘገባ ስራዎቻቸው የሕዝብንና የሀገርን ጥቅም በማስቀደም መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ሚዲያና የሚዲያ ባለሙያዎች ለሀገር እድገትና ህልውና ካላቸው ከፍተኛ ሚና አንጻር የሚሰሯቸውን የሚዲያ ስራዎች በሙያዊ ዲስፕሊን ፣ በእውቀትና ለሀገርና ለሕዝብ በመወገን መሆን አለበት ያሉት ዶክተር ፍጹም፤ መንግሥትም ለመገናኛ ብዙሃን የተሻለ ሁኔታን ለመፍጠር እየሰራ ነው ብለዋል፡፡

ጋዜጠኛ ልክ እንደወታደር በየትኛውም ስፍራ ላይ ለስራው ዘግጁ ሊሆን ይገባል ያሉት ዶክተር ፍጹም፣ የሚዲያ ባለሙያዎች መረጃ መታጠቅ አለባቸው፤ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን በመጋፈጥ መስራትም ከሙያው ይጠበቃል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በሚዲያዎቻችን በተለይም በቢዝነስና ኢኮኖሚ ጉዳዮች ዘገባ ዙሪያ ክፍተቶች መኖራቸውን ያነሱት ዶክተር ፍጹም፤ ይህንን ክፍተት ለመቅረፍም በተከታታይ ሥልጠናዎችን ለመስጠት የፕላንና ልማት ሚኒስቴር ከፍተኛ ፍላጎት እንዳለው አረጋግጠዋል፡፡

የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ዋና ጸሃፊ አቶ ሸበሺ ቤተማርያም በበኩላቸው ምክር ቤቱ የጋዜጠኞችን አቅም በማሳደግ ላይ በትኩረት እየሰራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ይህም የሀገሪቱን የቢዝነስና የኢንቨስትምንት እንቅስቃሴ ለማቀላጠፍና ጥራት ያለውና ሚዛናዊ መረጃን ተደራሽ ለማድረግ ያግዛል ብለዋል፡፡



ፎቶ - በበላይ አበፋቸው

ዶክተር ፍጹም አሰፋ

አዲስ ቻምበር ንግድና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ የማገዝ ፣ ማህበረሰቡ ያሉበትን መሰረታዊ ንግድ ነክ ችግሮች ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመመካከር የመፍታት ተልዕኮን ይዞ እየሰራ መሆኑንም ዋና ጸሃፊው ጠቁመዋል፡፡

ለቻምበሩ ስራዎች ውጤታማነት ሚዲያ ቁልፍ አቅም መሆኑን የጠቆሙት አቶ ሸበሺ፣ በቀጣይም የተጠናከረ የሚዲያ አቅም ግንባታ ስራ ይሰራል ብለዋል፡፡

የፕላንና ልማት ሚኒስቴር ከአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ጋር በጋራ በመሆን ለሁለት ቀናት የቆየ የቢዝነስና ኢኮኖሚ ዘገባ ሥልጠና ከተለያዩ መገናኛ ብዙሃን ለተውጣጡ ከ25 በላይ የቢዝነስ ጋዜጠኞች የሰጠ ሲሆን በቀጣይም መሰል ሥልጠናዎችን ለማድረግ ቃል ገብቷል፡፡

# የተቋማቱ ድጋፍ የአርብቶ አደሮች ሕይወት የተረጋጋ እንዲሆን አስችሏል

**ኤፍሬም አንዳርጋቸው**

አዲስ አበባ፡- የሀረማያ ዩኒቨርሲቲና የዓለምአቀፉ ቀይ መስቀል ኮሚቴ (አይ.ሲ.አር.ሲ) ባደረጉት የተቀናጀ ድጋፍ በኦሮሚያና ሶማሊያ ድንበር በጭንአክሰን ወረዳ የሚኖሩ የአርብቶ እና ከፊል አርብቶ አደሮች ሕይወት መሻሻሉ ተገለጸ።

በዩኒቨርሲቲው መምህርና በጭንአክሰን ወረዳ የምርጥ ዘር ብዜት ፕሮጀክት አስተባባሪ አቶ ከማል ቃሲም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በአገሪቷ ለውጥ ከመምጣቱ በፊት በኦሮሚያና ሶማሊያ ክልሎች ድንበር አካባቢ በነበረው ግጭት በርካቶች ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው ለከፋ ችግር ተጋልጠው ይኖሩ ነበር።

አርብቶ አደሮቹ ከቀያቸው በመፈናቀላቸውም በየዘመዶቻቸው ተጠግተው እንዲኖሩ፣ የከሰል ንግድ ላይ እንዲሰማሩ፣ በየከተማው የተለያዩ ትናንሽ ስራዎችን እንዲሰሩ ተገደው ነበር ብለዋል።

በአካባቢው ከሚፈጠረው ግጭት ባሻገር በየጊዜው የሚከሰተው ድርቅ የአርብቶ እና የከፊል አርብቶ አደሮቹን ሕይወት አስቸጋሪ አድርጎት እንደነበር የጠቀሱት አቶ ከማል፤ ይሁንና አገራዊ ለውጡን ተከትሎ በመጣው ሰላምና መረጋጋት በምስራቅ ሀረርጌ ጭንአክሰን ወረዳ የሚኖሩ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ወደ ቀያቸው መመለስ ብቻ ሳይሆን ተረጋግተው የእርሻ ስራ እንዲሰሩ አስችሏል ብለዋል።

በአካባቢው ሰፋፊ የእርሻ መሬት ቢኖርም አርሶ አደሮቹ ያላቸው ውስን የግብርና እውቀት የእርሻ ስራቸው ላይ ተግዳሮት ሆኖባቸው መቆየቱን ተናግረው ዩኒቨርሲቲውና አይ ሲ አር ሲ ከመንግሥት ጋር ተቀናጅተው በሰሩት ተከታታይ ስራ የአርብቶ አደሮቹን ሕይወት መቀየር ተችሏል ሲሉ አቶ ከማል ገልጸዋል።

በተለይም የአካባቢው ምርት እና ምርታማነት እንዲጨምር አርብቶ አደሮቹን በክላስተር የማደራጀት ስራ፣ በምርጥ ዘር አመራረት፣ አቀማመጥ እና ለገበያ አቀራረብ ላይ ሥልጠናና የልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ እንዲሁም አዳዲስ የግብርና ቴክኖሎጂ እንዲጠቀሙ የሚያስችል ስራዎች በስፋት ተሰርተዋል።

አካባቢው ለስንዴ ምርት ተስማሚ መሆኑ በጥናትና ምርምር በማረጋገጥ ከተለዩ 25 የስንዴ ዝርያዎች መካከል ድርቅንና በሽታን መቋቋም የሚችል እንዲሁም ከአካባቢው የአየር ንብረት ጋር የሚስማማ ምርጥ የስንዴ ዘር በዩኒቨርሲቲው ባለሙያዎች ተለይቶ ለአርብቶ አደሮቹ በመስጠት ሕይወታቸውን የሚያሻሽል ስራ ተሰርቷል ሲሉ ጠቅሰዋል።

በዚህም ባለፉት ሁለት ዓመታት ከ130 ኩንታል በላይ የስንዴ እና 15 ኩንታል የበቆሎ ምርጥ ዘር ተከፋፍሎ 1077 ኩንታል ምርጥ ዘር በማምረት ዘሩን ከራሳቸው የምግብ ፍጆታ አልፈው ለገበያ በማቅረብ 4 ነጥብ 2 ሚሊዮን ብር ገቢ ማግኘት ችለዋል። ይህም ግብርናቸውን የበለጠ ማዘመን የሚያስችል አዲስ ብራንድ ትራክተር እንዲገዙ አግዟቸዋል ሲሉ አብራርተዋል።

ባለፉት ሁለት ዓመታት የተገኘው አመርቂ ውጤት በማየት በ2014 የሰብል ማሳ ዝግጅት ወቅት 201 ሄክታር ስንዴ ማልማት መቻሉን ገልጸው በተለይ መንግሥት ለበጋ ስንዴ ልማት የሰጠውን ትኩረት ከፍተኛ እገዛ እንዳደረገላቸው ጠቁመዋል።

ከፕሮጀክቱ ተጠቃሚ የሆኑ አርሶ አደሮች በሰጡት አስተያየት ከሶስት ዓመት በፊት በነበረው ግጭትና ተደጋጋሚ ድርቅ የተረጋጋ ኑሮና የግብርና ስራ መስራት እንዳልቻሉ አስታውሰው አሁን መንግስት፣ ዩኒቨርስቲው እና አይ ሲ አር ሲ ተቀናጅተው በሚያደርጉላቸው ድጋፎች ሰላማዊ ሕይወት መምራት ብቻ ሳይሆን ምርጥ ዘር አብቃይ መሆን ችለናል ብለዋል።

በግብርና ስራ የተሰማራችው አሚና በከር በሰጠችው አስተያየት ከዚህ በፊት የአካባቢው አርብቶ አደሮች የነበራቸው አነስተኛ የግብርና እውቀት፣ ድርቅና ግጭት ተረጋግተው ኑሯቸውን እንዳይመሩ አድርጓቸው እንደነበር ገልጻለች። በአንድ ወቅት 50 ኩንታል ዘርታ 17 ኩንታል በማግኘት ለከፍተኛ ኪሳራ ተዳርጋ እንደነበረ ተናግራ በየጊዜው በሚደረግላት ድጋፍና ክትትል ምርጥ ዘር ለገበያ በማቅረብ ገቢ ማግኘት መጀመሯን ትናገራለች።

አብዱልፈታ ዳውድ በበኩሉ በወረዳው ምቹና ሰፊ መሬት ቢኖርም ድርቅ እና ከለውጡ በፊት በነበረው ግጭት ከቀያቸው ተፈናቅለው ለተለያዩ ችግሮች ተጋልጠው እንደነበር ጠቁሞ፤ መንግሥት ወደ ቀያቸው እንዲመለሱ ካደረገ በኋላ ዩኒቨርሲቲውና አይ ሲ አር ሲ ባደረጉላቸው ድጋፍ ተረጋግተው የግብርና ስራ እንዲሰራ እንዳስቻለው አስታውቋል።

ዩኒቨርሲቲው እና አይ ሲ አር ሲ የጀመሯቸው ስራዎች ተጠናክረው በሌሎች ቦታዎች ላይ ማስፋት ከተቻለ አካባቢውን መለወጥ ብቻ ሳይሆን መንግሥት በስንዴ ምርት የያዘውን አገራዊ እቅድ ለማሳካት ያስችላል ሲሉ ተናግረዋል።

# በሳይንስና ቴክኖሎጂ ማዕድ የሞላው ሙዚየም

ጌትነት ምህረቴ



ፎቶ - በፀሐይ ንጉሤ

አቶ አህመድ ሰይድ



ወይዘሮ ጽጌረዳ ደምሴ



የዲዲያ ማሪሁን፤

የጊቢው ውበት ውጡ ውጡ አያሰኝም። የዛፎቹ፣ የሳሩ፣ የአበቦቹና የህንጻዎቹ ማራኪነት ያስደምማል። አዲሱ የኢትዮጵያ ሳይንስ ሙዚየም ቅርጽና ኪነ ህንጻው እንደ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ፈጠራ ስራዎች እውቀትና ክህሎት የፈሰሰበት መሆኑ አያጠራጥርም። ፈረሱም ይኸው ሜዳውም ይኸው እንደሚባለው ሙዚየሙ በኢትዮጵያውያን የሚፈልቁ የሳይንስና ቴክኖሎጂ የፈጠራ ስራዎች ዕውቀትና ክህሎት መለዋወጫ ማዕድ ሆኖ ያገለግላል ተብሎ የሚጠበቅ ነው።

በተለይ በሳይንስና በቴክኖሎጂ የፈጠራ ስራዎች ፍላጎትና ልምዱ ያላቸው ወጣቶች፣ ህጻናትና ተመራማሪዎች ዓላማቸውን እንዲያሳኩ የሳይንስ ሙዚየሙ መነሳሳትና ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል። በሳይንስ ሙዚየሙ ሁለት ህጻናት ልጆቿን ይዛ ስትጎበኝ ያገኘናት ወይዘሮ ጽጌረዳ ደምሴ ሙዚየሙ ለምርምርና ለፈጠራ ስራ የሚያነቃቃ፣ በጣም የሚያምርና ብዙ ነገሮችን በውስጡ የያዘ ነው ትላለች።

ልጆቼ ለሳይንስና ለቴክኖሎጂ ያላቸው ፍላጎት ከፍተኛ ስለሆነ ሙዚየሙን አይተው መነቃቃት እንዲፈጠርባቸው ነው ለጎብኚት ክፍት እንደሆነ በመጀመሪያው ቀን ይዣቸው የመጣሁት የምትለው ወይዘሮ ጽጌረዳ፤ ሙዚየሙን የእውቀትና የክሂሎት መድረክ ሆኖ ለኢትዮጵያና ለህዝቧ የሚጠቅሙ የቴክኖሎጂና የሳይንስ የፈጠራ ስራዎች መፍለቂያ ይሆናል የሚል እምነት አላት።

ወላጆች ህጻናት ልጆቻቸውን ይዘው የሳይንስ ሙዚየሙን መጎብኘት አለባቸው። ልጆቻቸው ለሳይንስና ቴክኖጂዎች ፈጠራዎች እንዲነሳሱ ያደርጋል ብላለች።

ወጣቱ ከዚህ የሳይንስ ሙዚየም ብዙ የሚማርበትና ክሂሎት የሚቀስምበት ማዕከል ይሆናል የሚል እምነት አለኝ የሚለው ከአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የሳይንስ ሙዚየሙን ለጎብኘት የመጣው ይዲዲያ ማሪሁን፤ ሙዚየሙ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ፈጠራዎችን ለማስፋፋት፣ ወጣቱና ህጻናትን እንዲነሳሱ ያደርጋል ነው ያለው።

እንደ ሳይንስ ሙዚየሙ አይነት ተቋማት ቀድሞ አለመኖራቸው ወጣቶችና ህጻናት የሳይንስና የቴክኖሎጂ የፈጠራ ተሰጥኦቸውን እንዳያወጡ፣ እንዳያስተዋውቁት አድርጓል። የኢትዮጵያ የሳይንስ ሙዚየም መገንባቱም የሳይንስ ፈጠራ ተሰጥኦ ያላቸው ሰዎች በብዛት እንዲፈሩና ስራቸውንም አገርና ወገን እንዲጠቀምባቸው ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል ብሏል።

የኢትዮጵያ ዘመናዊ የሳይንስ ሙዚየም እንዲኖራት መደረጉ ህጻናትም ሆነ ወጣቶችን ለፈጠራ ስራ ያነቃቃል። የተሻለ አስተሳሰብ እንዲኖራቸው ያደርጋል የሚሉት አቶ አህመድ ሰይድ፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ይህን የመሰለ ዘመናዊ የሳይንስ ሙዚየም መኖሩ በራሱ ለሳይንስና ለቴክኖሎጂ ዘርፉ ትልቅ ትኩረት እንደተሰጠው ያሳያል ነው ያሉት። ሁሉም ዜጋ ልጆቹን ይዞ በመሄድ ሳይንስ ሙዚየሙን ማስጎብኘት እንደሚኖርበትም መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

አዲሱ የኢትዮጵያ የሳይንስ ሙዚየም የተሻለች ኢትዮጵያን ለመፍጠር የሚያነሳሳና ለሳይንስ ፈጠራ ስራዎችም እንደ ማስፈጠሪያ ሆኖ የሚያገለግል መሆኑን የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ሙዚየሙን መርቀው ሲከፍቱ ገልጸዋል። ሙዚየሙ በሳይንስ ዘርፉ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመዝለቅ የቴክኖሎጂና በሳይንስ የልህቀት ማዕከል ሆኖ ያገለግላልም ብለዋል።

በቀለበት ቅርጽ እና በጉልላት መልክ የታነፀው የኢትዮጵያ የሳይንስ ሙዚየም በሰባት ሔክታር መሬት ላይ ያረፈ ሲሆን የሳይንስ ሙዚየሙ በውስጡ ሁለት ግዙፍ ሕንፃዎችን ይዟል። ትልቁ ሕንፃ ከ15 ሺህ ሜትር ካሬ በሚበልጥ መሬት ላይ ያረፈ ነው።

የሳይንስ ሙዚየሙ ከአጠቃላይ ጊቢው 80 በመቶ የሚሆነው ክፍሉ በአገር በቀል ዛፎች፣ ዕፅዋትና አበቦች የተሸፈነ ነው። ሙዚየሙ ከመኪና ማቆሚያዎች በተጨማሪ በዙሪያው ካሉ የመዲናይቱ ፓርኮች ጋር የሚያገናኘው የእግረኛ መንገዶች አሉት። በሙዚየሙ ውስጥ ቋሚ እና ጊዜያዊ አውደ ርዕይ ማሳያዎችንም አካቶ ይዟል።

የሳይንስ ሙዚየም ትናንት፣ ዛሬንና ነገርን በአንድ ላይ አያይዞ ሳይንስን ጥበባዊ በሆነ መንገድ፣ ጥበብን ደግሞ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የሚያስቃኝ ሲሆን ተሞክሮዎችና አዳዲስ ዕውቀቶች የሚቀስሙበት መድረክ ነው።

# የማምሻ እድሜን አኗኗር ያፈኩ የበጎ ስራዎች

ዳግማዊት ግርማ





የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በቂርቆስ ክፍለ ከተማ የቤት ዕድሳት

በሰለጠንን ባዮቹ ዓለም ላይ ግለኝነት በዝቶ ኑሮ ሁሉ ለየብቻ ሆኗል፤ ኀዘን በር ተዘግቶ የሚለቀስ ደስታም ለብቻ ታምቆ የሚያዝ የውስጥ ሳቅ ነገር ነው። ኢትዮጵያ ግን አሁንም በአብሮነት መንገድ ላይ ተጓዥ ናት። በሀገሪቷ ነዋሪዎች መሀል ለብቻ የሚባል ነገር ዘበት ነው። በሀገር ውስጥ ያለን ሰዎች ሲከፋን አብሮ ተከፊ ኀዘንን ተገንዛቢ ወገን መሀል ነን። ለብቻ በማይበላ ሰው ለችግራችን የሚደርስ ጎረቤት ለሳቃችን ደጋሽ ሰዎች አሉን።

ሀገርን አስተዳዳሪው መንግሥትም ሕዝብ ከሌለ መንግሥትም የለም በማለት በብዙ የበጎ ፈቃድ አገልግሎቶች ላይ ሲሳተፍ ማየት እየተለመደ መጥቷል። መንግሥት አመራሮቹን ከወንበራቸው ሳይሆን ከድሆች ደጃፍ በመገኘት እንዲረዱና እንዲደግፉ አድርጎ አሰልጥኗል።

ይህንንም ከዚህ ቀደም አይተን በማናውቀው መልኩ የሀገሪቷ መሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድም ሳይቀሩ ዝቅ ብለው የድሆችን ቤት ሲያድሱና የተለያዩ መልካም ተግባራትን ሲከውኑ ተመልክተናል። መንግሥት የሕዝቡን ችግር የነዋሪውን ህመም በመረዳት የተለያዩ ተግባራትን በመከወን ላይ ነው።

የመንግሥት ተሿሚዎች በብዙ መልካም ተግባራት ላይ ሲሳተፉ ቢታዩም የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት ትግበራ ግን በበለጠ መንገድ አብዛኛውን ጊዜያቸውን ማሳለፊያቸው ከሆነ ውሎ አድሯል። በዚህ ከመንግሥት ካዝና ይወጡ የነበሩ ብዙ ሚልዮኖችን ባዳነው የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት ምክንያት ብዙዎች እምባቸው ታብሷል። በዚሁ መልካም ሃሳብ ምክንያት እልፎች ተመግበው አድረዋል፤ ብዙ መልካሞች ለብዙ ጧሪ የሌላቸው ወገኖች ደርሰዋል።

ከነዚህ የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት ውስጥ ከሚሰሩ ተግባራት መካከል አንዱ የቤት እድሳት ነው። ቤት ገመናን ሸፋኝ፣ ብቸኝነትን ተጋሪ፣ ቢገኝ ተበልቶ ቢታጣ ፆም የሚታደርበት፣ የቀኑን ፀሀይ የማታውን ብርድ ማምለጫ ታዛ፣ በሌትም ከአራዊት አውሬነት መሸሸጊያ ነው። ቤት መጦርያ ነው፤ የእድሜ ማምሻ የሚዋብበት። ቤት ማረፍያ ነው፤ ከዓለም ሁካታ የሚመለጥበት። አንድ ቤት ብቻውን እልፍ ጥቅም አለው።

የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርም የዚሁ መልካም ተግባር ተጋሪ ሆኖ ሰሞኑን በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ ስምንት ልዩ ስሙ መናኸርያ አካባቢ ለሚገኙ አምስት አባወራዎች የቤት እድሳት በማከናወን የየቤቶቻቸውን ቁልፍ አስረክቧል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትም በሚኒስቴር መስሪያቤቱ ቤት የተገነባላቸውን እናቶች ምን ተሰማችሁ ብሎ ጠይቋል፤ እነሱም እናታዊ ምርቃታቸውን በማዥጎድጎድ የተሰማቸውን ጥልቅ ደስታ ገልፀውልናል።

ወይዘሮ እልፍነሽ ዘውዱ ይባላሉ፤ መንግሥት ከማደሱ በፊት በነበረው ቤታቸው ከጃንሆይ ዘመን ጀምሮ ኖረውበታል። በቅጡ በማያስታውሱት እድሜያቸው ብዙ አይተውበታል። አራት ልጆቻቸውን ያሳደጉት በዚሁ ደሳሳው ጎጇቸው ውስጥ ነው። ቤቱ ከመጎዳቱ የተነሳ አውሬ እንዳይበላቸው ይሰጉ ነበር። ሕይወት ባሮጌ ቤታቸው መከራ የበዛባት ነበረች። ጓዳ ጎድጓዳው ለባዳ የማይታይ አብሮ ኗሪ ወገን የሚረዳው ገንዘብ ብዙ ነበር።

ቤታቸው ከታደሰላቸው በኋላ በብዙ ተለውጧል። ዓለሜን አሳዩኝ በስተርጅና ወግ ማዕረግ አሳዩኝ ሲሉ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እንዲሁም ደግ አሳቢዎችን ሁሉ አመስግነዋል። የቤቱ መታደስ ከክፉ አውሬዎች አትርፎኛል ብለዋል።

ሌላኛዋ ቤት የታደሰላቸውና አስተያየታቸውን ለድርጅታችን የሰጡት ደግሞ ወይዘሮ እታገኝ አክሊሉ ይባላሉ። ወይዘሮ እታገኝም በቤት እድሳቱ የተሰማቸውን ደስታና ምስጋና ገልፀዋል። አሮጌ ቤታቸው ጠባብና በራሳቸው ላይ ሊወድቅባቸው የደረሰ እንደነበር አውስተዋል። የ68 ዓመቷ ወይዘሮ ባልታደሰው ቤታቸው 48 ዓመት ኖረዋል።

ሚስትሯ ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬም በቤት እድሳቱ ቁልፍ ርክክብ ላይ ተገኝተው መልዕክት አስተላልፈዋል። ሚኒስትሯ በገለፃቸው ኢትዮጵያን ለማበልፀግ ሰው ተኮር ስራዎች ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይገባል ብለዋል።

ልማት ሰው ላይ ካላረፈና የሰውን ሕይወት ካልለወጠ ልማት ነው ልንለው አንችልም፤ የኢትዮጵያን የብልጽግና ጉዞ ለማረጋገጥ ሰው ተኮር ስራዎቹ ቀጣይነት መኖራቸውን ማረጋገጥ እንደሚገባ አፅንኦት ሰጥተው ገልፀዋል።

ኢትዮጵያ ትበለፅጋለች ስንል ቁሳዊ ብቻ ሳይሆን ሁሉን አቀፍ ብልፅግና እንዲኖር ነው መስራት ያለብን ብለዋል። የማህበራዊ ተቋማት ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ የማድረግ ስራን ሊሰራ እንደሚገባው የገለጹት ሚኒስትሯ፤ መስሪያቤቱ በመሰል ተግባራት ፋና ወጊ በመሆን የአርአያነት ስራን ማከናወኑን ተናግረዋል።

ማህበራዊ ችግሮች በመንግሥት ብቻ የሚያልቁ አለመሆናቸውን ያመላከቱት ዶክተር ኤርጎጌ ሁሉም ሰው ከተረዳዳ ምንም የሚያቅተን ነገር እንደማይኖር ጥቂት የጀመርነው ስራ አሳይቶናል ብለዋል።

# የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ወጥነት እንዲኖረው የአሰራር ማዕቀፍ እየተዘጋጀ ነው

አስናቀ ፀጋዬ

አዳማ፡- የወጣቶች የበጎ ፍቃድ አገልግሎት አሰጣጥ በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥነት እንዲኖረው ብሔራዊ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ፖሊሲና የአሰራር ማዕቀፍ እያዘጋጀ እንደሚገኝ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ገለጸ።

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ባዘጋጀው የ2014 ዓ.ም ሀገር አቀፍ የክረምት ወራት የወጣቶች የበጎ ፍቃድ አገልግሎትና አረንጓዴ አሻራ የማጠቃለያ መርሐ ግብር ላይ የተገኙት የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ እንደገለጹት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት የወጣቶችን የእርስበርስ ግንኙነትን ያጠናከረና ኢትዮጵያዊነትን ከፍ ያደረገ ነው።

ከዚህ አካኳያ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የወጣቶች የበጎ ፍቃድ አገልግሎት አሰጣጥ በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥነት እንዲኖረውና የታለመለትን ግብ እንዲመታ ብሔራዊ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ፖሊሲና የአሰራር ማዕቀፍ እያዘጋጀ መሆኑን ጠቁመዋል።

ለዚህም ስታንዳርድ በማውጣትና ትግበራውንም በማስተባበር፣ በመከታተልና አፈፃፀሙንም በመገምገም እንዲሁም በየደረጃው የሚገኙ አስፈፃሚ አካላትን አቅም በማጎልበት የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት የሚያግዙ የግንዛቤና ንቅናቄ መድረኮችን እያመቻቸ ለስኬታማነቱ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ እየተንቀሳቀሰ እንደሚገኝም ሚኒስትሯ ገልጸዋል።

የወጣቶች የበጎ ፍቃድ አገልግሎት በኢትዮጵያ ባህል ሆኖ እንዲቀጥል ሥርዓት መዘርጋት እጅግ አስፈላጊ መሆኑንና የሚሰጡ አገልግሎቶች ለምን ያህል ማህበረሰብ ደረሱ? ምን ያህል ወጪስ አዳኑ? የሚለውን በስታንዳርድ ለይቶ መሄድ ተገቢ ስለሚሆን የፖሊሲና የአሠራር ማዕቀፉን እየተዘጋጀ እንደሚገኝ አብራርተዋል።

አገልግሎቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ መሰጠት ከጀመረበት ከ2002 ዓ.ም ጀምሮ ወጣቶች በማህበረሰቡ ውስጥ የሚያከናውኗቸው ማንኛውም ተግባራት በክረምት ብቻ ሳይሆን በበጋ ወራት ከሚያካሂዱት የበጎ ፍቃድ አገልግሎቶች በባለቤትነት ስሜት እየተሳተፉ ያሉ ወጣቶች ቁጥር ከጊዜ ወደጊዜ እያደገ ሊመጣ ስለመቻሉ ጠቁመዋል።

እስካሁንም በርካታ ወጣቶች በልዩ ልዩ መስኮች በመሰመራት አካባቢያቸውንና ማህበረሰባቸውን ተጠቃሚ ያደረጉ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን ሲያከናውኑ መቆየታቸውንም ሚኒስትሯ ጠቅሰዋል።

ዜና

# ቴክኖሎጂን በመጠቀም ዘርፉን የማስተዋወቅና የማነቃቃት ስራ እየተከናወነ ነው



አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- ዓለም የደረሰበትን ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም የቱሪዝም ሀብታችንን የማስተዋወቅና ዘርፉን የማነቃቃት ስራ እያከናወነ መሆኑን የቱሪዝም ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ ሰሞኑን የአርኪዮሎጂ እና የቨርቹዋል ሪያሊቲ እንዲሁም የሴኖግራፊ አውደ ርዕይ በእንጦጦ ፓርክ ለእይታ ቀርቧል፡፡

በአውደርዕዩ መክፈቻ ላይ የተገኙት የቱሪዝም፣ ሚኒስትሯ አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ እንደተናገሩት፤ የኢትዮጵያን የምህንድስና ጥበብ ለዓለምአቀፉ ማህበረሰብ በስፋት ለማስተዋወቅና የኢትዮጵያን የቱሪዝም ዘርፍ ለማነቃቃት ቴክኖሎጂ ጉልህ ሚና አለው፡፡

የኢትዮጵያን የምህንድስና ጥበብ ለዓለምአቀፉ ማህበረሰብ ለማሳየትና የቱሪዝም ዘርፍ ለማነቃቃት ዘመኑ የደረሰበትን ቴክኖሎጂ መጠቀም አስፈላጊ በመሆኑ የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ለእይታ እንዲቀርቡ ተደርጓል ብለዋል።

የዲጅታል ኤግዚቢሽኑ ከሶስት ዓመት በፊት የፈረንሳዩ ፕሬዚዳንት ኢማኑኤል ማክሮን ሀገራችንን በጎበኙበት ወቅት ላሊበላን ለማደስና ለመጠበቅ ቃል በገቡት መሠረት ከታቀዱት ስራዎች መካከል አንዱ እንደሆነ የተናገሩት አምባሳደር ናሲሴ፣ የአውደ ርዕዩ ዋና ዓላማ ቅርሱን ለሀገር ውስጥና ለውጭ ሀገር ጎብኚዎች በስፋት ማስተዋወቅ ነው ብለዋል።

እንደ አምባሳደር ናሲሴ ገለፃ፡- አውደ ርዕዩ በቱሪዝም ሚኒስቴር፣ በፈረንሳይ መንግሥት፣ በፈረንሳይ ልማት ደርጅት፣ በቅዱስ ላሊበላ አብያተ ክርስትያናት፣ በቅርስ ጥበቃ ባለሥልጣን ትብብር የተከፈተ ነው። በዚህም የላሊበላን አጠቃላይ ገፅታ የሚያሳዩ ፎቶግራፍ ምስሎች፣ ቅርጾች፣ የአካባቢውን ማህበረሰብ አኗኗር የሚያንፀባርቁ ምስሎች ከገለጻቸው ጋር እንዲሁም የመስህብ ስፍራው ለአካባቢው ነዋሪ ምን ማለት እንደሆኑ የሚገልጹ አጫጭር የተንቀሳቃሽ ምስል መልእክቶች ለእይታ ቀርበዋል።

ይህ በአይነቱ ልዩ የሆነ የ3ዲ ቨርቹዋል ሪያሊቲ ዲጅታል አውደ ርዕይ እንደ ሀገር የዲጅታል 2025 እቅድ አንዱ አካል ሲሆን ዘርፉን ወደፊት አንድ እርምጃ የሚያራምድ እንደሆነና በላሊበላ የተጀመረው ይህ ስራ በሌሎች የቱሪዝም መስህቦች ላይም በስፋት እንደሚቀጥል ገልጸዋል፡፡

125ተኛው የኢትዮጵያና የፈረንሳይ የሁለትዮሽ ግንኙነት አስመልክቶ ይህንን ዲጅታል አውደርዕይ እንደተከፈተ የገለጹት አምባሳደር ናሲሴ፣ በቀጣይ በኢትዮጵያ መንግሥትና በዩኔስኮ ጥያቄ መሠረት ከፍተኛ ጥናት ሲካሄድባቸው የቆዩ ቅርሶቹን የማደስ ስራዎች እንደሚሰሩና አጠቃላይ ስራውን አስመልክቶ የፈረንሳይ መንግሥት በፈረንሳይ ልማት ድርጅት በኩል 500 ሚሊዮን ዩሮ ድጋፍ ማድረጉን ገልጸዋል፡፡

የፈረንሳይ መንግሥት የኢትዮጵያን የቱሪዝም መስህቦች በመጠበቅ ስራው ከዚህ ቀደም የብሄራዊ ሙዚየምን የማስተካከል ስራ እንደሰሩ ገልጸው፣ ቀጣይ እቅዳቸውን በአዲስ አበባና ሌሎች ክልሎች የቱሪዝም መስህቦችን የማልማትና የሰው ሃይል የማሰልጠን ስራዎች እንደሚሰሩ ገልጸዋል፡፡

ቴክኖሎጂ ዘርፉን ለማሳደግ አስፈላጊ መሆኑን ገልጸው፣ ያለንን የቱሪዝም ሀብት ቴክኖሎጂን ተጠቅሞ ከማስተዋወቅ አንፃር ብዙ ሥራ ይቀረናል ብለዋል።

በመሆኑም በቱሪዝም ዘርፉ ያሉ የፕሮሞሽንና ማርኬቲንግ፣ የአገልግሎት ብቃት ማረጋገጫና ሌሎችንም ዘርፎች ዲጅታይዝድ በማድረግ ጎብኚዎች ኢትዮጵያን እንደ አንድ የቱሪስት መዳረሻ እንዲያደርጉ ማስቻል ላይ ትኩረት መስጠቱን ገልጸዋል። አውደ ርዕዩም ዘርፉን በቴክኖሎጂ ለመደገፍ የሚያስችል ግብዓት የሚሰበሰብበት እንደሆነም ተናግረዋል።

## የአሸባሪው ትህነግ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በአሁኑ ወቅት በክልሉ ትምህርት፣ ህክምና እንዲሁም ፍትህ እንዳይኖር እያደረገ ያለው አሸባሪው ሕወሓት ትግራይን መንግሥት አልባ በማድረግ በአሸባሪዎች እንዲመራ አድርጎታል ብለዋል፡፡

ይህን ኃይል ካለበት ቦታ ለማስወገድ የትግራይ ሕዝብ ብቻ ኃላፊነት አይደለም ያሉት አቶ መኮንን ፣ የሁሉም የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ እንዲሁም ከትግራይ ውጪ ያለው የትግራይ ተወላጅ ጭምር ነው ብለዋል፡፡

አቶ መኮንን ፣ በተለይም ትግራይን ወክለን እየተንቀሳቀስን ያለነው የትግራይ ፖለቲከኞች ከትግራይ ውጪ ካለው የትግራይ ተወላጅ ጋር በመሆን ልቦናው ወደ እውነታው እንዲመለስ የማድረግ ሥራ መሥራት ይጠበቃል ብለዋል፡፡

## ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ አገራዊ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ጀምረነዋል። ለዚህ ትልቁ ማሳያ ሶማሌ ክልል ነው። በክልሉ በአሁኑ ጊዜ በሄክታር 40 ኩንታል በላይ ማምረት የሚቻልበት ሁኔታ ተፈጥሯል።

ዘንድሮ በሚሊዮን ኩንታል የሚቆጠር ስንዴ ለውጭ ገበያ እናቀርባለን ያሉት ዶክተር ዐቢይ፣ ለዚህ ስኬታማነትም አመራሩን ጨምሮ ሁሉም የሚመለከተው አካል ርብርብ ማድረግ እንደሚኖርበት አሳስበዋል፡፡

እኛ ኢትዮጵያውያን ሰፊ መሬት፣ ታታሪ አርሶ አደርና ለም መሬት አለን ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፣ ከስንዴ ጋር የተያያዘውን ችግር ሙሉ ለሙሉ በመፍታት አዲስ ታሪክ መጻፍ ይኖርብናል ነው ያሉት።

ኢትዮጵያን አጥግበን ለሌሎች ለመትረፍ የዘንድሮው በጋ ወሳኝ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ 2015 ዓ.ም የብዙ ድሎችና መሻገሮች ዓመት እንደሚሆንም ገልጸዋል።

በሶማሌ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሙስጠፌ ሙሐሙድ በበኩላቸው በዘንድሮ የበጋ ስንዴ ልማት ሁለት ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ለማግኘት ዝግጅት ተደርጓል ብለዋል።

ርዕሰ መስተዳድር ሙስጠፌ፣ አገራዊ የበጋ ስንዴ መስኖ ልማት ይፋ ሲደረግ እንደገለጹት በክልሉ በተደጋጋሚ የሚከሰተውን ድርቅ በዘላቂነት ለመከላከልና ምርታማነትን ለማሳደግ በ2015 በጀት ዓመት በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ሁለት ሚሊዮን ኩንታል በላይ ስንዴ ለማልማት ዕቅድ መያዙንና ይህን ለማሳካትም አስፈላጊው ዝግጅት መደረጉን ጠቁመዋል፡፡

ድርቅን ሁልጊዜ በዕርዳታ ስንዴ መቋቋም የለብንም በሚል የጀመርነው የስንዴ ልማት አመርቂ ውጤት አግኝተንበታል ያሉት አቶ ሙስጠፌ፣ የስንዴ ልማቱ የዋጋ ንረትንና ድርቅን በዘላቂነት ከማርገብ አኳያ ትልቅ ፋይዳ አለው ብለዋል። ባለፈው ዓመትም የሶማሌ ክልል 847 ሺህ ሄክታር ስንዴ ማልማት መቻሉን ጠቅሰዋል።

በ2015 ዓ.ም በክልሉ የሚገኙ ሶስት ወንዞችንና የጉድጓድ ውሃ በመጠቀም ከሁለት ሚሊዮን ኩንታል በላይ ስንዴ ለማልማት ዝግጅቱ እየተጠናቀቀ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

ዘንድሮ በበጋ ስንዴ በሀገር አቀፍ ደረጃ አንድ ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በማልማት 52 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ለማግኘት ዕቅድ ተይዟል። ይህም የአገርን ፍጆታ ሙሉ ለሙሉ ከማሟላት ባለፈ ለውጭ ንግድ ማቅረብ እንደሚያስችል ተገልጿል።

ባለፈው ዓመትም በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት 24 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ መገኘቱን ግብርና ሚኒስቴር ገልጿል።

ባለፉት አራት ተከታታይ ዓመታት በበጋ ስንዴ ልማት ለተገኘው አመርቂ ውጤትም ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድን ጨምሮ የከፍተኛ የአመራር ቁርጠኝነት ፣ የተቀናጀ የፋይናንስ ድጋፍና አገራዊ የስንዴ የመስኖ ፕሮጀክት አስተባባሪ ጽህፈት ቤት መዘርጋቱ ከፍተኛ ሚና ማበርከቱ ተገልጿል ።

## 72 ተቋማት የኤሌክትሮኒክስ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እንደ አቶ ታደሰ ገለጻ፤ የመጀመሪያው የበጀት ዓመት ጊዜ የእቅድ ማቀጃ ጊዜ በመሆኑ ተቋማቱ የግዥ እቅዳቸውን አዘጋጅተዋል። በሥርዓቱ ተጠቅመው ግዢያቸውን ፈጽመዋል። ይህ አዲስ ሥርዓት በኢትዮጵያ ዘርፈ ብዙ ችግር ያለበትን የግዥ ሥርዓቱን ያስተካክለዋል ተብሎ ይጠበቃል።

ሥርዓቱ ለመንግሥትና ለተጫራቾች ጠቀሜታ አለው ያሉት ማናጀሩ፤ ለመስሪያ ቤቶች ተመጣጣኝ በሆነ ዋጋ ደረጃውን የጠበቀ እቃዎችን ለመግዛት ያስችላቸዋል ብለዋል። የግዥ ጨረታዎች በሥርዓቱ ሲሆኑ የተወዳዳሪ ቁጥር የሚጨምር በመሆኑ ጥራት ያለውን እቃን በተመጣጣኝ ዋጋ በማግኘቱ ረገድ ጠቀሜታ አለው ሲሉም ተናግረዋል።

ይህ ሥርዓት ከምንም በላይ ጊዜንና ገንዘብን ይቆጥባል የሚሉት ማናጀሩ፤ ከተጫራቾች አኳያ ጊዜና ቦታ ሳይገድባቸው በማንኛውም ሰአት የመጫረቻ ሰነዶችን ከፖርታል ላይ ማግኘትና መጫረት ይችላሉ። ጋዜጣ ለማየት ጊዜ አያባክኑም፤ በኦንላይንም መጠቀም ይችላሉ፤ ይህ ደግሞ ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀስ የሚያውጡትን የትራስፖርት ወጪ ይቀንስላቸዋል ብለዋል።

እንደ አቶ ታደሰ ገለጻ፤ በማንዋል ሥርዓቱ ተጫራቾች ጨረታው ወደ አለበት መሄድ ይጠበቅባቸዋል፤ ሰነዶችን መግዛት የሚችሉት በመንግሥት የስራ ሰአት ብቻ በመሆኑ ለከፍተኛ ወጪ ይዳረጋሉ። ከዚህ አንጻር አዲሱ አሰራር ለአገር ኢኮኖሚ እድገትም ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል።

እንደ ፕሮጀክት ማናጀሩ ገለጻ፤ በኢትዮጵያ አንድ ጨረታ እስኪጠናቀቅ በአማካኝ ሁለት መቶ አስራ ሰባት ቀናት ይፈጃል። አዲሱ ሥርዓት ተግባራዊ ሲሆን ይህንን ጊዜ በግማሽ ማውረድ ይችላል። የተወዳዳሪን ቁጥር በእጥፍ በመጨመር ጥራት ያለው እቃ ማግኘት ያስችላል።

መንግሥት ለጨረታ ማስታወቂያና ለህትመት የሚያወጣውን ዋጋ በመቀነስ ከፍተኛ ብርን ማትረፍ ያስችላል። እንዲሁም የወረቀት ሕትመትን በማስቀረት ለግሪን ኢኮኖሚም ጠቀሜታ አለው ብለዋል።

ጥናቶች እንዳረጋገጡት የኤሌክትሮኒክስ የመንግሥት ግዥ ሥርዓትን የሚጠቀም ማንኛውም አገር ለግዥ ከሚያወጣው የትራንዛክሽን /የገንዘብ ልውውጥ/ ወጪ ከአምስት እስከ ሃያ አምስት በመቶ መቀነስ ይችላል። ኢትዮጵያ በቀላሉ አንድ በመቶ ወጪ ብትቀንስ ከአመታዊ በጀት ስልሳ አምስት በመቶው ለግዥ የሚወጣ በመሆኑ ከፍተኛ ገንዘብ ማትረፍ እንደምትችል ገልጸዋል።

የኤሌክትሮኒክስ የመንግሥት ግዥ እንደ ዓለም ከፍተኛ ጥቅም አስገኝቷል ያሉት ማናጀሩ፤ እ.ኤ.አ በ1991 ካናዳ ለመጀመሪያ ጊዜ መጠቀም መጀመሯን አስታውሰዋል። ከአፍሪካ ደቡብ አፍሪካ እ.ኤ.አ በ2002 እና ናይጀሪያ በ2006 ይህንን ሥርዓት መጠቀም የጀመሩ ሲሆን ከፍተኛ ጥቅም እንዳገኙበትም ማናጀሩ ጠቁመዋል። ሥርዓቱን መጠቀም ከጀመሩ በኋላ በአንድ ጨረታ ይወዳደሩ የነበሩ የተጫራቾችን ቁጥር ከፍ ማድረግ ችለዋል።

ደቡብ ኮሪያ በአመት እስከ ስምንት ቢሊዮን ዶላር፣ ባንግላዲሽ ከአንድ ነጥብ አንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ ይባክን የነበረ ብርን ማዳን ችለዋል። ሰላሳ ሰአት ይወስደባቸው የነበረውን የግዥ ሥርዓት ወደ ሰላሳ ደቂቃ ማውረድ ችለዋል። ሕንድ ከዘጠና አምስት ቀን እስከ አንድ መቶ አስር ቀን ይወስድባት የነበረውን ወደ ሰላሳ ቀን መቀነስ መቻሏን ገልጸዋል። እንዲሁም ቺሊ ይህን ሲስተም ተጠቅማ ግዥ መፈጸም ከጀመረች በኋላ ዘጠና አምስት በመቶ የሚሆነው ሕዝብ በመንግሥት ግዥ እርካታ ማግኘቱን ገልጸዋል። ኢትዮጵያም ይህን ሥርዓት መጠቀም ብትጀምር በርካታ ገንዘብ ማትረፍ ትችላለች።

የኤሌክትሮኒክስ የመንግሥት ግዥ ሥርዓት የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዘዴዎችን በመጠቀም ግዥ ፈጻሚ መስሪያ ቤቶች ጨረታ በአየር ላይ እንዲያወጡ የሚያደርግና ተጫራቾችም በኦንላይን ዘዴ ተጠቅመው እንዲጫረቱ የሚያደርግ ዘዴ ነው። መስሪያ ቤቶች ጨረታ በኦንላይን ካወጡ በኋላ የመጫረቻ ሰነዳቸውን፣ ቅሬታ ካላቸው ቅሬታቸውን በሲስተሙ ማስገባት ይችላሉ። ኦዲት የሚያደርጉ ተቆጣጣሪ አካላትም በሥርዓቱ ውስጥ ገብተው ኦዲት ማድረግ እንደሚችሉ አቶ ታደሰ ገልጸዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለድርድር የሚቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎች ተቀባይነት የላቸውም

ሰላምን የሁል ጊዜ አማራጭ አድርጎ ለመጠቀም ከሁሉም በላይ ስለሰላም የጸና እምነት መፍጠርን ይጠይቃል። የሰላም ጉዳይ ወቅታዊ ሁኔታዎችን በመከተል አንስተው የሚጥሉት ሳይሆን፤ ለዚህ የሚሆን ፍጥረታዊ ሰብእና የሚጠይቅ ነው። ከዚሕ ውጪ ስለሰላም መዘመርም ሆነ ሀዋርያ ሆኖ ለመገኘት መሞከር ብዙ ርቀት የሚያስኬድ አይደለም። ያልዘሩትን የማጨድ ያህል የሚከብድ፤ ከጥቅሙም ጉዳቱ የከፋ እንደሚሆን ይታመናል።

አሸባሪውን ትህነግ በሕዝባዊ እንቢተኝነት ከሥልጣን ያስወገደው አገራዊ ሕዝባዊ መነሳሳትም ሆነ ይህንን መነሳሳት አቅም አድርጎ ወደ ሥልጣን የመጣው የለውጥ ሀይል፤ ገና ከጅምሩ የለውጡ ጉዞ ሰላምንና ሰላምን መሰረት ያደረገ እንዲሆን ነገሮችን በይቅርታና በመደመር መንፈስ ለማስኬድም ብዙ ርቀት ተጉዟል፡፡ የሰላም ፍላጎቱ እውን ይሆን ዘንድም ከፍያለ ዋጋ ተከፍሏል።

በዚህ የሰላም መንገድ ጉዞውም፣ አይደለም በሀገር ውስጥ ከለውጡ ጋር በተያያዘ ያኩረፉ ሀይሎችን፤ ለዓመታት ያለ መፍትሄ የቆየውን የኢትዮ- ኢርትራ ጉዳይ ሰላማዊ መፍትሄ እንዲያገኝ በማድረግ በቀጠናው የተሻለ ሰላምና መረጋጋት እንዲሰፍን፤ ለአካባቢው አገራት ህዝቦችም አዲስ ተስፋ ማብሰር እንደቻለ የአደባባይ ሚስጥር ነው።

የለውጡ ኃይል ነገሮችን ከጉልበት ይልቅ በንግግርና በሰላማዊ መንገድ ለማስቀጠል የሄደበት አዲስ የፖለቲካ መንገድ ብዙ ኢትዮጵያውያን ስለነጋቸው የተሻለ ተስፋ እንዲያደርጉ አስችሏል፤ አገሪቱን ከቀደመው ዘመን የግጭት አዙሪት እንድትወጣ መልካም አጋጣሚ ተደርጎ የተወሰደበት ሁኔታ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው።

ይህ የለውጥ ኃይሉ አዲስ የፖለቲካ አካሄድ ያልጣመው፤ ከሁሉም በላይ ከፍጥረቱ ጀምሮ በሀይል እምልኮ አገርንና ህዝብን ብዙ ዋጋ ሲያስከፍል የኖረው አሸባሪው ትህነግ ግን፤ ለሰላም የሚከፈለውን ዋጋና ትዕግስት እውነታውን ከመመልከት ይልቅ እንደ አቅመቢስነት በማየት የትግራይን ህዝብ ለአስርት ዓመታት ሲጠብቅ በነበረው የመከላከያ ሰራዊት ላይ ጥቃት በመሰንዘር ፍጽም ሰላም ጠልነቱን በተጨባጭ አሳይቷል።

በመቀጠልም በተከታታይ ለተጨማሪ ሁለት ጊዜያት በአገር ላይ ጦርነት በማወጅ በአጎራባች ክልሎች ላይ ባካሄዳቸው ወረራዎች ዜጎችን ለሞት፣ ለአካል ጉዳትና ለስደት ዳርገዋል። ከፍያለ የአገር እና የህዝብ ሀብትና ንብረት ዘርፏል፤ መዝረፍ ያልቻለውን አውድሟል። በዚህም በህዝባዊ እንቢተኝነት ያጣውን ስልጣን በኃይል ለማስመለስ ረጅም ርቀት ተጉዟል።

አሸባሪው ትህነግ ይሄን የሰላም ጠልነቱን ተፈጥሯዊ ባህሪ በተግባር በሚገልጽባቸው በእነዚህ ጊዜያት በመንግስት በኩል አገርን የመጠበቅ ኃላፊነቱን ከመወጣት በተጓዳኝ ለሽብር ቡድኑ የሚያቀርበውን ተደጋጋሚ የሰላም ጥሪ፤ ከዛም ባለፈ መንግስት ስለሰላም ያደረጋቸውን የተናጠል የተኩስ አቁሞች ከመቀበል ይልቅ ጊዜ መግዣ በማድረግ የትግራይን ህጻናት፣ ወጣቶች፣ አዛውንቶች፣ መነኩሳትና አይነስውራንን ሳይቀር በጦርነት በማሰለፍ ለከፋ እልቂት ዳርጓቸዋል። ዛሬም ቢሆን በዚሁ እኩይ ተግባሩ እንደቀጠለበት ነው።

ሕጻናትን ከእናታቸው ጉያ በኃይል በመንጠቅ እየፈፀመ ያለው የጭካኔ ተግባር፣ የትግራይ እናቶች አምጠው በወለዷቸው ልጆች ተስፋ አጥተው፤ ከፍ ያለ የልብ ስብራት ውስጥ እንዲገቡ አድርጓቸዋል። ይህ ለቡድኑ አዲስ ያልሆነ በቀደመውም ዘመን በነጻነት ትግል ስም ተከስቶ ጠበሳው ያላገገመ እንደነበርም ይታወሳል።

ቡድኑ ከዚህ ሁሉ ጥፋት በኋላ አሁን ላይ ስለሰላም "ሀዋርያ" ሆኖ የመቅረቡ እውነታ በብዙ መልኩ ፍጥረታዊ ባህሪውን፤ የመጣበትን መንገድ ዱካ የሚመጥን አይደለም። ከዚሕ ይልቅ አፈትልኮ በወጣው ሰነዱ ላይ በግልጽ እንዳመለከተው ሁሉ የሰላም ዲስኩሩ የማስመሰያ እና እንደ ቀደመው ሁሉ አጋጣሚውን ጊዜ መግዣ በማድረግ አገርና ህዝብ ላይ ተጨማሪ የአደጋ ምንጭ እንዳይሆን በአግባቡ ማጤን ያስፈልጋል።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የሽብር ቡድኑ ስለ ሰላማዊ ንግግር ሲያስብም ሆነ ስለ ሰላምና ድርድር ድምጹን ከፍ አድርጎ ሲጮህ እየጮሀ ያለው የሰላም ጥሪዎችን አሻፈረኝ በማለት በፈጠራቸው እልቂቶችና ውድመቶች ተጸጽቶ እና የሰላምን ሁለንተናዊ ዋጋ ተገንዝቦ ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታ በድርድሩ በመሳተፍ ለሰላም እውቅና ሊሰጥ ይገባል። ከዚህ ውጪ የተለያዩ ቅድመ ሁኔታዎችን ለመደርደር የሚደረጉ ጥረቶች በየትኛውም መመዘኛ ተቀባይነት የሚኖራቸው አይደሉም።


ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

# ለሰላም ያልታጠፉ እጆች

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

ሰላም የፍጥረታት ሁሉ ዋስትና ነው። ሕይወት ያለው ሁሉ በሰላም ውሎ ሲያድር ስለነገው መኖር መተማመንን ያተረፋል። ሰላም የነገዋን ጀንበር በድል ያሻግራል፣ የትውልድ ተስፋን ይቀጥላል፣ የሕይወት ትርጉምን ያደምቃል። ብዙሀን ያለ ሰላም ዓለም ሁሉ ምንም ስለመሆኑ በአንድ ቃል ይስማማሉ። እውነት ነው። ዓለም ያለ ሰላም ምንም ነች ምንም።

አገራችን ለዘመናት በጦርነት ስትታመስ ቆይታለች። የሰላም ትርጉሙ ባልገባቸው ኃይሎች ጠብ አጫሪነትም ህዝቦቿ ሲያልቁ፣ ንብረታቸው ሲወድምና ለስደት ሲዳረጉ ኖረዋል። ይህ የታሪካችን ደማቁ ጠባሳ ነው። የጦርነት ሀሩር ያሳረፈብን ጉዳት ስማችንን ከርሀባችን ገጽ ቀጥሎ በክፉ ሲያስነሳ፣ ሲያስነብበው ታይቷል።

ኢትዮጵያ ባህር ተሻግረው ከመጡት ጠላቶቿ ባለፈ ከጉያዋ ወጥተው፣ ከዕቅፏ ተነጥለው በወጓት ልጆቿ አይረሴ ታሪኮችን አልፋለች። ጀግንነት ከጥንት የወረሰችው ታሪክ ቢሆንም ስለ ሰላም ባላት አቋም በጎውን እያስቀደመች፣ ክፉ መንገዶችን ስታሳጥር ቆይታለች።

ስልጣን መራሹ የወያኔ ስርዓት ዙፋኑን «እምቢኝ» ብሎ ከተቆናጠጠበት ወንበር ከተወገደ ማግስት የመጀመሪያ ምርጫው የጦርነት ሜዳ ሆኗል። ሁሌም «እሞትልሀለሁ» ሲል የሚገድለውን የትግራይ ህዝብ ለጦርነት ማግዶም ለሰላም ያለውን ንቀት በግልጽ አሳይቷል።

እነሆ ! የጦርነቱ እሳት ተጭሮ በርካታ ንጹሀን በነዲዱ መቃጠል ከጀመሩ ሁለት ዓመታት ተቆጥረዋል። በነዚህ ዓመታት ለሰላም የተዘረጉ እጆችን ሲያጥፍ የቆየው እኩይ ቡድን ከስልጣን ባሻገር ለሚያልመው ተስፋ ቢስ ዓለም የብዙሀንን ነፍስ እንደ ግብር ጭዳ ማድረጉን ቀጥሏል።

ሰላም ናፈቂው የትግራይ ህዝብ የሚሻውን እፎይታ ከተነጠቀ ወዲህ ልጆቹን ለጦርነት እንዲያዘምት ተገዷል። ስለምን ሲል የመጠየቅ መብቱን የተነፈገው ወገን በጥቂቶች ስግብግብነት ማንነቱ ተሰርቆ የችግሮች ሁሉ ሰለባ ከሆነ ጊዚያት ተቆጥረዋል።

አሁንም ካለፈው ክፋቱ የማይማረው የጥፋት ቡድን ህጻናትን ከእናቶቻቸው፣ ወንዶችን ከባሎቻቸው፣ ተማሪዎችን ከትምህርት ገበታቸው እየነጠለ በጦርነቱ እሳት መማገዱን ይዟል።

እነሆ! ባሳለፍናቸው የጦርነት ዓመታት የለመለሙ ተስፋዎቻችን ከስመዋል። ያደጉ ሰብሎቻችን ተቃጥለዋል። ከከፍታ የደረሱ፣ ትውልድን የሚቀርጹ የትምህርት ተቋሞቻችን ትቢያ አመድ ሆነዋል። ከምንም በላይ ጦርነቱ ተተኪ የሌለውን የሰው ልጆች ህይወት አጭዶብናል። በዚህ አይተኬው ትውልድ ያለጊዜው ባክኗል። ውድ አገራችንም በኢኮኖሚው ማደግ፣ መመንደግ ሲገባት በእጅጉ ከስራለች፤ ኮስምናለችም።

ይህ ሁሉ እውነታ የሰላም አለመኖር ማሳያ ነው። ሁሌም በሰላም ውስጥ ያሉ እሴቶች በክፉት ሀይሎች በተነጠቁ ጊዜ ሕይወት ያለወጉ ይመነዘራል፣ ያለመንገዱ አቅጣጫውን ይስታል። በዚህም የዓለም መሰረት ይናወጣል፣ የፍጥረት ህልውና ይናጋል።

ተደጋግሞ እንደሚነገረው ጦርነት የሰው ልጆች መቅሰፍት ነው። በጦር የተጀመረ መንገድ ኪሳራው የበዛ፣ ጨለማው የደመቀ ይሆናል። በጦርነት መልካም ውጤት አይገኝም። በጦርነት ዕቅድ ዓለም ሰምሮ፣ መልካም ህይወት ተቀምሮ አያውቅም። ጦርነት ያወድማል፣ ትውልድ ይጨርሳል፣ ታሪክን ከቅርስ፣ አገርን ከህዝብ ይነጥቃል። ሰላም ባጣ አገር የሚኖሩ ነፍሶች ዕንቅልፍን አያውቁም፣ ዘርቶ ማጨድ፣ ወልዶ መሳም፣ አስተምሮ ለወግ ይሏቸውን እውነቶችም ፈጽሞ አያልፉባቸውም።

ጦርነት በተጫረባቸው አገራት ያሉ ህዝቦች ዕጣ ፈንታቸው ሞትና ስደት ነው። ማን ከማ ጋር እንደተጋጨ በወጉ የማያወቁ ንፁሀን ጭምር የነፍስ ዋጋ ይከፍላሉ። የስደት መንገድ ይጀምራሉ። በዚህ መሀል ህጻናትና ሴቶች፣ ወጣቶችና አረጋውያን ሰው የመሆን ህልውናቸውን ያጣሉ። ባገራቸው የሚያገኙትን ክብር ተነፍገው የሰው አገር አፈር ይበላቸዋል። ታሪካቸው በበረሀው አሸዋ ይዋጣል። ስምና ዝናቸው በባህሩ ሞገድ ይሰጥማል።

አሁን አገራችንና ህዝቦቿ በሰላም እጦት እየተፈተኑ ነው። የዚህ ክፉ ጽንፍ ጭራም ከአንዳንድ ዓለም አገራት ጋር የነበረውን መልካም ዲፕሎማሲ ሳይቀር በጥቁር ጥላው ሸፍኖታል። ሰላም ወዳዱ የኢትዮጵያ ህዝብ ግን ሁሌም ለሰላም የሚዘረጋው እጁ አይታጠፍም። በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ስለሰላም አብዝቶ ይጮሀል። ድምጹን አጉልቶ ይዘምራል። ሰላም ህይወቱና የመኖር ትልሙ መሆኑን ያውቃልና ከህልሙ ተገናኝቶ፣ ከእፎይታው ለማደር ሌት ተቀን በትኩረት ይተጋል።

ከጦርነቱ ማግስት አንስቶ የሰላም አማራጮች ሲቀርቡለት የቆየው አጥፊ አሸባሪው ትህነግ ቃሉን ከእርኩሰት ቆጥሮ በሰው ልጆች ህይወት ሲቀልድ ቆይቷል። ከሰላም ይልቅ ጦርነትን ምርጫው ሲያደርግም ስለሚጠፋው ክቡር ሕይወትና ስለሚወድመው በርካታ ንብረት አንዳች ስሜት አልነበረውም። በጦርነት ዕልፍ ወገኖች ሲያልቁ፣ ቤት ጎጆ ይናዳል። የትውልድ ተስፋ መክናኖ የነገው ሕይወት ይጨልማል።

እንዲህ በሆነ ጊዜ ታሪክ ፈጥኖ ለመጥፋት፣ አገር በውድመት ለመፍረስ ትቃረባለች ። የክፉዎች ጥፍር በሰላ ቁጥር የሚቀደድ፣ የሚቦተረፈው ይበዛል፣ የሚዘረፍ የሚጠፋው ያይላል ። ይህ አጋጣሚ ዳር ሆነው ለሚያዩት ባዕዳን መግቢያ በር ከፋች ነው። ሁኔታውን የሚሹት የቅርብና የሩቅ ጠላቶችም በተፈጠረው ክፍተት ተጠቅመው የፍላጎታቸውን ለማድረስ ያመቻቸዋል። አንዱን ከአንዱ እያጋጩ በሚያገኙት ውጤትም የረጅም ጊዜ ህልማቸውን ለመፍታት ዕንቅልፍ ይሉትን አይተኙም።

ይህ እውነታ ክፉ ልቦና ካላቸው እሳቤ ጋር ሲዛመድ ትርጓሜውን ይለውጣል። ከሰላም ይልቅ ጦርነትን «ይሁነኝ» ለሚሉ ሁሉ የስልጣን ርካባቸውን ለማስፋት ፣ የአምባገነን ታሪካቸውን ለማርዘም ሰፊ ዕድል ይሰጣል። እንዲህ በሆነ ጊዜ ስልጣንን ያለወጉ የተቆናጠጡ ከርሳሞች የህዝብን ለቅሶ ለመስማት ጆሯቸው ይደፈናል። ምርጫቸው ጦርነት ብቻ ሆኖ የሰላም እጆችን ይገፋሉ። ዓለምን በአንድ የሚያስተሳስረውን ፍቅርም አጥብቀው ይረግጣሉ።

ስልጣን ወዳዱ አንጃ ቡድን እስካሁን የተሰጠውን የሰላም መንገድ ላለመቀበል ምክንያቶችን ሲደረድር ቆይቷል። በጦርነቱ በደረሰበት የመጨረሻ ኪሳራ «ሰላምን እሻለሁ ሲል ቢቆይም ወደ ህዝብ የደቀነውን አፈሙዝ «ይብቃኝ» ሲል በተግባር አላሳየም። በተማጽኖው መሀል አስብቶ የሚያርደውን ህዝብ ለአፍታ ለመታደግ ፍላጎት አልታየበትም። አንደበትና ድርጊቱ ፊትና ጀርባ ሆኖ በተቃራኒ ሲጓዝ መክረሙን ድፍን ዓለም የሚያውቀው ሀቅ ነው።

እነሆ ! ሁሌም በአንድ ቃል የምንዘምረለት የሰላም ጥያቄ ቋጠሮው ሊፈታ ጊዜው ደርሷል። ዛሬም ለሰላምና ፍቅር እጁን የማያጥፈው የኢትዮጵያ ህዝብ በደልና ግፉን ለታሪክ ትቶ የሰላም እጁን ለመዘርጋት ተዘጋጅቷል። ከጦርነት እፎይታን፤ ከስደትና መፈናቀል በአገር መኖርን፣ ከክፉት ተግባራት ይልቅ መልካም ዝማሬን የሚሻው የአገራችን ህዝብ ሁሌም ለሰላም፣ ስለሰላም ሲባል ቅድሚያውን ይሰጣል። በህዝቦች አንድነትና ሕብረ ብሄራዊነትም ፈጽሞ አይደራደርም።

አዎ ! ስለሰላም የቀረቡ እጆች ዛሬም በሰፊው ተዘርግተዋል። ይህ ዋጋ የሚከፈለው ስለኢትዮጵያና ስለሰላም ወዳዶቹ የኢትዮጵያ ህዝቦች ህልውና ሲባል ነው። ያለፈው የጦርነት ጠባሳ፣ ያደረሰው ግፍና መከራ በዋዛ ባይረሳም እኛ ግን ታሪክን ለጊዜው እውነታ እንተዋለን። እኛ ለሰላም የተዘረጉ እጆችን አናጥፍም። የሰላም ዝማሬን በለቅሶ ጩኸት አንቀይርም። ሰላም ታሪካችን ነው። ሰላም መለያችን ሆኖ ይቀጥላል።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## ኢሬቻና አዲሱ የፋሽን አልባሳት አብዮት

**ቦጋለ አበበ**

ካለፉት ሶስት ዓመታት ወዲህ በኦሮሞ ሕዝብ ዘንድ በተለይም በአዲስ አበባ በድምቀት እየተከበረ የሚገኘው የኢሬቻ በአል የፋሽን አልባሳት ዲዛይነሮችን ቀልብ በስፋት እየሳበ እንደሚገኝ ይታወቃል። በዚህም ባለፉት በርካታ ዓመታት ተዘውትረው ሲለበሱ ከማይታዩ በርካታ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች አልባሳት መካከል ውስጥ አንዱ የነበረው የኦሮሞ ባህል አልባሳት የኢትዮጵያን የፋሽን ኢንደስትሪ በስፋት እንዲቀላቀሉ አድርጓል። የአገሪቱ የፋሽን ኢንዱስትሪ አልባሳቱን በተለያየ ስልት ሸምነው በማቅረብ በርካቶች እንደየ ፍላጎቶቻቸውና እንደምርጫቸው በተለይም በኢሬቻ በአል ወቅት እንዲደምቁበት አስችለዋል።

ይህ አዲስ የኦሮሞ ባህል አልባሳት የፋሽን አብዮት ባለፉት ጥቂት ዓመታት እየተስተዋለ ቢገኝም ከሳምንት በፊት በተከበረው የኢሬቻ በአል ላይ ግን በስፋት ታይቷል። በዚሁ ክብረ በዓል ላይ በእነዚህ ባሕል አልባሳት ተውበው የሚታዩ የተለያዩ ግለሰቦች ቁጥርም በርክቶ ተስተውሏል። ለዚህም የተለያዩ የፋሽን ዲዛይነሮች ትልቅ ሚና እንደነበራቸው ማስተዋል ይቻላል።

ቀይ፣ ጥቁርና ነጭ ቀለማት ያላቸው የኦሮሞ ባህል አልባሳት ወትሮም የነበሩ ናቸው። አዲሱ ነገር እነዚህን ሶስት ቀለማት በአንድ ላይ በህብር አድርጎ በዘመናዊ መልክ ውብና ምቹ ሆነው በተለያዩ ዲዛይኖች እንዲቀርቡ መደረጉ ነው።

የ27 ዓመቷ ዲዛይነር ሴናከቤኪ ግርማ በኦሮሞ ባህል አልባሳት ላይ ያየችውን ለውጥ "ማይታመን" ስትል ለቢቢሲ አማርኛ ድረ ገጽ በሰጠችው ቃለምልልስ የሰሞኑን የፋሽን አብዮት ትገልፀዋለች። "ሰዎች የበለጠ በማንነታቸው እየኮሩ መምጣት ጀምረዋል" የምትለው ወጣት ዲዛይነር እነዚህ የባህል አልባሳትም ከበዓል ቀናት ውጪ ሰርክ የሚለበሱ



በኢሬቻ በዓል ላይ በአዳዲስ የኦሮሞ ባሕል አልባሳት ተውበው የሚታዩ ግለሰቦች ቁጥር በርክቶ ተስተውሏል፣

እንዲሆኑ ምኞቷ ተናግራለች።

በየዓመቱ በአሉ ከሚከበርባቸው ቀናት ቀደም ብሎ "የኢሬቻ ፋሽን ትርኢት እና የባህል ፌስቲቫል" እንዲሁም የሞዴሊንግ ውድድሮች በአዲስ አበባ፣ አዳማና ሌሎች ከተሞች መካሄዳቸው ዲዛይነሮች የበለጠ እንዲነቃቁና አዳዲስ የፈጠራ ውጤቶችን ይዘው ወደ ገበያ እንዲያቀርቡ ምክንያት ሆኗል። ይህም በፋሽን ገበያው ትስስር ለብዙዎች ትልቅ የስራ እድል የፈጠረ ሲሆን ኢሬቻ ለፋሽን ኢንዱስትሪው እያበረከተ የሚገኘው አስተዋጽኦ እንደሆነ ተነግሮለታል።

አልባሳቱን በማዘመን ረገድ ትልቅ ድርሻ ከነበራቸው ዲዛይነሮች የኬቲ ፋሽን ባለቤት አቶ ዘሩ ዓለማየሁ ለአዲስ ዘይቤ ሲናገሩ፣ "ኢሬቻ በአልባሳት ሽያጭ እና ዲዛይን ሥራ ላይ የሚታይ ለውጥ ስለማምጣቱ" ይጠቁማሉ። "በበዓሉ ዕለት ደምቀው ለመታየት የሚሆኗቸውን አልባሳት የሚያዙ ሰዎች ቁጥር በማሻቀቡም ትዕዛዝ መቀበል አቁመናል" ሲሉ በዚህ ፋሽን ላይ ያለውን ሰፊ የገበያ ፍላጎት ያብራራሉ።

የፋሽኑ መስፋፋት የኦሮሞን ባህል ከማስተዋወቅ ያለፈ ጥቅም እንዳለው ብዙዎች በተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎች ሃሳብ ሲለዋወጡ ነበር። በርካታ ድረ ገጾችና ማህበራዊ ሚዲያዎችም በዚህ ጉዳይ ላይ ትኩረት አድርገው የተለያዩ ዘገባዎችን አሁንም ድረስ እየሰሩ ይገኛሉ። ይህ የፋሽን አብዮት በእርግጥም ባህልን ከማስተዋወቅ ባሻገር ወጣቶች ባህላቸውን እንዲወዱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከተ እንደሚገኝ ለማንም ግልጽ ነው። የበዓሉ ሕዝባዊነት ወደሌሎች አካባቢዎችም ተስፋፍቶ ሁሉም ኢትዮጵያዊ የሚያከብረው እንዲሆንም የሚያበረክተው አስተዋጽኦም ቀላል አይደለም። ለዚህም የፋሽኖቹ ውበትና ሳቢነት ከኦሮሞ ማህበረሰብ ባለፈ የሌሎች ብሔረሰቦችንም ቀልብ እየሳበ እንደመጣ መታዘብ ይቻላል። ወደ ፊትም የዲዛይነሮች ትጋትና አዳዲስ የፈጠራ ሃሳብ ታክሎበት በአፍሪካ ብሎም በሌሎች አለማት ሰፊ ተቀባይነት የሚያገኝበት እድል እንዳለው መናገር አይከብድም።

ይህ የፋሽን አብዮት በብዙ መልኩ ያለውን ጥቅም ያህል የራሱ ጉዳት እንዳለውም ስጋታቸውን የሚገልጹ አልጠፉም። ይህም ስጋት ባህላዊ አልባሳት በአዳዲስ ዲዛይኖች በዘፈቀደ እንዲዘምኑና የቀደመ ይዘታቸውን እንዲለውጡ ከመደረጋቸው ጋር የተያያዘ ነው። በባህል ተሟጋቾች ዘንድ እንዲህ አይነት የፋሽን አብዮቶች የልዩ ልዩ ባህሎችን (አካባቢዎችን) አለባበስ መቀላቀል፣ በሽመና ወቅት የቀለም ድርድሮችን ወይም መስመሮችን ማዛባት፣ የጥራት ደረጃን ማሳነስ ወይም ከባህሉ ውጭ ያሉ ጨርቆችን መጠቀም፣ በአጊያጊያጥ ወይም አለባበስ ላይ ያለውን ባህላዊ ስርአት ሊያፋልሱ ይችላሉ የሚል ስጋት አላቸው።

በኦሮሞ ባህል ውስጥ የባሌ፣ የአርሲ፣ የቦረና፣ የጉጂ፣ የሐረርጌና የጅማ አካባቢዎች የተለያዩ የአልባሳት አይነቶች የራሳቸው መገለጫ ያላቸው አለባበሶች ሲዘምኑ የቀደመ ታሪካቸውን ባልለቀቀ መልኩ መሆን እንዳለበት ሁሉንም ያስማማል። ይህም የአንዱን አካባቢ አለባበስ ከሌላው ጋር በመደበላለቅ የባህል መዘበራረቅ እንዳይኖር በማሰብ የሚሰነዘር አስተያየት ነው።

ይህንን ስጋት ለማስቀረትም ወጣቶችን እና ዲዛይነሮችን ባህልና ወጉን ጠንቅቆ በማስተማር ፋሽኑን በአዳዲስ ጥበብ አዘምኖ ማሳደግ እንደሚቻል ይታመናል።

# ትዝብት/ ማረፊያ

## ስለ ሳይንስ ሙዚየሙ...

**አቤል ገ/ኪዳን**

በዚህ ሳምንት የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ሙዚየም ተመርቋል። ከጠቅላይ ሚኒስትሩ እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ቢሮ መሀል ላይ የተሰየመው ይሄ አዲስ ህንጻ በጣም ግዙፍ እና ውብ ነው። በእውነቱ እነዚህን ሁለት ነገሮች ማለትም ውበት እና ግዝፈትን አንድ ላይ አስተባብሮ መያዝ ቀላል አይደለምና ገንቢዎቹን ማድነቅ ተገቢ ነው። አይታችሁታል ከውጭ እንኳን እንዴት እንደሚያምር። አንድ ትልቅ የአውሮፓ ስቴድየም እኮ ነው የሚመስለው። በእውነቱ ይህን የመሰለ ውበት በአጥር እንዲከለል ባለማድረጋቸው የግንባታው ባለቤቶች ምስጋና ይገባቸዋል። አስቡት እስኪ ይህን የመሰለ ግንባታ ላይ ትልቅ የኮንክሪት ግድግዳ ገድግደውበት ሳናየው ቢቀር...በጣም አሳዛኝ ነበር የሚሆነው። አሁን ግን ግቡብኝ ግቡብኝ የሚል ተቋም ሆኗል።

ለማንኛውም ዛሬ ስለዚህ ሙዚየም አንዳንድ ነገሮች ልል እወዳለሁ። የመጀመሪያው የህንጻውን ውበት በተመለከተ ነው። አስተውላችሁ እንደሆነ የእኛ አገር ግንባታዎች ዲዛይን እና ግንባታው ጭራሽ አይመሳሰልም። አንዳንዴ እንደውም የእኛ አገር ግንባታ ከአንዳንድ ሰዎች የማህበራዊ ሚዲያ ገጽታ ጋር ይመሳሰላል። ሁላችንም እንደምናውቀው ብዙ ሰዎች በማህበራዊ ሚዲያ ላይ የሚለጥፉትን ፎቶ ከብዙ ፎቶዎቻቸው መሀከል መርጠው እና ብዙ አርትኦት አድርገውበት ነው። በዚህም የተነሳ ብዙ ሰዎች ፎቶ ላይ ሲታዩ ሞዴል ይመስላሉ። በአካል ሲታዩ ግን ፉንጋም ባይባሉ እንኳ ፎቶው ላይ ካሳዩን ገጽታቸው የተለዩ እንደሆነ እናውቃለን። ብዙ ህንጻዎቻችንም እንደዚያው ናቸው። ከግንባታው በፊት ንድፋቸውን ስናይ ውበታቸው እጅን በአፍ የሚያስጭን ነው። የህንጻው ማማር፤ የአረንጓዴ ስፍራው ልምላሜ፤ የመኪና ማቆሚያው ስፋት፤ ያለው መጸዳጃ ቤት ብዛት ምናምን ሲታይ የሚፈጥረው ጉጉት የትየለሌ ነው። ህንጻው ሲያልቅ ግን አንድ ትልቅ የኮንክሪት ክምር ይሆንና ወይ ውበት ወይ ጥቅም የሌለው አሰልቺ ነገር ይሆናል። የሳይንስ ሙዚየሙ ግን ከዚህ የተለየ ነው። አሁን ከተመረቀ በኋላ የተነሱት ፎቶዎች ራሱ ደንበኛ ዲዛይን ነው የሚመስሉት። ግዝፈቱ ውበቱን አልቀማውም። ሁለቱንም አቻችሎ የያዘ ግሩም ህንጻ ሆኖ ተጠናቅቋል። ወደፊት ደግሞ አገልግሎቱ እንደ ግንባታው ያማረ እንደሚሆን ተስፋ እናደርጋለን።

ሁለተኛው ጉዳይ ግንባታው መመረቁን አስመልክቶ የሚሰጡ አንዳንድ አስተያየቶች ጉዳይ ነው። አገሪቱ በጦርነት ተወጥራ፤ የኑሮ ውድነት ሰማይ ነክቶ፤ በአንዳንድ ቦታዎች ድርቅ እያጠቃን የሳይንስ ሙዚየም መስራት ምን ያደርግልናል የሚል ትችት በዚህም በዚያም ይሰማል። እውነት ነው አገሪቱ አሁን በታሪኳ ከተፈተነችባቸው ጊዜያት ከባዱ ላይ ነው ያለችው። ጦርነቱም፤ ረሀቡም፤ የኑሮ ውድነቱም ሌላውም አለ። ነገር ግን ይህ ስላለ ሌሎች መሰራት ያለባቸው ነገሮች መቆም አለባቸው ወይ ነው ዋናው ጥያቄ።

ዛሬ ላይ አገሪቱ በብዙ ችግሮች ውስጥም ሆና ሰዎች ትዳር እየመሰረቱ፤ ልጅ እየወለዱ፤ እየተማሩ፤ እየሰሩ፤ እየተዝናኑ ነው። ትክክል ናቸው። ምክንያቱም ጦርነት ስላለ የግል ኑሮ መቆም አይገባውምና ነው። ጦርነት ስላለ አንማርም፤ አንሰራም፤ አናገባም፤ አንወልድም፤ አንዝናናም ብንል ለሰላም መምጣት ከምንከፍለው መስዋእት ይልቅ በራሳችን ላይ የምንፈጥረው ችግር ይበልጣል። ጦርነት አለ ብሎ ስራ ያልሰራ ሰራተኛ፤ ትምህርት ያልተማረ ተማሪ፤ ሁሉንም እቅዶቹን በይደር ያቆመ ማንም ሰው የገዛ ህይወቱን ችግር ውስጥ ከትቶ ለአገርም የሚያበድረው ችግር ይኖረዋል። ስለዚህም የሚዋጋው እየተዋጋ ሌላው ስራውን መቀጠል አለበት።

በተመሳሳይም አገር ጦርነት ውስጥ ስለሆነች መንግስት ሌላ ስራውን ትቶ ጦርነቱን ብቻ ይዋጋ ወይም ረሀቡን ብቻ ይከላከል ወይም የኑሮ ውድነቱን ብቻ መላ ያበጅ ካልን ለነገ የሚተርፍ ስራ አንሰራም ማለት ነው። ይሄ ብልህት አይደለም። እርግጥ ነው ሰላም ከሁሉ ነገር ቀዳሚው ነው። የሰዎች በሕይወት የመኖር ጉዳይም ከማንኛውም ጉዳይ ይቀድማል። ነገር ግን ዛሬ ሰላም ለማስከበር ጥረን ቢሳካልን ወይም የኑሮ ውድነቱን መግታት ቢሰምርልን እንኳ ዛሬ ያልሰራናቸው የቤት ስራዎች ለነገ ሌላ ችግር ሆነው ይጠብቁናል። ስለዚህም የሳይንስ ሙዚየምም ሆነ ሌሎች ስራዎች አሁን ላይ የሚሰሩ እንጂ ለከርሞው ስራ ስንፈታ እንሰራቸዋለን ብለን የምናስቀምጣቸው ስራዎች አይደሉም።

በነገራችን ላይ ስለ ሰላም የሚያስብ ሰው ለጦርነት መዘጋጀት አለበት ይላሉ ልሂቃን።ለጦርነት ዝግጅት የሚደረገው በጦርነት ውስጥ ሆኖ ሳይሆን በሰላሙ ጊዜ ነው።ለሰላምም ዝግጅት የሚደረገው በሰላም ወቅት ሳይሆን በጦርነት ወቅት ነው። በዚህ መልኩ ነው ጦርነትን ማስቀረት እና ሰላምን ማጽናት የሚቻለው። ስለዚህም ቀጣዩ ጦርነት በየት በኩል እንደሚመጣ የሚያውቅ ሰው ከአሁኑ ለሰላም ዝግጅት ያደርጋል። የዓለም አካሄድ እንደሚያሳየው ቀጣዩ ጦርነት የሚካሄደው በቴክኖሎጂ ነው። አብዛኛው ውጊያ የሳይበር ነው። ይህን የሳይበር ውጊያ መመከት እና ራስን ማስከበር የሚቻለው ደግሞ ጦርነቱ ከተከፈተብን በኋላ አይደለም። በጦርነት ውስጥ ሆነን ተዋጊ ምልመላ እና ስልጠና አናካሂድም። አሁን ላይ ነው አገርን የሚመክት ተዋጊ የምናዘጋጀው። የሳይንስ ሙዚየሙም ቀጣዮቹን የሳይበር አርበኞች የምንመለምልበት እና የምናሰለጥንበት የከተማው ብር ሸለቆ ወይም የሳይንሱ ወታደራዊ ካምፕ ነው ልንል እንችላለን። በተመሳሳይ ረሀብንም ሆነ የኑሮ ውድነትን ወይም ሌላ አይነት ችግር መመከት የምንችለው በዋነኝነት ሳይንስን እንደ ትጥቅ በመያዝ እንጂ የእለት የእለቱን ችግር ብቻ ለመቅረፍ በመንደፋደፍ አይደለም።

ሌላኛው ስለ ሳይንስ ሙዚየም የተመቸኝ ነገር ያረፈበት ቦታ ነው። ሳይንስ ሙዚየም ብቻ ሳይሆን አብርሆት ቤተ መጻህፍት እና ወዳጅነት አደባባይ በከተማው ደላሎች ዐይን ግንባር የሆኑ ቦታዎች ናቸው ተብሎ ለዓመታት በከፍተኛ ንቃት ለሽያጭ ሲጠበቁ የነበሩ ናቸው። አድዋ ሙዚየምንም እዚያው ውስጥ ልንጨምረው እንችላለን። እነዚህ ቦታዎች ለባለሀብት ቢሸጡ ቢበዛ ሊሆኑ የሚችሉት ሆቴል ወይም የገበያ ማእከል ነው። ከዚያ ያለፈ እንደማይሆኑ የከተማው ባህል ያሳያል። ከነዚህ አንጻር የተሰራበትን ነገር ስናይ በጠቀሜታውም ይሁን በውበት ብሎም በፋይዳ በጣም የተሻለ ነው ብሎ በድፍረት መናገር ይቻላል።

በአጠቃላይ ሲታይ የሳይንስ ሙዚየሙ እንደ አገር እጅጉን የሚጠቅመን ምርጥ ነገር ነው ብለን በድፍረት እንናገራለን።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

# አፍሪካ እና መጪው ዘመን

ግርማ መንግሥቴ

እዛ ብቻ አይደለም፤ አፍሪካም አባቶች አሏት። ለዛውም የደለበ ታሪክ ያላቸው፤ ለአፍሪካ ርእይ የሰነቁ፤ ስለ አፍሪካ የወደቁ፤ ስለ አፍሪካም ሲሉ ህይወታቸውን ሳይቀር አሳልፈው የሰጡ፤ ቅኝ ገዢነትነትን አምርረው የተጠየፉና የጸረ ቅኝ አገዛዝ ትግል ያካሄዱ፤ የነጮቹን "ጨለማዋ አህጉር" ትርክትን ከስሩ ለመገልበጥ ሌት ተቀን የተጉ። አህጉሪቱ ከቅኝ ገዢዎች የግፍ አገዛዝ ነፃ እንድትወጣ በፋና ወጊነት የታገሉ፤ ችጋር፣ እረሃብ፣ በሽታ፣ ድንቁርና ... እንዲወገድ የለፉ፤ አስቀድመው የPan-Africanism ፍልስፍናን ያቀነቀኑ፤ የNegritudeን (የጥቁርን ህዝብ የተወሳሰብ የስልጣኔ፣ ባህል፣ ምጣኔ ሀብት፣ ማህበራዊ ዋጋ ያለው ሲሆን የሰብዓዊ መብት ጽንሰ ሃሳብን የያዘ ነው) ርእዮት መሰረት ያስያዙ።

በኒው ዮርክ የኢትዮጵያ አምባሳደር የነበሩት ሀዲስ አለማየሁ ያፈለቁት፣ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በኩል አልፎ በአፍሪካ መሪዎች ይሁንታን ያገኘውና በአፍሪካ የመጀመሪያው የሆነው ዓለም አቀፍ ድርጅት (የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን)ን በአዲስ አበባ የመሰረቱት (ለቅኝ ገዥዎች አልበገር ያለችውን ኢትዮጵያን ጨምሮ ላይቤሪያ፣ ጋና፣ ሞሮኮ፣ ሱዳን፣ ቱኒዚያና ግብጽ ናቸው) ይህንኑ ራእያቸውን ለማሳካት መሆኑን ማስታወስ ተገቢ ነው።

ይህ ተቋም ሲመሰረት "የአፍሪካን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ለውጥ ለማፋጠንና አንድነታቸውን ለማጎልበት በስራ ዕድል ፈጠራ፣ ቴክኖሎጂ ሽግግር፣ በሰው ኃይል ልማትና በአቅም ግንባታ ስራዎች ላይ ድጋፍ ለማድረግ ያለመ ነው" የሚለው ዋና አላማው እንደሆነም መገንዘብ ጠቃሚ ነው።

ድርጅቱ የምስረታውን 60ኛ ዓመት ሲያከብር ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን እንዳሉት፤ የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን አፍሪካዊያን በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በሰላም ጉዳዮች ውጤታማ ትብብር እንዲኖራቸው አግዟል። ... የአፍሪካ ኅብረት አጀንዳ 2063 እና የ2030 ዘላቂ የልማት ግቦች እንዲፈጸሙ የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን በፖሊሲ የተመሰረተ የፋይናንስ፣ የቴክኒክና የአቅም ግንባታ ድጋፍ እየሰጠ፤ በስራ ዕድል ፈጠራ፣ በአረንጓዴ ልማት፣ ለአፍሪካ ሰላምና የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ፣ በውጤታማ የፋይናንስና የተፈጥሮ ሐብት አስተዳደር እንዲሁም በቀጣናዊ ሰላም ማስፈን የበኩሉን አስተዋጽኦ እያደረገ ይገኛል።

የሚታወቁትን ለመጥቀስ ያህል፣ "የአፍሪካ አባት" የሚል ማህበራዊ ማእረግን የተጎናፀፉት ቀዳማዊ ኃይለሥለሴ፣ ክዋሜ ንክሩሁማ፣ ጆሞ ኬኒያታ፣ ጋርቬይ፣ የታንዛኒያው አባት ሙዋሊሙ ጁሊዬስ ኔሬሬ፣ ሴዳር ሴንጎር ... ወዘተርፈ ሁሉ የዘመናዊት አፍሪካ መስራች አባቶች ናቸው። በመሆኑም፣ ከላይና ከታች የጠቀስናቸውን አፍሪካዊ ተቋማት ትተውልን ሄደዋል።

የአጼ ኃይለሥላሴና ክዋሚ ንክሩሃማን ጨምሮ ሌሎች የአፍሪካ ታላላቅ መሪዎች ባደረጉት ታላቅ ጥረት እንደ ጎርጎሮሲያኑ አቆጣጠር ግንቦት 1963 የ32 ነጻ አገራት መሪዎች በኢትዮጵያ መዲና አዲስ አበባ ላይ በመሰብሰብ የአፍሪካን የመጀመሪያውን አህጉራዊ ተቋም ("የአፍሪካ አንድነት ድርጅት" በሚባል ይታወቅ የነበረውን ማለቴ ነው) ማቋቋማቸውና ተቋሙ አፍሪካን ይታደግ ዘንድ አላማ ይዘው መነሳታቸው በራሱ ከበቂ በላይ ማሳያ ነው። ዝርዝሩ ብዙ ነውና ወደ ጉዳያችን እንመለስ።

ምንም እንኳን፣ አህጉሪቷ በ"ተፋላሚ ወገኖች" ብራንድ ብትታወቅም፣ አንድ ቀን (በቅርቡ) ከዚህ አይነቱ አዙሪት ውስጥ ትወጣለች፣ ከተጣባት ደዌ ትላቀቃለች .... የሚለው የበርካታ አፍሪካዊያን ተስፋ ነው። እውነትም ያ ጊዜ ደግሞ አሁን ይመስላል። ከጊዜዎች ሁሉ "አሁን" ለአፍሪካ ወሳኝ ጊዜ ነው። አሁን የተደቀነባትን ዘመናዊ ቅኝ አገዛዝ ወይ መቀበል፤ አለያም አሽቀንጥሮ መጣል።

አዎ፣ ዘመናዊ ቅኝ አገዛዝ አይኑን በጨው አጥቦና አፍጥጦ፤ ጥርሱን አግጥጦና ጦሩን ሰብቆ መጥቷል። መምጣት ብቻም አይደለም የአልሞት ባይ ተጋዳይነቱን

**የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን በፖሊሲ የተመሰረተ የፋይናንስ፣ የቴክኒክና የአቅም ግንባታ ድጋፍ እየሰጠ፤ በስራ ዕድል ፈጠራ፣ በአረንጓዴ ልማት፣ ለአፍሪካ ሰላምና የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ፣ በውጤታማ የፋይናንስና የተፈጥሮ ሐብት አስተዳደር እንዲሁም በቀጣናዊ ሰላም ማስፈን የበኩሉን አስተዋጽኦ እያደረገ ይገኛል**

ከጀመረ ሰንብቷል። በ"የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ"ዬ ያልተፃፈ ሕግ አፍሪካን ሊቀራመትና መቅኔዋን ሊመጠምጥ ያለ የሌለ ኃይሉን አሰልፏል። ቢለመን፣ ቢዘከር፤ ቢገሰፅ፣ ቢገፈተር ... በፍፁም ሊገባው አልቻለምና ንክች ያባ ቢላዎ ልጅ ብሎ በር ላይ ተገትሯል። ታዲያ የዚህ መፍትሄው ምንድነው?

ከመፍትሄው በፊት፣ ዘመናዊ ቅኝ አገዛዝ አይኑን አፍጥጦ፣ ጥርሱን አግጦ ... መጥቷል ስንል ያለ ምክንያትና መረጃ ሳይሆን፤ በርካታ ምክንያቶችንና መረጃዎችን ይዘን፣ ለምሳሌ ያህልም፣ በዚህ በአንድና ሁለት ዓመት ውስጥ አሜሪካ ከ40 በላይ የሚሆኑ አገራት ላይ የኢኮኖሚ ማእቀብ መጣሏ (ኢትዮጵያም ከ"አጎዋ" መታገዷን ልብ ይሏል)፤ እንዲሁም፣ ትንሽ እንኳን ይሉኝታ በሌለው ሁኔታ አገራት ጉዳይ ላይ ጣልቃ የመግባቷ፤ ገብታም (እንደ ለመደችው ሁሉ - ሶሪያ፣ አፍጋን፣ ሊቢያ ...ን ያስታውሷል) አፈራርሳ ለመውጣት እያለከለከች መሆኗን ጠረጴዛችን ላይ በማስቀመጥ ነው።

ሰሞኑን የፈረንሳዩ መሪ በ"ፍራንስ 24" ቲቪ መስኮት ብቅ ብለው 14 የአፍሪካ አገራት ቅኝ የገዛኋችሁን ዓመታት ወጪዬ እንደ እዳ ተቆጥሮ እዳችሁን ልትከፍሉኝ ይገባል በማለት ያስተላለፉት መልእክትም እዚህ ጋር ለታሪክም ቢሆን ሊጠቀስ (ምንም እንኳን ጉዳዩ መሳቂያ መሳለቂያ ቢያደርጋቸውም፣ የአፍሪካ አካሄድ የፈጠረባቸው ከብስጭትም ያለፈ ብሽቀትን ያመላክታል) ይገባል።

የዚህ መፍትሄው ያው ሁሌም እምንደሚባለው፤ ታሪክም ልምድም እንደሚያስተምረው አንድነት ጥንካሬ ነው (Unity Is Strength)። ዩኤስ ይህንን ሁሉ ታድርግ እንጂ፣ የአሁኑ ወቅት የአፍሪካዊያን ትብብርና አንድነት፤ የዩኤስን ጫና በጋራ ለመቋቋም እያደረጉት ያለው ርብርብ ተስፋ ሰጪ ነውና አፍሪካ ወደ ዘመናዊ ቅኝ አገዛዝ ዘመን የመግባቷ ጉዳይ በመርፌ ቀዳዳ የመሹለክ ያህል ነውና እዳው ገብስ ነው።

በመሆኑም፣ አሁን ከመቸውም ግዜ በላይ የአፍሪካዊያን አንድነት ያስፈልጋል። ከምን ግዜውም በላይ ለአፍሪካዊ ችግር አፍሪካዊ መፍትሄን ማቀንቀን የግድ ይላል። ከምን ግዜውም በላይ የአህጉሪቷ መሪዎች አፍ ከልብ ሆነው ሊናገሩ፣ "አይሆንም"፤ "እምቢ" ሊሉ ይገባል። የተናጠል ጉዞ የትም አያደርስምና "በቃ" ወይንም "ኖ ሞር" ማለት ካለባቸው ጊዜው አሁን ነው። ይህ ካልሆነ፤ ይህን ካላደረጉ... "መጪው ጊዜ ለአፍሪካ ብሩህ ነው!!!" ማለት አይቻልም።

ሁሉም እንደሚመሰክረው፤ ባለፈው አመት የአሜሪካው "ዎል ስትሪት ጆትርናል" (ለምሳሌ እንኳን "U.S.-China Tech Fight Opens New Front in Ethiopia" (ሜይ 23 2021) በሚል ርእስ የወጣውን ፅሁፍ ይመለከቷል) እንደ ዘገበው ሃያላኑ የአፍሪካን ጦርነት ኢትዮጵያ ላይ እያካሄዱ ነው። (ይህንን ማብራራት የሚጠበቅ ስለማይሆን እንዝለለውና ወደ አጠቃላይ አፍሪካ እንመለስ።) እዚህ ላይ አንድ የተለመደ፣ ግን ደግሞ ወሳኝ የሆነ ጥያቄ እናንሳና ለጥያቄው ማብራሪያ እንስጥ። "ለምን?"

እንደሚታወቀው አፍሪካ ድንግል ነች። ዲያመንዱ ከአፍሪካ ነው፣ ወርቁ፣ ቡናው ....፣ ሁሉ ከአፍሪካ ነው። ታላቁ ተቃርኖ የሚሆነው ድህነቱም ያለው እዚሁ አፍሪካ የመሆኑ ጉዳይ ነው። ይህ ብቻ አይደለም፤ East African Bottling Share Company (EABSC) የሚባለው ዓለም አቀፍ የንግድ ተቋም እንኳን አፍሪካ ምን ያህል ለኮካ ኮላ ምርቶችና ግብይት አዋጪ እንደሆነች ያመለከተ ሲሆን ከአፍሪካም በተለይ ኢትዮጵያን የሚደርስባት እንደ ሌለ "Africa is an important market for Coca- Cola as it fights a campaign to increase per-capita annual consumption. Nowhere is this truer than in Ethiopia." በማለት መግለፁንም በሌላኛው ጎኑ ተፈላጊ ይሆናል።

ይህንን ሁሉ ስናይ አፍሪካ እንደ አጠቃላይ፣ በተለይም አገራችን ምን ያህል የውጭ ባለ ሀብቶችን እየሳበች እንደሆነ በግልፅ እንረዳለን። ታዲያ ቤት በኩል፣ የፖለቲካ አለመረጋጋቱ፣ የኋልዮሽ ጉዞው ... ወዘተርፈ ... በየት በኩል። እናም አፍሪካ ከዚህ መውጣት አለባት የሚለው የዚህ ፅሁፍ ምክረ ሀሳብ ሳይሆን ድሮም ሲባል፣ በመስራች አባቶችም ሲመከር ነበርና በጉዳዩ ላይ ወገብን በመቀነት አስሮ መስራት የአሁኑ ዘመን መሪዎች የመሪነት ድርሻ ይሆናል።

ግራም ነፈሰ፣ ቀኝም ነፈሰ .... አፍሪካ የድሮው አልበቃ ብሎ እንደ ገና ወደ ዘመናዊ ቅኝ አገዛዝ ጭለማ ዘመን ውስጥ መግባት አለባት ብሎ አፍሪካዊያን ፊት ቆሞ የሚናገር ተስፋ የቆረጠ ካልሆነ በስተቀር ደፋር ሰው አይገኝም። ቅኝ መገዛቱ መቀጠል አለበት ብሎ የሚከራከር ማንም አፍሪካዊ የለም። የተፈጥሮ ፀጋዋም ሆነ ሰው ሰራሽ ሀብቷ በባእድ መበዝበዝ አለበት ብሎ የሚያምንም ሰው አይኖርም። ስለዚህ ሁሉም የሚስማማበትን፣ ሰርቶ የመለወጥን ጉዳይ ማንም፣ በተለይም አመራሩ ቸል ሊለው አይገባም። ማለትም፣ የዘመናዊት አፍሪካ መስራች አባቶችን ራእይ ማስቀጠል የግድ ይሆናል ማለት ነው።

እርግጥ ነው፣ አንዳንድ የአፍሪካ ጉዳዮችን ለተከታተለ ጉዳዩ ተስፋ ሁሉ ሊያስቆርጥ ይችላል። እንኳን የዘመናዊት አፍሪካ መስራች አባቶችን ራእይ ለማስቀጠል ቀርቶ እራሷ አፍሪካም ስለ መቀጠሏ ያጠራጥራል። ይህንን ስንል ሟርት አይደለም፤ አንድም በአፍሪካዊነታችን፣ ሁለትም አፍሪካ በመፈንቅለ መንግሥት ላይ መፈንቅለ መንግሥት እሚካሄድባት ጉደኛ አህጉር ስለ መሆኗ "የአይን ምስክር" በመሆናችን ነው።

ይህ በመንግሥት ግልበጣ ላይ የመንግሥት ግልበጣ ጉዳይ የእሩቅ ታሪክ የሆነና ነገር ለማጣፈጥ እዚህ የተደነቀረ ሳይሆን፤ ሰሞኑን ቶማስ ሳንካራ ሲመራት በነበረች አገር (ቡርኪና ፋሶ) የሆነውና፤ መንግስት ገልብጦ ቁጭ ያለውን አካል ሌላ ገልባጭ መጥቶ ገልብጦት ቁጭ ማለቱ ነው። (ነገሩ አንዳንዴ የልጆች ጨዋታ ሁሉ ይመስላል፤ የዛሬ ልጆች ከዚህ የተሻለ ይጫወታሉ ካልተባለ በስተቀር። የአፍሪካ ህብረትም በሕጉ መፈንቅለ መንግስትን ይኮንን እንጂ በተግባር በፌጦ ተውጧል።)

አፍሪካ ይህ ሁሉ - ከላይ የጠቀስናቸው መልካም አጋጣሚዎችና እድሎች፣ ይህ ሁሉ ተፈላጊነትና ተመራጭነት ይኑራት እንጂ እራሷን በሯሷ ጠልፋ እየጣለች እንጂ ወደ ፊት ስትራመድ ለማየት አዳጋች እየሆነ ነው። ከእድሎቿ ፈተናዎቿ አመዝነው እዚ እሳት፣ እዛ እሳት፣ እዚም እዛም እሳት .... መሆኑ ነው እየታየ ያለው።

ዛሬ አፍሪካ ውስጥ የቱ ጋር ሰላም እንዳለ ፈልጎ ለማግኘት ያስቸግራል። በመሆኑም ከዚህ መውጣት ያስፈልጋል። ድህነትን ተረት ማድረጉ ቢከብድ እንኳን መቀነስ የግድ ይሆናል። 1.4 ቢሊዮን ላይ ያለው የህዝብ ቁጥር በ2050 2.5 ቢሊዮን መድረሱን ከወዲሁ አውቆ መስራት ብልህነት ነው። በግሉ ዘርፍ ያለው ሀብት ቀጫጫ መሆኑን ($2.1 ትሪሊየን) ተገንዝቦ ለማሳደግ መጣር ይገባል። ሙስናው፣ ሰብአዊ መብት ጥሰቱ፣ ስራ አጥነቱ (ከ42 ሚሊዮን በላይ ደርሷል)፤ መፈናቀልና ስደትን .... በአይነትም በመጠንም ከተቻለ መወገድ፣ ካልተቻለ መቀነስ አለባቸው።

ቅጥ የለሹ ፖለቲካ ሊሰለጥን ይገባዋል። እርስ በእርስ መጋደል ለ21ኛው ክ/ዘ የማይመጥን መሆኑን መገንዘብ ጠቃሚ ነው። ከ40 ሚሊዮን በላይ አፍሪካዊያን በከፋ ድህነት ውስጥ መሆናቸውን የመሪዎች ራስ ምታት ሊሆን ይገባል። እንደ አንድ አህጉር የጋራ ራእይ ያስፈልጋል። ለአጀንዳ 2063 መሳካት አፍ ከልብ ሆኖ መስራት ይጠበቃል። ቋንቋችን እንደ መስራች አባቶቻችን "እኛ አፍሪካዊያን ..." እንጂ "እኔ ..."፣ "እኔ ..." ሊሆን አይገባውም። ተቋማት እንደነ ኤዥያን (ASEAN) ሊጠነክሩ ይገባል።

ባጠቃላይ ሲታይ ተስፋ አለን። እንደገና የቀድሞው ዘመን ‹‹አፍሪካን መቀራመት›› አጀንዳ እንደሚመክን ተስፋ አለ። በተለይ ከምስራቁ ዓለም ጋር እጅ ለእጅ የመያያዙ ጉዳይ እየተባለ ባለው መሰረት ከሄደ ... ምንም ጥርጥር የለም ... አፍሪካ ተስፋ አላት። መጪው ዘመኗም ብሩህ ነው!!! ። እስከዛው ቦብ ማርሌይ Africa Unite ያለውንና ሁሉም የሚስማማበትን እኛም እንደግመዋለን - አፍሪካዊያን እንተባበር።

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# ወደራ ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበር (ዩኒየን) ምን ሰራ? ምንስ አቀደ?

**ስምስም መንግሥቱ**

በምርትና አገልግሎቶች ላይ የዋጋ ንረት ሲከሰት እና የኢኮኖሚ ጫና ሲፈጠር ሁለገብ የገበሬዎች የህብረት ሥራ ማህበራት (ዩኒየኖች) እና የሸማች ህብረት ሥራ ማህበራት በቅብብሎሽ የሚያከናውኗቸው ገበያን የማረጋጋት ሥራዎች፣ ለሸማቹ ማህበረሰብ ትልቅ የሆነ እፎይታን በመስጠት ይታወቃሉ። ማህበራቱ ወቅታዊ የኢኮኖሚ ጫና ሲፈጠር የእሳት ማጥፋት ሥራ በመሥራት ብቻ ሳይወሰኑ፣ በአገር ደረጃ ድህነትን ለማስወገድ የሚደረገውን ጥረት በማገዝ ቁልፍ ከሆኑ የልማት ኃይሎች መካከል ተጠቃሽ ናቸው። በተለይም የገበሬዎች የህብረት ሥራ ማህበራት (ዩኒየኖች) ለግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ምርታማነት የሚውሉ ማዳበሪያ፣ ምርጥ ዘርና ሌሎች ግብአቶችን ተደራሽ በማድረግ በጊዜ፣ በጉልበትና በዋጋ አርሶአደሩን ተጠቃሚ የሚያደርግ አገልግሎት በመስጠት ከፍተኛ እገዛ ያደርጋሉ። ዩኒየኖቹ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ በምግብ እህል እራስን በመቻል ከድህነት ለመውጣትና ከውጭ እርዳታ ጥገኝነት ለመላቀቅ ከረምት ከበጋ በማምረት እንደአገር የተያዘውን አቅጣጫ ከግብ ለማድረስ ሚናቸው የጎላ ነው። እንዲህ ጉልህ የሆነውን ድርሻቸውን ለመወጣት የተሻለ የገንዘብ አቅም በመያዝ፣ በሰለጠነ የሰው ኃይል በመመራት እንዲሁም በጠንካራ አደረጃጀት አቅማቸው አድጎ ከፍ ያለ አገልግሎት መስጠት ይጠበቅባቸዋል።

የተቋቋሙበትን ዓላማ ለማሳካት፣ የአባላቶቻቸውን ጥቅም በማስጠበቅ፣ በኢኮኖሚ እድገት ውስጥ ያላቸውን ድርሻ ለመወጣት ጥረት የሚያደርጉ ጠንካራ ዩኒየኖች የመኖራቸውን ያህል፣በእርሻ ሥራ ወቅት ግብአትን በወቅቱና በተመጣጣኝ ዋጋ ባለማቅረብ፣ አርሶአደሩን ተጠቃሚ የማያደርግ የምርት ግዥ መፈጸም፣ ከተልእኮአቸው ውጭ ባልተገባ የንግድ ጥቅም ውስጥ ገብተዋል የሚባሉና ተያያዥ ጉዳዮች ቅሬታና ነቀፌታ የሚቀርብባቸው ዩኒየኖች መኖራቸው አይዘነጋም። እኩል ተልእኮን የሚያሳኩ ዩኒየኖችን መፍጠር ካልተቻለ ደግሞ የሚጠበቅባቸውን አገራዊ ተልእኮ ለመወጣትም ሆነ ውጤት ማስመዝገብ አይቻልም።በጥንካሬ የሚነሱትን እንዲሁም በድክመት የሚሰጡ አስተያየቶችን መሠረት በማድረግ በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን የወደራ ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበር (ዩኒየን) ውስጥ ቀደም ሲል የዘር ብዜት ባለሙያ፣ አሁን ደግሞ የማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ ሆነው በማገልገል ላይ ከሚገኙት አቶ ታደሰ ፈቃደ ጋር ቆይታ አድርገናል።

**አዲስ ዘመን፤ በቅድሚያ ወደራ ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበር (ዩኒየን) እያከናወናቸው ሥላሰው ተግባር ቢነግሩን**

**አቶ ታደሰ፤** ዩኒየኑ ወደ 140 የሚሆኑ መሠረታዊ ማህበሮችን በአንድ ያሰባሰበ ሲሆን፣ ወደ 200ሺ የሚሆኑ አርሶ አደር አባላት ይዞ በተለያየ አገልግሎት ተደራሽ ለመሆን እየሰራ ይገኛል። ማህበሩ የእርሻ ግብአቶችን በማሰራጨት ተደራሽ ከሚያደርጋቸው ግብአቶች መካከል በግዥ ከውጭ ወደ አገር ውስጥ የሚገባውን የአፈር ማዳበሪያ በሰሜንሸዋ ዞን ውስጥ ለሚገኙ 12 ወረዳዎች ያሰራጫል። ፀረ አረም፣ ፀረ ፈንገስ፣ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችንም በአንድ ማእከል የአገልግሎት መስጫ በተመጣጣኝ ዋጋ ያቀርባል። የምርምር ውጤቶች የሆኑ ከኢትዮጵያ ግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽንና ከሌሎችም የምርምር ተቋማት የተገኙ የስንዴ፣ ጤፍ፣ ገብስና ሌሎች ሰብሎች ምርጥ ዘሮችን በማዳረስ ተልእኮውን ይወጣል። ከ ማሳ መረጣ ጀምሮ የአርሶአደሩን የግብርና ግብአቶች አጠቃቀም በተመለከተም ዩኒየኑ ባሉት ባለሙያዎች የድጋፍና ክትትል ሥራ ይሰራል።

አርሶአደሩ ጊዜን በሚወስድና አድካሚ በሆነ ሁኔታ በበሬ አርሶ በግል ኑሮውም ሆነ በአገር ኢኮኖሚ ላይ የኢኮኖሚ ለውጥ የሚያመጣ ውጤት እያስገኘ ባለመሆኑ፣ ጊዜውንና ጉልበቱን በሚቆጥብ ምርታማነቱን ለመጨመር የሚረዳውን ዘመናዊ የግብርና ዘዴ እንዲከተል ዩኒየኑ በሚያደርገው እገዛ የበሬ ጉልበትን የሚተካ የእርሻ ትራክተር አገልግሎት በማቅረብ አባላቱን ተጠቃሚ እያደረገ ይገኛል። ከማህበሩ አባላት ውጭ ላሉ የአካባቢው አርሶአደሮችም ለማቅረብም አቅሙ ስላለው ጥያቄ ለሚያቀርቡ አገልግሎቱን ይሰጣል።

የግብርናውን ሥራ ከሚያግዙ የአገልግሎት አቅርቦት ጋር በተያያዘ ማህበሩ በ2014/2015 የምርት ዘመን ካጋጠሙት ችግሮች መካከል የአፈር ማዳበሪያ እጥረት አንዱ ነበር። እጥረቱ አገራዊ ቢሆንም፣ ዩኒየኑ በተቻለው መጠን ለማዳረስ ጥረት አድርጓል።

**አዲስ ዘመን፤ እንዲህ እንደናንተ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ተቋቁመው አባላቶቻቸውንና ከማህበራቸው ውጭ ያሉትንም በማገዝ ሥራ እየሰሩ እንደሆነና ውጤታማነታቸውንም ይገልጻሉ። ነገር ግን አንዳንድ አባላቶች በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ቅሬታ ያሰማሉ።ተጠቃሚነታቸው ከሚጠብቁት በታች እንደሆነና ዩኒየኖቹ በአርሶ አደሩ ስም ይነግዳሉ ወይም ይጠቀማሉ የሚሉ ሀሳቦች በአንዳንዶች ይነሳል። በቅሬታና አስተያየቶቹ ሳይ ሀሳብዎን ቢያካፍሉን።**

**አቶ ታደሰ፤** ቅሬታና አስተያየቱ የለም ብዬ አልከራከርም። ከመሠረታዊ የህብረት ሥራ ማህበራት እስከታችኛው ተጠቃሚው አርሶአደር ድረስ የውይይት መድረኮች ተመቻችተው ሀሳቦች ይሰጣሉ። ዩኒየኑም ሀሳቡን በግብአትነት ይጠቀማል። ‹‹ዩኒየኑ አትራፊ ሆኗል።እኛንም በዋጋ እየጎዳን ነው። በአግባቡ ተደራሽ እየሆነ አይደለም›› የሚሉ ቅሬታዎች አሉ። አንዳንዶቹ ቅሬታዎች እውነታነት ያላቸው ቢሆኑም ከእውነታ ውጭም የሆኑም አሉ። እውነታነት የሌለው ቅሬታ ብለን ከምንጠቅሳቸው መካከል ለአብነት በ2014/2015 የምርት ዘመን እንደአገር የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት እጥረት በማጋጠሙ አርሶአደሩ በሚፈልገው ልክ አልደረሰውም። ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ጠይቆ ከመረዳት ይልቅ ግብአቱ ለነጋዴ እንደተሸጠ አድርጎ የመውሰድ ነገር ተፈጥሯል። ያልተጣራ ነገር ይዞ መናገር አሉባልታ ነው የሚሆነው። ማዳበሪያ አቅርቦት ላይም ቢሆን፣ የዞን ግብርና መምሪያን ጨምሮ ከተለያየ አካላት በተውጣጣ የተዋቀረ ኮሚቴ አማካኝነት ነው የስርጭት ሥራው የሚከናወነው። የዩኒየኑ ድርሻ ማዳበሪውን ማድረስ በመሆኑ ለነጋዴ ተላልፎ የሚሰጥበት እድል የለም። ሆኖም ግን በአንዳንድ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ከአሰራር ጋር በተያያዘ ክፍተቶች እንደሚኖሩ እንገነዘባለን። ክፍተቶችን ማስቀረት የሚቻለው ጥብቅ የሆነ የአሰራር ሥርአት ዘርግቶ በክትትል መሥራት ሲቻል ነው። የኛም ዩኒየን ትክክል የሆኑትንም ያልሆኑትንም ሀሳቦች በግብአትነት ወስዶ በጥብቅ የአሰራር ሥርአት ቅሬታዎችን መፍታትና አሰራሮችን መፈተሽ እንደሚገባ ይሰማኛል።

**አዲስ ዘመን፤ በመኸሩ የግብርና ሥራ በዩኒየኑ በኩል የተደረጉት ድጋፎችና የግብአት አቅርቦቶች ሳይ የነበረውን ስኬትና ተግዳሮት ያስታውሱን**

**አቶ ታደሰ፤** በመኸሩ የግብ ርና ሥራ ከግብአት አቅርቦት ጋር ተያይዞ እንደተግዳሮት ከሚ ነሳው አንዱ የአፈርማዳበሪያ አቅርቦት እጥረት ነው። ለዚህም በመፍትሄነት አስቀምጠን የተንቀሳቀስነው የግብርና ዘር ፉን ከሚመሩት በየደረጃው ካሉ ተቋማትና ባለሙያዎች እንዲሁም ከአርሶአደሩ ጋር በመሆን ማን ምን አይነት መሬት ላይ ምን ይዘራል? ትኩረት የሚያስፈልገው የትኛው የሰብል አይነት ነው? በሚል የማቻቻል ሥራ ነው የተከናወነው። ቀደም ሲል በነበረው አሰራር አንድ አርሶአደር አስር ኩንታልና ከዚያም በላይ እንደፍላጎቱ የሚያገኝበት የነበረውን አሰራር በመፈተሽና ያለውን የመሬት መጠን በመለየት እያንዳንዱ አርሶአደርም የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ካርታውን ወይንም ደብተሩን ይዞ እንዲቀርብ በማድረግ በተቻለ መጠን ፍትሐዊነትን ለማስፈን ጥረት ተደርጓል። በተለይ የኢትዮጵያ ግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን በኦሮሚያ ክልል አዳማ ላይ ካለው መጋዘን 26ሺ ኩንታል ማዳበሪያ፣ ዩሪያና ዳፕ በዩኒየኑ የማከፋፈል ሥራ ተከናውኗል።

አገር ውስጥ የማይገኙ ከውጭ አገር በግዥ የሚገቡ አንዳንድ ኬሚካሎችም በውጭ ምንዛሪ እጥረት ምክንያት የአቅርቦት ማነስ አጋጥሟል። በዚህ በኩል የነበረውንም ክፍተት ለመሙላት በተለያየ መንገድ መግዛት ያልተቻለውን ኬሚካል መተካት የሚችል ሌላ ግብአት በማካካስ እጥረቱን መፍታት ተችሏል። የአረም ማጥፊያ ኬሚካሎች የአቅርቦት እጥረትንም ለመፍታት የማረሙ ሥራ በሰው ጉልበት እንዲከናወን በማድረግ አማራጭ ተወስዷል። ዩኒየኑ በቂ የሆነ የግብርና ባለሙያ ባይኖረውም በተቻለው ሁሉ ከአርሶአደሩ ጋር እጅና ጓንት ሆኖ በመሥራት ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር የበኩሉን አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ይገኛል።

**አዲስ ዘመን፤ አርሶአደሩ በተለያየ ድጋፍ ታግዞ ምርታማነቱ ከጨመረ በኋላ ደግሞ ያመረተውን ሸጦ ኑሮውን መለወጥ ይፈልጋል።ይሁን እንጂ ለዩኒየኖች የሚያስረክብበት ዋጋ በሚ ፈልገው ልክ ዋጋ እያገኘበት አለመሆኑንና ተጠቃሚዎቹ ዩኒየኖቹ እንደሆኑ አንዳንዶች ቅሬታ ያነሳሉ። ምርቱን ለዩኒየኖች ከመሸጥ ቀጥታ ከሸማቹ ጋር መገበያየትን ምርጫው የሚያደርጉም አሉ።እዚህ ሳይስ ምን ይላሉ? ከእናንተ ዩኒየን በመነሳት ምላሽ ይስጡበት**

**አቶ ታደሰ፤** እንዲህ ያሉ አስተያየቶችም ለዩኒየናችን ደርሷል። ዩኒየኖች በርካሽ ገዝተው በውድ ዋጋ ይሸጣሉ ለሚባለው የሀገሪቱን ወቅታዊ የገበያ ሁኔታ ካለመገንዘብ የተሰጠ አስተያየት ነው ብዬ እወስዳለሁ።ገበያው የተረጋጋ አይደለም።በየጊዜው ይለዋወጣል። ከአርሶአደሩ በኪሎ በ36 ብር ስንዴ ገዝተን ቀናት ሳይቆጠር 40 ብርና ከዚያ በላይ ዋጋ ጨምሮ ይገኛል። ወቅታዊ ገበያን መሠረት አድርጎ ግብይቱ ይፈጸማል።አርሶአደሩ በሚሸጥበት ወቅት ያለው ዋጋና ከሸጠ በኋላ ባለው ዋጋ መካከል ያለው ልዩነት ነው ቅሬታ የሚያስነሳው። ዩኒየኖች የተለያዩ ወጭዎች ስላሉባቸው ይህን ታሳቢ ያደረገ ሽያጭ ነው የሚከናወነው። ነገሮችን ባለመረዳትና ባለመገንዘብ ዩኒየኖችን ትቶ እንደማንኛውም ነጋዴ ለመገበያየት የሚደረግ ጥረት መኖሩን እናውቃለን።የዩኒየኖችንና አርሶአደሮችን ግንኙነት ለመለያየት በትንሽ የትርፍ ልዩነት ሚዛን ይዘው በመሄድ የሚንቀሳቀሱ ነጋዴዎችም አሉ። ችግሩን ለመቅረፍም ከከተማ ንግድና ኢኮኖሚ ቢሮ ጋር በመሆን ነጋዴው ከተመደበለት የመገበያያ ውጭ እንዳይንቀሳቀስና ህገወጥነት እንዲቀር ዩኒየኑ ተንቀሳቅሷል። ዩኒየኖች በኃላፊነት እንደሚሰሩም መገንዘብ ያስፈልጋል። ነጋዴው ዋጋ በጨመረ ቁጥር ዩኒየኖች እርሱን ተከትለው ዋጋ አይጨምሩም። የዩኒየኖች ዓላማ ገበያው እንዳይረበሽ ማድረግ ነው። ሌላው መዘንጋት የሌለበት ማህበራት ትርፋማ ሲሆኑ አባላቶችም ተጠቃሚ የሆናሉ።የሚገኘው ትርፍ ለአባላት ይከፋፈላል። ይህን የተረዱ የዩኒየናችን አባላት አሁንም ምርቶቻቸውን ለመሰረቱት ዩኒየን በመሸጥ ማህበሩ እንዲያድግና የትርፍ ተጠቃሚ ለመሆንም የበኩላቸውን እገዛ እያደረጉ ይገኛሉ።

**አዲስ ዘመን፤ በ2014/2015 የምርት ዘመን ዩኒየኑ ከአርሶአደሩ በግዥ ምን ያህል ምርት ለመሰብሰብ አቅዷል? የምርት ዘመኑን ምርታማነትስ እንዴት ገመገማችሁት?**

**አቶ ታደሰ፤** አጠቃላይ በሰሜን ሸዋ ዞን ሊገኝ የሚችለውን የምርት መጠን ለማወቅ የሚያስችል ነገር የለንም። ያም ሆኖ ግን በግምትና ካለፉ ተሞክሮዎች በመውሰድ ነው እቅድ የሚሰራው። በ2013/2014 የምርት ዘመን 80ሺ ኩንታል የተለያየ ሰብል ለመግዛት ነበር እቅዳችን። ነገር ግን በተለያየ ምክንያት አላሳካንም። ይሁን እንጂ የነበሩ የአሰራር ክፍተቶችን በማስተካከል እንዲሁም በቅሬታ የሸሸ የማህበር አባል ካለም ችግሩን በመፈተሽ ማስተካከያዎችን በማድረግ ምርቱን ለዩኒየኑ የሚሸጠውን ለመጨመር ጥረቶች እየተደረጉ በመሆናቸው ከመኸሩ የምርት ዘመን የምንገዛውን ከፍ በማድረግ ወደ 150ሺ ኩንታል በመግዛት ለሸማቹና ለተለያዩ ተቋማት ለማቅረብ ነው ያቀድነው።

**አዲስ ዘመን፤ ዩኒየኑ አቅሙን በመገንባት አባላቱን ተጠቃሚ ለማድረግ ጥረቶቹ ምን ይመስላሉ?**


**አቶ ታደሰ፤** ዩኒየኑ ለአርሶአደሩ የሚቀርቡ ግብአቶችን የሚያከማችበት የራሱ የሆነ መጋዘን ስለሌለው ለመጋዘን ኪራይ እስከ 90ሺ ብር በማውጣት ነበር የሚያከማቸው። ወጭዎችን ለመቀነስ የተለያዩ እርምጃዎችን በመውሰድ ላይ ይገኛል። በአሁኑ ጊዜም እያንዳንዳቸው 50ሺ ኩንታል የሚይዙ ሁለት መጋዘኖችን በማስገንባት ላይ ይገኛል። ዩኒየኑ በአባል ማህበራት በኩል ለአርሶአደሩ የተለያዩ ሸቀጣሸቀጦችን በማቅረብም በጊዜና በዋጋ ተጠቃሚ እንዲሆንም በመሥራት እያገዘ ይገኛል። የእንስሳት መኖም በተመጣጣኝ ዋጋ ያቀርባል።የዱቄት ፋብሪካም አቋቁሟል።

**አዲስ ዘመን፤ ዩኒየኖች አርሶአደሩን በተለያየ መንገድ በማገዝና ተጠቃሚ እንዲሆን፣ ከዚያ ባለፈም በአገር ሳይ የዋጋ አለመረጋጋት ሲከሰት ዋጋ በማረጋጋት ትልቅ ሚና አላቸው። ከዚህ አንጻር እርስዎ የሚመሩት የወደራ ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበር (ዩኒየን) የተሳካ ሥራ ሰርቷል?**

**አቶ ታደሰ፤** በአሰራር ሥርአት፣ መሪዎች ኃላፊነታቸውን ባለመወጣት፣ የዩኒየኑ ሠራተኞች በሚፈጥሩት ክፍተት፣ አባላቱን ተጠቃሚ ለማድረግ ባሰበው ልክ ተንቀሳቅሷል የሚል እምነት የለኝም። ውስኑነቶች አሉ። እኛ በተለያየ ምክንያት ግብአቶችን ማቅረብ ባለመቻላችን የዩኒየኑ አባላት በከፍተኛ ዋጋ ከነጋዴ ገዝተው ለመጠቀም ተገደዋል። ይህ ሲባል ግን የዩኒየኖች መኖር እጅግ ጠቃሚ ነው። ከነክፍተቱም ቢሆን ጉልህ ሚና ተወጥተዋል። የወደራ ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበር (ዩኒየን) ርዕይው ሰፊ ነው። የምግብ ማቀነባበሪያ (የምግብ ኮምፕሌክስ) እንዲሁም የትራክተር መገጣጠሚያ ፋብሪካ ለማቋቋም እቅድ አለው።

**አዲስ ዘመን፤ ስለነበረን ቆይታ አመሰግናለሁ።**

**አቶ ታደሰ፤** እኔም አመሰግናለሁ።



ፎቶ- ስምስም መንግሥቱ

አቶ ታደሰ ፈቃደ፤

ማህበራዊ

# አስኳላ

# የ12ኛ ክፍል ፈተናና የዩኒቨርሲቲዎች ዝግጅት

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

አሁን አሁን ብሔራዊ ፈተናዎች ሲታሰቡ በየጊዜው ሁሉም አዕምሮ ውስጥ ብቅ ማለት የሚጀምረው የፈተና መስረቅና መኮራረጅ ጉዳይ ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞም በርካታ ተማሪዎች ተጎድተዋል። በማለፍና በመውደቅ ማለት ነው። ሳያውቅ ዩኒቨርሲቲ የገባው ከአቅሙ በላይ ትምህርት ስለሚገጥመው በጭንቀት እንዲዋዥቅ ይሆናል። አቅሙ ኖሮት ደግሞ በፈተናው መሰረቅ ምክንያት ውጤት ዝቅ ያለበት ሲቆጭ ይኖራል። ሁለቱም የተጎዱበት ይህ የፈተና ጉዳይ መሰረታዊ ችግሩ ምንድነው ከተባለ ሁለት ምክንያቶችን መጥቀስ እንችላለን። መስረቅና የእርማት ስህተት ናቸው። በዚህ ውስጥም ሁለት ነገሮች ተፈጥረዋል።

የመጀመሪያው በስርቆት ፈተናው የደረሰው ተማሪ አቅሙ ሳይኖረው በገፍ ዩኒቨርሲቲን እንዲቀላቀል መሆኑ ሲሆን፤ ሁለተኛው በገፍ የመጣው ውጤት ጎበዞቹን ተማሪዎች ከቤት ማስቀረቱ ነው። ምክንያቱም ውጤት ይሰቀልና ለእነርሱ የሚሆን ቦታ ይጠፋል። እናም የስነልቦና ስብራት ሁለቱም ላይ እንዲገጥም ያስገድዳል። ለዚህ ደግሞ ካቻምና የሆነውን ብቻ መጥቀስ በቂ ነው። ፈተናው ተሰርቋል፤ የእርማትም ስህተት ነበረበት። በዚህም ብዙዎች ዩኒቨርሲቲ የመግባት እድላቸው ከሽፏል። ከእነዚህ መካከል በአንድ ወቅት ኢንተርቪው ያደረግነው በአማራ ክልል ሰሜን ወሎ ዞን መቄት ወረዳ የፍላቂት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ ሳሙኤል ጸጋዬ አንዱ ነው።

እርሱ እንደሚለው፤ ቤተሰቦቹና መምህራኑ ብቻ ሳይሆኑ ዞኑ ጭምር ይጠብቀው ነበር። ሆኖም በፈተናው መሰረቅና በእርማት ስህተት የተነሳ ውጤቱ ሞልቶለት መግባት አልቻለም። የአስተራረም ችግሩን በተደጋጋሚ ቢገልጽም ማንም ቦታ ሊሰጠው አልፈቀደም። ይህ ነገር ደግሞ የእርሱ ብቻ ሳሆን የሌሎች ጓደኞቹም ችግር ነበር። ስለዚህም እርሱና እኩዮቹ ውጤታማ ቢሆኑም ከቤታቸው ቀርተዋል። መንግስት በእኛ ይብቃና እዚህ ላይ ልዩ ትኩረት መስጠት አለበትም ባይ ነው።

እርሱና መሰሎቹ በጦርነቱ ምክንያት ዳግም እድሉን እንዳገኙ የሚያስረዳው ተማሪው፤ አሁን በሚደረገው ፈተና በሚገባም ራሳቸውን ለማሳየት እንደሚሞክሩ ይገልጻል። ለዚህም ክረምቱን ሙሉ በመረዳዳት ውስጥ እንዳሳለፉ ያነሳል። እናም ምን ያህል ብቁ እንደሆኑ ለማሳየት ቋምጠዋል። ነገር ግን አሁንም ቢሆን አንድ ነገር ያሳስባል። ይህም የአስተራረሙ ጉዳይ ሲሆን፤ የፈተና ስርቆቱም ቢሆን ዩኒቨርሲቲ መፈተኑ ብቻ ያቆመዋል የሚል እምነት የለውም። ስለሆነም ጥብቅ ክትትል እንዲደረግበት ያስገነዝባል።

ተማሪው ያለውን የስርቆት ጉዳይ ለማስቀረት ሰሞኑን ለጋዜጠኞች በተሰጠ መግለጫ እንደተባለው ትምህርት ሚኒስቴር ትልቅ ትኩረት ሰጥቷል። አንዱ አዲስ ፕሮጀክት ነድፎ መንቀሳቀሱ ነው። ከፈተና መስጫ ቦታ ጀምሮ የተለየ እንቅስቃሴ ማድረግ ጀምሯል። በዩኒቨርሲቲዎች ፈተናው እንዲሰጥ ማድረጉ አንዱ ሲሆን፤ በዙሪያው የሚደረጉ ማንኛውም የፈተና ሒደቶችም በጥብቅ ዲሲፕሊን የሚከናወኑ እንደሆኑ ተገልጿል።

ቀደም ሲል በፈተና ወቅት በሚደረግ ጉዞ ፈተናዎች የመዘረፍ ዕድላቸው ሰፊ ነበር። አዲሱ አሰራር ግን ይህንን እንደሚያስቀር እምነት ተጥሎበታል። ምክንያቱም አብዛኞቹ ዩኒቨርሲቲዎች የሚገኙት የአየር ማረፊያ ያለባቸው በመሆኑ ፈተናዎች በአውሮፕላን ስለሚጓጓዙ የመሰረቅ አጋጣሚያቸው ይቀንሳል። በተጨማሪም የሚጎዳ ሰውም እንዳይኖር ያደርጋል። የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ እንዳሉት፤ ባለፈው ዓመት በነበረው ፈተና 13 የሚሆኑ የፌደራል ፖሊስ አባላት ሞተዋል። ስለዚህም ይህ እንዳይሆን የአሁኑ አሰራር በብዙ መንገድ ያግዛል።

አዲሱ አሰራር ፈታኞች በምንም መልኩ ከተማሪዎች ጋር እንዳይታወቁ የሚደረግበት አሰራር ተዘርግቷል። ይህ ደግሞ የእርስ በእርስ መጠቃቀም እንዳይኖር ያስችላል። ሌላው ኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች ማለትም እንደ ሞባይል፤ ታብሌትና መገናኛ መሳሪያዎች በምንም ተአምር ወደ ፈተና አካባቢ እንዳይደርሱ መደረጉ ሲሆን፤ ፈተናውን ተማሪዎች በራሳቸው ብቃት እንዲሰሩ ያስችላቸዋል። ከዚህ ጋር ተያይዞ ክልከላው ለተማሪዎች ብቻ ሳይሆን ለፈታኞችና ለሌሎች አካላትም ነው። አንድ ተማሪ ከፈተና በኋላም ቢሆን ወጥቶ ሞባይል ይዞ በቅጥር ግቢ ውስጥ ቢገኝ በምንም አይነት መልኩ ዳግም ወደ ፈተና መግባት እንደማይችልም ተወስኗል። እናም ተማሪዎች ሕይወታችሁ እንዳታበላሹ በዚህ አጋጣሚ ለመግለጽ እንወዳለን።

ሌላው እንደ ሕግ የተቀመጠው ነገር ማንኛውም ተማሪ የአንገት ሐብል፣ የጸጉር ጌጥ፣ የጆሮ ጌጥ፣ የጣት ቀለበት ከጋብቻ ቀለበት በስተቀር ይዞ መገኘት አይችልም የሚለው ነው። የጦር መሳሪያና ፎቶ አንሺ መሳሪያዎች እንዲሁም የድምጽና መሰል መቅጃዎችም ይዞ መግባትም አይቻልም። ማንኛውንም አደንዛዥ እጽ መጠቀምም ሆነ ይዞ መግባት የተከለከለ ነው። በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ በሚቆይባቸው ጊዜያት ምንም አይነት ጫጫታ ያለ ድምጽ ማሰማትም አይቻልም። ይህንን ሁሉ መመሪያ የሚያስፈጽሙት ደግሞ ወደ 8 ሺ የሚጠጉ የፌደራል ፖሊሶች እንደሆኑም ፕሮፌሰሩ ተናግረዋል።

በዘንድሮው ማለትም በ2015 ዓ.ም የሚፈተኑት ተማሪዎች በ2014 የነበሩት ሲሆኑ፤ በሁለት ዙሮች ፈተናቸውን ይወስዳሉ። የመጀመሪያውን ፈተና የሚወስዱት ማለትም ዛሬ ለፈተና የቀረቡት የማህበራዊ ሳይንስ ተፈታኞች ሲሆኑ፤ በሁለተኛ ዙር ደግሞ የሚፈተኑት የተፈጥሮ ሳይንስ ተማሪዎች ናቸው። ፈተናውን የሚወስዱበት ቀን ጥቅምት ስምንት ጀምሮ ሲሆን፤ በዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ ውስጥ ከጥቅምት አምስት ጀምሮ መግባት አለባቸው። በሁለቱም ዙር ከዘጠኝ መቶ ሺህ በላይ ተማሪዎች ይፈተናሉ። በተለያዩ ችግሮች ምክንያት የማይፈተኑ 56ሺህ ተማሪዎችም አሉ። ከወር ቆይታ በኋላ ፈተናውን እንደሚወስዱም ሚኒስትሩ አስረድተዋል።

ተፈታኞቹ እንደተለመደው ፈተናውን የሚ ወስዱት በወረቀት ሲሆን፤ ከባለፉት ዓመታት የሚለየው በዩኒቨርሲቲ የሚፈተኑ መሆናቸውና 11 ኮዶች ተሰጥተውት መፈተናቸው ነው። ይህ ደግሞ ኩረጃን ከመቀነሱም በላይ ተማሪዎች ሌሎች ጎበዝ ተማሪዎችን አስበው እንዳይገቡ ያደርጋቸዋል። በራሳቸው አቅም ሰርተው የት ላይ እንዳሉም ለመለየት ያስችላቸዋል። ለመሆኑ ይህንን አዲስ የፈተና ስርዓት ለመተግበር ዩኒቨርሲቲዎች በምን ያህል ተዘጋጅተዋል ስንልም የተወሰኑ ዩኒቨርሲቲዎች ፕሬዚዳንቶችን ማነጋገር ችለናል። በተለይም የስጋት ቀጠና ናቸው የተባሉት ልዩ ትኩረታችን ናቸው።

የጸጥታ ችግር ተማሪዎችን ሳይረብሽ በተረጋጋ መንፈስ እንዲፈተኑ ከማድረግ አንጻር ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ምንም ሳይጎልባቸው እንዲፈተኑ ከማድረግ አኳያ ምን ያህል ዝግጁ ናችሁ ካልናቸው መካከል የደብረታቦር ዩኒቨርሲቲ አንዱ ሲሆን፤ የአካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዚዳንት ዶክተር ክንዴ ገበየሁ በጉዳዩ ላይ ሀሳባቸውን አጋርተውናል። እርሳቸው እንደሚሉትም፤ ዩኒቨርስቲው በአማራ ክልል ባለው ጦርነት ከባድ ችግሮችን አሳልፏል። ሆኖም የ12ኛ ክፍል ፈተና አገርን የማዳን ጉዳይ ነውና ችግርን ተጋፍጦ መልካም ነገሮችን ለማምጣት የተቻለውን እያደረገ ነው። በቂ ዝግጅት አድርጓልም። ይህ ዝግጅቱ ብዙ መሥራትን ያስተማረው ነው። ዩኒቨርሲቲው አንዱ የመፈተኛ ተቋም ተደርጎ በመመረጡ ያሉትን ሃብቶች አብቃቅቶ መጠቀም እንዴት እንደሚቻልም ተምሮበታል። ማለትም በእከዛሬው ቆይታ 190 የሚሆነውን ክፍል ብቻ ይጠቀማል። አሁን ግን ነገሮች ሲከብዱና ከሚቀበላቸው ተማሪዎች በላይ እንዲፈትን ሲገደድ ወደ 500 የሚደርስ የመፈተኛ ክፍል ማዘጋጀት ችሏል። የጸጥታ ችግሩ ብዙ ንብረቶችን ቢያወድምበትም እነዚያን ለመተካት የተለያዩ አማራጮችን ተጠቅሟል። ለአብነት ለመፈተኛ የሚሆኑ ወንበሮችን ከመጠገን ባለፈ ከኮሌጆች ጭምር በማምጣት ለመሙላት ጥረት አድርጓል።

የደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ ዛሬ በሚጀምረው ፈተና ከ17 ሺህ በላይ ተማሪዎችን ተቀብለው ያስተናግዳል። በቀጣዩ ዙርም ከዚህ ያልተናነሰ ተማሪ ያስፈትናል። ይህ ደግሞ ለቀጣይ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ቅበላ ዩኒቨርሲቲው አቅሙን የሚያሳይበት ይላሉ የአካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዚዳንቱ ዶክተር ክንዴ ገበየሁ።

የጸጥታ ስጋቱን በተመለከተ ከከተማ አስተዳደሩና ከዞን ጋር እየሰሩ መሆኑን የሚናገሩት ምክትል ፕሬዚዳንቱ፤ እንደ ፌደራል እስከ አሁን ከ60 በላይ የፌደራል ፖሊሶች ገብተው ሥራ ጀምረዋል። ተጨማሪ የጸጥታ አካላትም ይኖራሉ። ስለሆነም ችግር ይገጥማል ተብሎ አይታሰብም። ክልሉም ቢሆን የጸጥታውን ጉዳይ በስፋት ትኩረት አድርጎ እየተንቀሳቀሰበት ነው። ከፍተኛ እስከ ፈተና ቆይታቸው ድረስ ተማሪዎች ተረጋግተው እንዲፈተኑ ያደርጋል። ማህበረሰቡ ጭምር ለዚህ የፈተና ዝግጅት የበኩሉን እንዲያደርግ ስምምነት ላይ ተደርሷል። ይህ ደግሞ መጨረሻው ባይታወቅም ጅማሮው ግን ስኬታማ ነው ለማለት ያስችላል ይላሉ።

የደንቢዶሎ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ለታ ተስፋዬ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ አካባቢው የስጋት ቀጠና ተደርጎ ቢወሰድም ከተለያዩ አካባቢዎች ወደ ዩኒቨርሲቲው ተመድበው የመጡትን 4000 ተማሪዎች እስካሁን በነበረው ጊዜ ተቀብለን ስናስተናግድ ነበር። ይህ ሁኔታ ደግሞ ዩኒቨርሲቲያችን ጸጥታና መረጋጋት ያለበት እንደሆነ አረጋግጦልናል። የቀጣዩን ስራ እንዲሰጠንም አድርጎናል። በቂ ዝግጅት ያደረግንበት ነው ብለዋል።

መደበኛ ተማሪዎቹ አሁን የትምህርት ዘመኑን ፈተና ስላጠናቀቁ መውጣት ጀምረዋል የሚሉት ዶክተር ለታ፤ ምንም ችግር ሳይደርስባቸው ወደየቤተሰባቸው እንዲሄዱ ከማድረግ አኳያ ከኮማንድ ፖስቱ ጋር በመቀናጀት የዩኒቨርሲቲውን 10 የሚሆኑ ሰርቢሶች በማዘጋጀት ጉዞ እንዲጀምሩ አድርገናል። በምትኩ የ12ኛ ክፍል ተፈታኞች የሚገቡበት ይሆናልም። ለዚህ ደግሞ በዩኒቨርሲቲው እስከዛሬ ተቀብለን የምናስተምራቸው ተማሪዎች ሰባት ሺህ ብቻ በመሆናቸው ለፈተና የተሰጡን 6500 ተማሪዎች አይከብዱንም ብለውናልም።

በመጀመሪያው ዙር 3200 ተማሪዎችን እንደሚያስተናግዱ የጠቆሙት ፕሬዚዳንቱ፤ በሁለተኛው ዙር 3300 ተማሪዎችን ያስፈትናሉ። ለዚህም በተለይ ተማሪዎች ምንም አይነት የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያ ይዘው ስለማይገቡ ችግር እንዳይገጥማቸው ከማድረግ አንጻር ዩኒቨርሲቲው ሁሉንም ነገር አሟልቶ ይጠብቃቸዋል። በተመሳሳይ መመገቢያና መሰል የተማሪዎች አገልግሎቶችን በበቂ ሁኔታ እንዲያገኙ ማድረጉንም ተናግረዋል።

ለፈተና በአንድ ክፍል ቢበዛ 30 ተማሪ እንዲፈተን ይደረጋል በሚል 250 ክፍሎችን በማዘጋጀት እየጠበቁ እንደሆነ የገለጹት ፕሬዚዳንቱ፤ በጸጥታ ጉዳይም ተማሪው ብቻ ሳይሆን ቤተሰብ ጭምር ስጋት እንዳይገጥመው ጥብቅ ክትትልና ቅንጅት እየተደረገ ነው። ለዚህ ደግሞ ከፌደራል ጭምር የመጡ ፖሊሶችና የጸጥታ አካላት አሉ። እንደ ክልልም ቦታው የስጋት ቀጠና በመሆኑ ልዩ ትኩረት ተደርጎ እየተሰራበት እንደሆነም አንስተዋል።

የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር መሃመድ ኡስማን በበኩላቸው እንዳሉት፤ ዩኒቨርሲቲው ይህ ዕድል የተሰጠው ለመጀመሪያ ጊዜ በመሆኑ ደስተኛ ነው። ተማሪዎቹን በተረጋጋና በተሻለ መንገድ እንዲፈተኑ ለማድረግም የተቻለውን ሁሉ ያደርጋል። የዝግጅት ሥራውን የጀመረው ከሁለት ወር በፊት ሲሆን፤ በተለይም በአፋር ቴሌቪዥንና ሌሎች ሚዲያዎችን በመጠቀም ተማሪዎች ተረጋግተው እንዲፈተኑ ለማድረግ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ ሲሰራ ቆይቷል።

አፋር የስጋት ቀጠና በመሆኑ ተማሪዎች ብቻ ሳይሆኑ ቤተሰብ ጭምር ይጨነቃል። ጉዞ ላይ ችግር ይገጥማቸዋልም የሚል ስጋት ያደረባቸውም አሉ። እናም ዳሎልና መሰል የጦርነት አካባቢዎች ላይ ያሉ ተፈታኝ ተማሪዎችን የክልሉ ትምህርት ቢሮ፤ የክልሉ መስተዳደርና ዩኒቨርሲቲው በመደጋገፍ ተማሪዎቹ ቀድመው ወደ ከተማው በመምጣት ለፈተናው ልዩ ዝግጅት እንዲያደርጉ እየታገዙ ነው። ዩኒቨርሲቲው ከተፈቀደለት አካልና ጊዜ ውጪ ማንም መግባት ስለማይችል በተለያዩ ኮሌጆች ውስጥ ተረጋግተው የሚፈልጉት ነገር ተሟልቶላቸው እንዲቀመጡ ተደርገዋልም ብለዋል።

ጸጥታ ችግር ያለባቸው አካባቢዎች ላይ ለፈተና የሚዘጋጁ ተማሪዎች የስነልቦና ጫና ጭምር ያጋጥማቸዋል። ስለሆነም ችግር እንዳይገጥማቸው ከማድረግ አንጻር እንደ ዩኒቨርሲቲ የሥነልቦና መምህራን በማዘጋጀት የሚያግዙበትን መንገድ አመቻችቷል የሚሉት ዶክተር መሀመድ፤ በሁለቱም ዙሮች ከስምንት ሺህ በላይ ተማሪዎችን ተቀብለው እንደሚያስፈትኑ ይናገራሉ። ለዚህም በቂ ዝግጅት መደረጉን ያነሳሉ። በተለይ አካባቢው በሙቀት የሚታወቅ በመሆኑ ከውሃ፣ ከኤሌክትሪክ ጋር የሚያጋጥሙ ችግሮች እንዳይኖሩ ከወዲሁ መዘጋጀታቸውንም ገልጸዋል። መተፋፈግ እንዳይኖርም በአንድ ክፍል ውስጥ ከ25 በላይ ተማሪዎችን ለመፈተን መወሰኑን አስረድተዋል።

የጸጥታ ጉዳይን በተመለከተ ከክልል እስከ ፌደራል ድረስ በጥብቅ ክትትልና ቅንጅት እየተሰራ መሆኑን የሚጠቁሙት ፕሬዚዳንቱ፤ አካባቢው በሦስተኛ ዙር ጭምር ጦርነት ውስጥ ያለ በመሆኑ ይህንን ትልቅ መዋዕለንዋይ የፈሰሰበትን የፈተና ጉዳይ በቀላሉ የሚያየው አይሆንም። ስለዚህም ማህበረሰቡን ጭምር በማሳተፍ የሚሰራ ይሆናል። ከወዲሁ ትልቅ ሥራ እየተከናወነም ነው። ከዚያም ባሻገር የክልሉ የጸጥታ ኃይልና የፌደራል ፖሊስም በሙሉ አቅማቸው በመስራት ላይ ናቸው። እንደውም ከጸጥታ አኳያም ሆነ በሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ ወልዲያና ሌሎች አጎራባች ከተሞች ጭምር ሄዶ በማገዝ ላይ እንደሆኑ አንስተዋል።

ይህ ፈተና ብዙ ተስፋ የተጣለበት ነው። ለተማሪውም ሆነ ለአገር አበርክቶ ያላቸውን ተማሪዎች በብቃት ለማውጣት ያለመ ነው። ስለሆነም ከእስከዛሬው በተለየ መንገድ እንዲሰራበት እንደመንግስት አቅጣጫ ወርዷል። ይህንን ደግሞ የማስፈጸም ኃላፊነቱ የሁሉም ማህበረሰብ መሆን አለበት። ጉዳዩ ለትምህርት ማህበረሰቡ ብቻም የሚተው አይደለም። በተለይም የጸጥታ ችግር ያለባቸው አካባቢዎች ላይ ሁሉም ካልተረባረበ ፈተናው የሚጠበቅበትን ውጤት ሊያመጣ አይችልም። ጠላት ደግሞ ይህንን ይፈልገዋል። እናም ለአገር ሲባል ይህንን ፈተና ተደጋግፎ በሰላም ማጠናቀቅ እንደሚያስፈልግም አስረድተዋል። እኛም ምክራቸው ተገቢ ነውና ሁላችንም ልዩ ትኩረት በመስጠት ሰላማዊ ፈተና እንዲሆን የበኩላችንን እናበርክት በማለት ተሰናበትን። ሰላም!!

ወቅታዊና ልዩ ልዩ

# ወቅታዊ

# «የአገር ህልውና እና ሉዓላዊነት፤ ከፖለቲካ ልዩነት በላይ ነው»

-አቶ እዮብ መሣፍንት
የኢዜማ አገራዊ ምክክር ኮሚቴ ሰብሳቢ

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

**ዓለምአቀፉ የሰብአዊ መብት ባለሙያዎች ኮሚሽን በቅርቡ ያወጣው €€ሪፖርት« በአብዛኛው ኢትዮጵያ ላይ ያተኮረ ክስ፣ ወቀሳ እና ጫና ስለመሆኑ ከሪፖርቱ መረዳት ይቻላል፡፡ የሰብዓዊ መብት ይመለከተናል የሚሉት ዓለም አቀፍ ተቋማት በጥቂት ሰዎች የተዘጋጀው ሪፖርት ዓላማ ምንነትና በአሸባሪው ሕወሓት እጅግ ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባቸውን አማራ እና አፋር ክልሎችን በመዘንጋት ከፍተኛ የተጎጂነቱን ድርሻ ለትግራይ ክልል የመስጠቱ ሚስጥር ምን ይሆን ስንል እንጠይቃለን፡፡**

**ዓለም አቀፍ ተቋሚት በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ ኮሚቴ አቋቁመናል የሚሉበት፣ መንግስት ርሃብን እንደጦር መሳሪያ በመጠቀም፣ ጀኖሳይድ በመፈፀምና የመሳሰሉትን በመጥቀስ የኢትዮጵያን መንግስት የሚከሱት ስውር ዓላማ ምንድን ነው፣ ወደ ትግራይ ክልል የሄደው እርዳታና መድሃኒት ለአሸባሪው ቡድን ዓላማ ማስፈፀሚያ ሲውል ብሎም ለእርዳታ የተባሉትን ነዳጅና ስንዴ በቡድኑ ሲዘረፍ ዝምታን ለምን መረጡ፣ በዲፕሎማሲውስ ረገድ ምን መሠራት አለበት ስንል የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) አገራዊ ምክክር ኮሚቴ ሰብሳቢ ከሆኑትና የሕግ ባለሙያው አቶ እዮብ መሣፍንት ጋር ቆይታ አድርገናል፡፡**

**አዲስ ዘመን፡- የሰብዓዊ መብት ይመለከተናል የሚሉ ዓለም አቀፍ ተቋማት ኢትዮጵያን በተመለከተ ያወጡትን «ሪፖርት» እንዴት አገኙት?**

**አቶ እዮብ፡-** ሪፖርቱ በተወሰነ ደረጃ ሲጠበቅ የነበረ ነው፡፡ ኮሚሽኑ እንደተቋቋመ ይታወቅ ነበር፡፡ የተቋቋመውም ለአንድ ዓመት ስለሆነ የሚጠበቅ ሥራ አለው ማለት ነው፡፡ ሆኖም ከሚጠበቀው ጊዜ ቀደም ብሎ የወጣ ነው፡፡ በውስጡ ጎልተው የሚታዩ ልዩነቶች የተካተቱበት ሪፖርት ነው፡፡ በተወሰነ ደረጃ አንድን ወገን ለመኮነን ብቻ የወጣ ሪፖርት ሆኖ አግኝቸዋለሁ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የሚጠበቅ «ሪፖርት» ነው ብለዋል፡፡ ማነው የሚጠብቀው ለምንድነው ይህን አይነት «ሪፖርት» የሚጠበቀው?**

**አቶ እዮብ፡-**የሚጠበቅ ነው ሲባል ኮሚቴ ተቋቁሞ ነበር፡፡ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ያቋቋመው ነው ለማለት የፈለኩት በመጨረሻም ጥናቱን አድርጎ ሲጨርስ ሪፖርት እንደሚያወጣ የሚጠበቅ ነው፡፡ ነገር ግን በሪፖርቱ ይህን ይላል ወይንም ሐሳቡ በግልጽ ይህ ይሆናል የሚል እሳቤ ይሆናል ማለቴ አይደለም፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በሪፖርት ላይ የተገለፁት ሚዛናዊ የሆኑ፣ በማረጋገጫ የሚገለፁና በማስረጃ የተደገፉ ብሎም ገለልተኛ ነው ብለው ያምናሉ?**

**አቶ እዮብ፡-** በጣም ችግር ያለበት ሪፖርት ሆኖ ነው ያገኘሁት፡፡ በዋናነት ጥናቱን የተካሄደበት ዘዴ አስገራሚ ነው፡፡ እራሳቸው በጥናታቸው ላይ የማያምኑት ነገር ነው፡፡ ብዙ ችግሮች ያሉበት ሪፖርት መሆኑን ያሳያል፡፡ ለአብነት በዚህ ሪፖርት ላይ የበጀት ችግር ስለነበረብን ጥናቱን ያካሄዱት ሁለት ሰዎች ናቸው ይላል፡፡ የሚገርመው ይህን ሰፊ ጊዜና ሁኔታ የሚጠይቅ ብሎም የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሚሸፍነው ጉዳይ ሁለት ግለሰቦች ያመጡለትን ሪፖርት ነው፤ እንደ ሪፖርት ያቀረበው፡፡ የበጀት ችግር ስለነበር ሁሉም ቦታ መሄድ አለመቻላቸውን ይናገራሉ፡፡ መንግስት ከልክሎናል፤ ስለዚህ በአማራ እና አፋር ክልሎች ማየት አልቻልንም ይላል፡፡

ሪፖርቱ በአማራ እና አፋር ክልሎች የደረሰውን ጉዳት በሪፖርቱ ስላልተካተተ ወይንም ስላልተፈለገ ምክንያት አድርጎ ያቀረበው የኢትዮጵያ መንግስት ስላልፈቀደልን ነው ይላሉ፡፡ ትግራይ ክልልም አልሄዱም፡፡ ግን ትግራይ ክልል ተፈፅሟል ያሉትን የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ከማውጣት አላገዳቸውም፡ ፡ ይሁንና በአማራ እና አፋር ክልል የተፈፀሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን አድበስብሰው ያልፉታል፡፡ በትግራይ ክልል ያለውን ሁኔታ ግን በስልክ መረጃ አግኝተናል፤ ቃለመጠይቅም አድርገናል ብለዋል፡፡

እውነታው በትግራይ ክልል የስልክ አገልግሎት እንደሌለ ይታወቃል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በስልክ መረጃ አገኘን ይላሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ከስደተኞች ጣቢያ ነው መረጃውን ያገኘነው ይላሉ፡፡ በዋናነትም ሱዳን ያሉትን ማዕከል አድርገው ነው፡፡ ይህ ደግሞ የሱዳን መንግስት ጭምር ያመነው የስደተኞቹ ጣቢያዎች የአሸባሪው ሕወሓት ሰራዊት መመልመያ ጣቢያዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ መረጃውን ከማን አገኙ፤ ከማንስ ጋር ቃለመጠይቅ አደረጉ የሚለው አጠያያቂ ይሆናል፡፡ ይህን የመሰሉ በርካታ ግድፈቶች አሉበት፡፡

በዚሁ ሪፖርት በጣም አስቂኝ የሆነው ደግሞ፤ በበጀት እጥረት የተነሳ በኦሮሚያ ክልል ያለውን ሁኔታ ማካተት አልቻልንም ወይም ማጥናት አልቻልንም ይላል። ነገር ግን ደግሞ በራሳቸው መንገድ ቃለ መጠይቅ አድርገናል ብለው በምዕራብ ወለጋ የሆነውን ያትታል፡፡ ስለዚህ ይህንን የመሳሰሉ የተደበላለቁ ችግሮች ያሉበት ነው፡፡ መሰል ጥናቶች ሲካሄዱ ማየት ያለብን የአጠናን ዘዴውን «ሜትዶሎጂውን» ነው፡፡ ሌላ አካል ጥናቱን በተመሳሳይ ሜትዶሎጂ ቢያካሂድ ወደ ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ እሳቤ ይደርሳል የሚል እሳቤ አለው ሳይንሳዊ አካሄዱ፡፡ ነገር ግን እነርሱ የተጠቀሙትን የጥናት ዘዴ ተጠቅሞ ሌላ አካል ጥናት ቢያካሂድ ከዚህ ሪፖርት በፍጹም የማይገናኝ እና መደምደሚያውም የማይጣጣም ይሆናል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በሁለት ሰዎች የተዘጋጀው በዚህ ሪፖርት ላይ የተገለፁት አማራ እና አፋር ክልልን በመዘንጋት ከፍተኛ የተጎጂነቱን ድርሻ ለትግራይ ክልል ይሰጣል፡፡ ለምን?**

**አቶ እዮብ፡-** ከዚህ በፊት የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽንና ሂዩማን ራይት ኮሚሽን በጋራ የተጠና ጥናት አለ፡፡ እነዚህ ሁለት ሰዎች ይህ የቤት ስራ ሲሰጣቸው ቀድሞ የተካሄደውን ጥናት እንደ መነሻ ተጠቅመው፤ ጥናቱን እንዲያካሂዱ ነው፡፡ አጥኚዎቹ ግን መጨረሻ ላይ የሚያስቀምጡት ቀደም ሲል የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽንና ሂዩማን ራይት ኮሚሽን በጋራ ያካሂዱትን ጥናት ለጊዜው ባለማግኘታችን አልተጠቀምንም ብለዋል፡፡ ይህ እንግዲህ የጥናቱን ምንነት ለመረዳት ያግዛል ማለት ነው፡፡ በጣም አስገራሚ የሚሆነው ግን ይህ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽንና ሂዩማን ራይት ኮሚሽን በጋራ የተጠናው ጥናት በኢንተርኔት ላይ የተበተነ ነው፡፡ ማንኛውም ሰው የሚያገኘው ነው፡፡

ቀደም ሲል የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽንና ሂዩማን ራይት ኮሚሽን በጋራ የተጠናው ጥናት ጥቅሙ የኢትዮጵያን ሁኔታ በአግባቡ የሚረዳ ነው፡፡ ስለ ኢትዮጵያም በደንብ የሚረዳ ተቋም ነው፤ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን፡፡ ጥናቶችን ደግሞ ወሳኝ ከሚያደርጉ ነገሮች አንዱ ‹ኮንቴክስቱ› ነው፡፡ ስለዚህን ይህን እንደ መሰረት ሳይወሰድ የሚካሄድ ጥናት በየትኛውም መስፈርት ወካይ ሊሆን አይችልም፡፡

እውነታው በአማራ እና አፋር ክልሎች የተሻለ መረጃ ማግኘት ይቻል ነበር፡፡ ይሁንና ተከለከልን ነው ያሉት፡፡ ሆኖም ማን እንደከለከላቸው እንኳን በግልፅ አልጠቀሱም። በደፈናው የኢትዮጵያ መንግስት ከልክሎናል የሚል ነው፡፡ ይሄ ታማኝነቱን ጥያቄ ውስጥ ይከተዋል ።

**አዲስ ዘመን፡- የአሸባሪው ሕወሓት ስብስብ እና የፌደራል መንግስት ያለጦርነት ስድስት ወራትን ቆይተው ነበር፡፡ ይሁንና በእነዚህ ስድስት ወራት ምንም ሪፖርት ሳይወጣና በአሁኑ ወቅት ሕወሓት ሶስተኛ ዙር ጦርነት ከፍቶ እያለ ሪፖርቱን ማውጣት ለምን አስፈለገ ?**



**አቶ እዮብ፡-** ትልቁ ነገር እሱ ነው፡፡ በእርግጥ ጦርነት ባለበት ቦታ ቀርቶ በትንሽ ሁኔታዎችም የሰብዓዊ መብት ቀውሶችና ጥሰቶች መከሰታቸው አይቀሬ ነው። ነገር ግን ይህ ሪፖርት አሁን ለምን ወጣ የሚለው አነጋጋሪ ነው። ኮሚሽኑ የተቋቋመው ለአንድ ዓመት ነው፡፡ ጥናቱን አካሄድኩ የሚለው ሰኔ እና ነሃሴ ነው። በሁለት ወር የተካሄደው ጥናት በጥድፊያ እንዲወጣ ተደረገ፡፡ ምንም ፋታ መስጠት አልተፈለገም፡፡ ታዲያ ዓመት ሳይሞላ በዚህ ጥድፊያ ማውጣት ለምን አስፈለገ የሚለው ዋነኛ አጀንዳ መሆን አለበት፡፡ አጠያያቂውም ነገር ይሄው ነው ጊዜው ጭምር።

**አዲስ ዘመን፡- ሪፖርቱ ለምን አሁን እንዲወጣ የተፈለገ ይመስልዎታል?**

**አቶ እዮብ፡-** ዓላማቸው ይህ ነው፡፡ አድሎዓዊነት ስላለ እና ሕወሓትን የሚደግፍ ስለሆነ ነው፡፡ በተቃራኒው ደግሞ የኢትዮጵያን መንግስት ለመኮነን ሆን ተብሎ የተዘጋጀና የወጣ ሪፖርት ነው፡፡ ዓላማው ይህ እንደሆነም የኢትዮጵያ መንግስት አስቀድሞ ተናግሯል። በግልጽ የታየውም ይኸው ነው፡፡ የሕወሓትን ጉዳይ በትንሹ ለመጠቃቀስ ሞክሯል፡፡ ዋነኛ አጀንዳው ግን የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊትን መኮነንና ማብጠልጠል ነው፡፡

ሪፖርቱ ሕወሓት ያላለውን ሁሉ ይጠቅሳል። ሕወሓቶች የኤርትራ ሰራዊት ዘርፏል የሚል ክስ ነበራቸው፡፡ ታዲያ ይህ የአሁኑ ሪፖርት ይህን ሁሉ ክስ አምጥቶ የሚሰጠው የኢትዮጵያ ሰራዊት ዘርፏል በሚል ነው፡፡ ሆስፒታሎችን ዘርፏል ይላል። ማውደም አይደለም፤ ይህ በጦርነት ወቅት ሊከሰት ይችል ይሆናል።ነገር ግን የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ከትግራይ ክልል የሚዘርፈው ወደየት ሊወስደው ነው? የራሱን ንብረት ለምን ይዘርፋል? የራሱንስ ንብረት ዘረፈ ይባላል ወይ ነው ጥያቄው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የአውሮፓ ህብረትና የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በየፊናቸው፣ ሰብዓዊ መብት ጥሰት ያገባናል የሚሉና ሌሎችም በተበታተነ መንገድ በኢትዮጵያ ጉዳይ ኮሚቴ እናቋቁም የሚሉበት ምክንያት ምንድን ነው?**

**አቶ እዮብ፡-** በአጭሩ ልመልስልህ! የኢትዮጵያ መንግስት ላይ ጫና ማድረግ ይፈልጋል፡፡ ጫና በመፍጠር ወደ ድርድርና ሥምምነት ካመጣን በኋላ የምዕራባውያን እና የአሜሪካ ታዛዥ ወይንም በቁጥጥራቸው ስር የሚሆን መንግስትና ውጤት እናገኛለን የሚል ነው፡፡ በተደጋጋሚ የወያኔን ነፍስ ለማዳን ጫና ተፈጥሮ ነበር፡፡ በተለይ በአሜሪካ በኩል ከአሳዋ ሥምምነት እስከመሰረዝ ተደርሷል፡፡ ይህ በይፋ የሚናገሩት ነገር እንጂ በድብቅ የሚያደርጉት ጉዳይም አለመሆኑ ይታወቃል፡፡ መሰል ማዕቀቦችም ለአሜሪካ

ተገዥነት ወይንም ለማንበርከክ ይጠቀሙበታል፡፡ ይህ ደግሞ የአሜሪካ፣ አውሮፓና እና ሌሎች አገራትም የውጭ ፖሊሲያቸው አንዱ አካል ነው። ነገር ግን ይህ ሁሉ የመጣብን በድህነታችንና በምጣኔ ሃብት ባለመዳበራችን ነው፡፡ መፍትሄው የሚሆነውም ድህነታችንን ማስወገድ የሚለው ይሆናል፡፡

ሌላው ቀርቶ እርዳታን እንደ ፖለቲካ መሳሪያ መጠቀም በየትኛው መመዘኛ አግባብ አይደለም፡፡ በዓለም አቀፍ ህግም ነውር ነው፡፡ የውጭ እርዳታ የውጭ ፖሊሲ ማስፈፀሚያ ብሎ ማሰብና መውሰድም በምንም አግባብ ከሄድን አግባብ አይደለም፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በሪፖርቱ ላይ ርሃብን እንደጦር መሳሪያ መጠቀም፣ ጀኖሳይድ በመፈፀምና የመሳሰሉትን በመጥቀስ የኢትዮጵያን መንግስት ይከሳል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት፣ ሰብዓዊ መብት ጥሰት ያገባናል የሚሉና የአውሮፓ ህብረት ጨምሮ ለአሸባሪው ሕወሓት የተላከውን የመድሃኒትና የሰብዓዊ እርዳታ መጠን አግዝፈው ሲናገሩ ነበር። ይህ እርስ በእርሱ አይጋጭም?**

**አቶ እዮብ፡-** እርዳታ እንዳይገባ ተከለከለ ከሚለው እንጀምር፡፡ ኢትዮጵያዊ አውድ በሆነ መንገድ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ በኢትዮጵያ አግባብ ዕርዳታ ሊገባ የሚችለው በሁለት መንገድ ነው፡፡ አንደኛው በአማራ ክልል በወሎ መስመር ሲሆን፤ ሁለተኛው በአፋር ክልል በኩል ነው፡፡ ሁለቱም መስመር ጦርነት አለ። ጦርነቱን የከፈተው ደግሞ ራሱ አሸባሪው ሕወሓት ነው።የሰብዓዊ እርዳታ ኮሪደር ለመክፈት እንኳን ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆነው ወያኔ ነው፡፡ እርዳታ ለማድረስ የሄዱ ተሽከርካሪዎችን ደግሞ ለተዋጊዎቹ ማጓጓዣ ሲጠቀም የነበረውም አሸባሪው ሕወሓት ራሱ ነው፡፡ ይህ ስለመሆኑ ደግሞ የተባበሩት መንግስታት ሪፖርትም በደንብ ያሳያል። የእርዳታ እህልን ለአሸባሪው ቡድን ሰብስቦ ሲወስድና ሲዘርፍ የነበረውም ራሱ አሸባሪው ሕወሓት ነው፡፡ በዚህ ጊዜም ዝምታን ነው የመረጡት፡፡

ከሳምንታት በፊትም መጋዘን ሰብሮ የእርዳታ ነዳጅ ሰርቋል ሲባል፤ የአሸባሪው ሕወሓት መልስ የነበረው ያበደርናቸውን ነዳጅ ነው መልሰን የወሰድነው ሲሉ ነበር፡፡ አሸባሪው ቡድን አፉን ሞልቶ እንዲህ ሲናገርም አስገራሚ ነው፡፡ ይህ ሁሉ ባለበት ለህዝቡ ሰብዓዊ እርዳታ ካልደረሰ ማነው ተጠያቂ መሆን ያለበት? ለዚህ ሁሉ ተጠያቂው ውግያ የጀመረው እና ጦርነቱ እንዲቆም ያልፈለገው የአሸባሪው ሕወሓት ቡድን መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ የሠላም እጅ ሲዘረጋለት አሻፈረኝ ብሎ ሠላምን ያልፈለገውና ጦርነትን የመረጠው አሸባሪው ትህነግ ነው፡፡ ይህ እየሆነ ባለበት ሁኔታ የኢትዮጵያን መንግስት መክሰስ ተገቢ አይደለም፡፡

የትግራይ ህዝብ በጣም የሚያሳዝን ምስኪን ህዝብ ነው፡፡ በአሸባሪው ሕወሓት እንደመያዣ ተደርጎ እንደ ንዋይ የተያዘ ህዝብ ነው፡፡ እርዳታ መድረስ አለበት፤ በዚህ ላይ ምንም ጥያቄ የለውም፡፡ አንድም ሰው በርሃብ መሞት የለበትም፡፡ በትግራይ ክልል ብቻ ሳይሆን በየትኛውም የኢትዮጵያ ክልል፡፡ ይሁንና ይህ እንዳይሳካ ያደረገው አካል ተጠያቂ መሆን አለበት፡፡ በእኔ እምነት ይህ እንዳይሆን ያደረገው አሸባሪው ሕወሓት ነው። ለዚህ ተጠያቂው ራሱ ሕወሓት ነው፡፡ የትግራይን ህዝብ እንደ መሸሸጊያ ያደረገው ይህ ቡድን ነው፡፡ ሪፖርቱ ይህን ሁሉ ቦታ አይሰጠውም፡፡ የራሳቸውን ፍላጎት ለማራመድ እና ዓላማቸውን ለማሳካት ብቻ የሚጠቅማቸው ላይ ነው ትኩረት የሰጡት እንጂ ሰብዓዊነት የሚለው ለሥራቸው መሳካት እንደከለላ የሚጠቀሙበት አደገኛ ስልት ነው፡፡

‹‹ሪፖርቱ›› መጋዘኖች በአሸባሪው ሕወሓት ታጣቂዎች መዘረፋቸውንም አይገልጽም፤ ስለሁኔታውም አያብራራም፡፡ አሸባሪው ሕወሓት የዘረፋቸውን እርዳታ የሚያጓጉዙ ተሽከርካሪዎችን ቁጥር አይጠቅስም፡፡ ይህን ሁሉ እንዳላየ ያልፍና ችግሮቹን ሁሉ ጠቅልሎ የኢትዮጵያ መንግስት ላይ ለመደፍደፍ ይሞክራል። በመጨረሻም ሪፖርቱ ድብቅ ዓላማውን ለማሳካት እንጂ ገለልተኛ ሆኖ የመጣ አይደለም፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በ«ሪፖርቱ» ላይ ስለጅምላ ጭፍጨፋ ለማውራት ይሞክራል፡፡ ማይካድራ እና ጭና ላይ በአሸባሪው ሕወሓት የተፈፀመውን ጅምላ ጭፍጨፋ በዝምታ ለማለፍ ሞክሯል። ይሄ በግልጽ አድሏዊነት መኖሩን አያሳይም ?**



**አቶ እዮብ፡-** ጭና ላይ የተፈፀመውን ጅምላ ጭፍጨፋ በጨረፍታ ይጠቅሳል፡፡ ይህ ሁላችንም የምናውቀው ነው፤ የዓይን እማኞች ያሉበት ሲሆን እነርሱን ለማናገር ከተፈለገ አካባቢው ድረስ በመሄድ መረጃ መውሰድ ይቻላል፡፡ በአካል ሁኔታዎችን የሚታይበትም ዕድል አለ፡፡ ይህ ሁሉ አማራጭ ባለበት በስልክ ባገኘነው ሪፖርት እየተባለ ነው የተፃፈው፡፡ በመረጃቸው መሰረትም ጭፍጨፋውን የፈፀመው መንግስት ነው ብሎ በጣም የተዛባ መረጃ እና ከእውነት የራቀ ሪፖርት ያቀርባል፡፡ ጥፋቶቹን በሙሉ ወደ ኢትዮጵያ መንግስት ያላክካል፡፡ በዚህ ላይ ስንመለከተው የሪፖርቱ ዓላማው ግልፅ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡-የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን በየጊዜው የሚያወጣቸውን ሪፖርቶችን በዋና የመረጃ ምንጭነት ወይንም ዋቢነት መጠቀም ያልፈለገው ለምንድን ነው?**

**አቶ እዮብ፡-** የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን በኢትዮጵያ ውስጥ ትንሽ የተቋም ግንባታ የታየበት ተቋም ነው፡፡ ገለልተኛ ለመሆን በጣም ጥረት እያደረገ ያለ ተቋም ነው፡፡ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች በመንግስት ጭምር የሚፈፀሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን የሚያወጣ ተቋም ነው፡፡ የዚህን ተቋም ሪፖርትና መረጃ ለመጠቀም የሄዱበት ርቀት ምንም ዓይነት አመክንዮ የላቸውም። የዚህን ተቋም ድጋፍ እና እገዛ አለመጠየቅ፣ አብሮ አለመስራት ብሎም ከዚህ በፊት የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ከተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብት ኮሚሽን ጋር በጋራ ያወጡትን እንደ ማጣቀሻ አለመጠቀም በእኔ እይታና አረዳድ ትክክል አይደለም ብዬ አምናለሁ፡፡ ዓላማውንም ለመጠራጠር ከሚያደርጉ ዋነኛ ምክንያቶችም አንዱ ይህ አካሄዳቸው ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የዚህ ሁሉ ክስና ወቀሳ ድምር ውጤት ኢትዮጵያን በመዳፋቸው ሥር በማስገባት ሉሌ የሆነ መንግስት መፍጠር ነው ብለውኛል። እውነት ምዕራባውያን ይህ ዓላማቸው ይሳካ ይሆን?**

**በአንድ ላይ ተባብረን እስከቆምን ድረስ የውጭ ጫና ሊያንበረክከን አይችልም። ድህነት እያለባቸው በውጭ ጫና ያልተንበረከኩ ብዙ አገራትን እናውቃለን። ነገር ግን ይህን ማድረግ ካልቻልን፣ አብረን መቆም ካቃተን፣ ከተለያየን፣ ሁላችንም ጠርዛችን ይዘን አገርን የምንወጥር ከሆነ ያኔ ዓላማቸው ይሳካላቸዋል**

**አቶ እዮብ፡-** ኢትዮጵያ በተደጋጋሚ የውጭ ጫናዎችን ተቋቁማ መመለስ የቻለች አገር ናት፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው በአንድነት መቆም በመቻላችን ነው፡፡ አሁንም አገር ላይ የሚመጣውን ጫና መመከት ካስፈለገ ሁላችንም በአንድነት መቆም አለብን፡፡ የፖለቲካ ልዩነቶች ሊይዙን አይገባም፡፡ የአገር ህልውና እና አገር ሉዓላዊነት ከፖለቲካ ልዩነት በላይ ነው፡፡ ስለዚህ በአንድ ላይ ተባብረን እስከቆምን ድረስ የውጭ ጫና ሊያንበረክከን አይችልም፡፡ ድህነት እያለባቸው በውጭ ጫና ያልተንበረከኩ ብዙ አገራትን እናውቃለን፡፡ ነገር ግን ይህን ማድረግ ካልቻልን፣ አብረን መቆም ካቃተን፣ ከተለያየን፣ ሁላችንም ጠርዛችን ይዘን አገርን የምንወጥር ከሆነ ያኔ ዓላማቸው ይሳካላቸዋል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የምዕራባውያን ክስ፣ ወቀሳና ጫና ለመቋቋም በዲፕሎማሲው ረገድ ምን መሠራት አለብን?**

**አቶ እዮብ፡-**ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት በዲፕሎማሲ ላይ ያላት ሁኔታ በጣም ደካማ ናት፡፡ በታሪካችን በዓለም አቀፍ ዲፕሎማሲ ደካማ የሆንበት ወቅት ቢኖር አሁን ነው፡፡ ይህ የራሱ አውድና ምክንያቶች አሉት፡፡ ቀደም ሲል ዲፕሎማቶቻችን የሚሾሙበት መንገድ፣ የሚሰጣቸው ተልዕኮ ትልቅ ትኩረትን የሚስብ ነው። ዋና ዋና በሚባሉ አገራት የሚሾሙ ዲፕሎማቶችን እናውቃለን፡፡ ዋነኛ ዓላማቸው ለክልላቸው ኢንቨስትመንት ለመሳብና ለግል ጥቅማቸው ለማሳደድ ነው፡፡

ብዙ ቦታዎች ላይ ዲፕሎማቶች ሲሾሙ ከማዕከሉ ፖለቲካ ገሸሽ ለማድረግ ሲፈለግ የሰዎች መጣያ ቦታ ነበር። አሁንም እንደዚያው ነው ብዙ የተሻሻለ ነገር የለም።ዲፕሎማቶች አሁንም ለህክምና እና ጡረታ የሚላኩበት ቦታ ሆኗል፡፡ በዚህ ምክንያት በጣም ደካማ የዲፕሎማሲ ጊዜ ላይ ነው ያለነው፡፡ ስትራቴጂ ያለው አይመስልም፡፡ እዚህም እዚያም መዝለል ነው የሚመስለው፡፡

ብቸኛው ውጤት እያመጣልን ያለው የዜጎች ዲፕሎማሲ ነው፡፡ በተለያዩ አገራት የሚገኙ ዜጎቻችን አገራቸውን ወክለው የሚያደርጓቸው ተፅዕኖዎች እና ጫናዎች ለኢትዮጵያ የተሻለ ነገር እየሰሩ ነው፡፡ በማህራዊ ሚዲያውም እያገዙን ነው፡፡

‹‹የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴራችን አሁንም ድክመቶች አሉበት፡፡ ለጥቅም ማሳደጃ እየተጠቀሙበት ነው የሚል እምነት›› አለኝ፡፡ ይህን ለማስተካከል ዲፕሎማሲያችንን ከፖለቲካው አውጥተን በሞያ የሚመራ ተቋም ማድረግ መቻል አለብን፡፡ ይህ እስካልሆነ ድረስ በዜጎች ላይ የሚመሰረት ዲፕሎማሲ ጊዜያዊና ወቅትን ጠብቆ የሚነሳ እሳት ማጥፊያ ነው የሚሆነው፡፡ ጫና ሲኖር ጫናውን ለመመከት የሚደረግ እንጂ ዘላቂ የዲፕሎማሲ ሥራ ለመሥራት አይሆንም፡፡ በመሆኑም ዲፕሎማሲው በባለሙያዎች እንጂ የእኔ በሚባሉና ለጡረታ በሚላኩ ሠዎች መመራት የለበትም፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ከዝግጅት ክፍላችን ጋር ስለነበረው ቆይታ እያመሰገንኩ የሚጨምሩት ሐሳብ ካለ ዕድሉን ልስጦት - አቶ እዮብ፡፡**

**አቶ እዮብ፡-** በእኔ እምነት አሁን ከአሸባሪው ሕወሓት ጋር የገባንበት ጦርነት ማስወገድ የማይቻል ጦርነት ነው፡፡ ወያኔን ከጫንቃችን ላይ ለማውረድ በሠላማዊ መንገድ እጁን አጣጥፎ ይቀመጣል ብለን መጠበቅ አልነበረብንም፡፡ ለዚህም መዘጋጀት ነበረብን። ይህ ባለመሆኑ ብዙ ነገሮችን አጥተናል፡፡ እንደ አገር አሁንም ሕወሓት የጀመረውን ሶስተኛውን ዙር ጦርነት መከላከል ላይ ነው፡፡ አሁን ጦርነቱ በተራዘመ ቁጥር የውጭ ጫናዎች እየበረቱ ይመጣሉ፡፡ በተራዘመ ጦርነት ላይ ሰራዊቱ የመሰላቸት ባህሪ ሊያሳይ ይችላል፡፡

ደርግን የሚያክልና በጣም ትልቅ ሰራዊት ገንብቶ የነበረ መንግስት የተሸነፈው ለ17 ዓመታት በጦርነት ላይ በመቆየቱና በመሰላቸቱ ነው፡፡ ስለዚህ አሁን ያለፈው ሁኔታ ሳይመጣ በጣም ባጠረ ጊዜ አሸባሪው ሕወሓት ለአገራችን ሥጋት የማይሆንበት ደረጃ ላይ ማድረስ አለብን ብዬ አምናለሁ፡፡ በዚህ ረገድ እንደ የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ ኢዜማ ፓርቲም ከአገር መከላከያ ሰራዊት ጎን መሆናችን ማረጋገጥ እፈልጋለሁ፤ አመሰግናለሁ፡፡

# ዓለም አቀፍ

## በከባድ ፍንዳታ ተጎድቶ የነበረው የክሬሚያ ድልድይ በከፊል መከፈቱ ተገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**


ከሩሲያ ወደ ክሬሚያ የሚወስደው ብቸኛ ድልድይ

አዲስ አበባ፡- በከባድ ፍንዳታ የወደመው እና ከሩሲያ ወደ ክሬሚያ የሚወስደው ብቸኛ ድልድይ ከሰዓታት በኋላ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው መኪኖችን ማስተናገድ ጀምሯል።

በአውሮፓ ረዥሙ ድልድይ ላይ በደረሰው ፍንዳታ የሦስት ሰዎች ሕይወት ማለፉን መርማሪዎች ተናግረዋል። ድልድዩ እአአ በ2014 ሩሲያ ከዩክሬን ባሕረ ገብ መሬቱን የመውሰዱን ምልክት ተደርጎ ይታያል።

ተጎጂዎቹ በአቅራቢያው ባለ መኪና ውስጥ እያሉ ሌላ መኪና መፈንዳቱን ነው የሩሲያ ባለሥልጣናት የተናገሩት።

የነዳጅ ታንከሮች የተቃጠሉበት የድልድዩ የባቡር ሐዲድ ክፍልም እንደ ገና ተከፍቷል። የሩስያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቅዳሜ ምሽት ላይ ባሰራጨው ቪዲዮ መኪኖች ድልድዩን ሲጠቀሙ አሳይቷል።

በ2018 የተከፈተው ድልድይ እና የባቡር ሃዲድ ሩሲያ ለዩክሬን ጦርነት የምትጠቀምበትን ሎጂስቲክ የምታገኝበት ቁልፍ መስመር ነው። የዩክሬን ፕሬዚዳንት ቮሎዲሚር ዜለንስኪ አማካሪ ማይካሂሎ ፖዶሊያክ የዩክሬን ኃላፊነት በቀጥታ ባይቀበሉም "ክሪሚያ፣ ድልድይ፣ መጀመሪያው" የሚሉ ቃላትን አስፍረዋል።

"ሕገ ወጥ ነገር ሁሉ መወገድ አለበት። የተሰረቀው ነገር ሁሉ ወደ ዩክሬን መመለስ አለበት። በሩሲያ የተያዘው ነገር ሁሉ መባረር አለበት" ብለዋል። የዩክሬን መከላከያ ሚኒስቴር የድልድዩን ፍንዳታ በሚያዝያ ወር ከሰጠመችው የሩስያዋ ሞስኮቫ የሚሳኤል መርከብ ጋር አነጻጽረዋታል።

"በዩክሬን ክሬሚያ ውስጥ የነበሩ ሁለት ታዋቂ የሩሲያ የታላቅነት ምልክቶች ወድመዋል። በቀጣይስ ምን አለ?" ሲሉ በትዊተር ገጻቸው ላይ አስፍረዋል። የዩክሬን መንግሥት በትዊተር ገጹ "ተቃጥሏል" ብሎ አስፍሯል።

በፕሬዚዳንት ፑቲን የተከፈተውን ድልድይ በእሳት ሲቃጠል ማየት ያለውን ጠቀሜታ እና ምሳሌያዊነት ማጋነን ከባድ ነው። ክሬምሊን ድልድዩን ተጠቅማ ወታደራዊ መሣሪያዎችን፣ ጥይቶችን እና ወታደሮችን ከሩሲያ ወደ ደቡብ ዩክሬን የጦር አውድማዎች ታዘምታለች።

የዩክሬን ባለሥልጣናት ባህረ ሰላጤውን መልሰው ለመውሰድ ቃል ስለገቡ ይህ ትክክለኛ ዒላማ ነው ብለዋል። ከፍተኛ የሩስያ ጦር ባለባት በክሬሚያ ላይ የሚደርስ ማንኛውም ጥቃት ለክሬምሊን ሌላ ትልቅ ውርደት ተደርጎ ይታያል።

በተለይም በዩክሬናውያን ድልድዩ ይጠላል። የሩሲያው ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን 70ኛ ዓመት የልደት በዓላቸውን ባከበሩበት ቀን ድልድዩ በእሳት መያያዙን በማየታቸው በዩክሬን ያሉ የማህበራዊ ድርአምባዎች ተጠቃሚዎች በደስታ ተሞልተው ነበር ።

በክሬሚያ የሚገኙ ባለሥልጣናት በከፊል የተከፈተውን ድልድይ መጠቀም ለማይችሉ ከባድ ተሽከርካሪዎች መሸጋገሪያ መርከቦችን አዘጋጅተዋል።

የሩሲያ ብሄራዊ የፀረ-ሽብርተኝነት ኮሚቴ "ዛሬ በታማን ባሕረ ገብ መሬት ላይ በሚገኘው የክሬሚያ ድልድይ አውራ ጎዳና ላይ በሚገኝ የጭነት መኪና ላይ ፍንዳታ ተፈጽሟል። ወደ ክሬሚያ ባሕረ ገብ መሬት ይሄድ የነበረውን ባቡር ሰባት የነዳጅ ጋኖች በእሳት ጋይተዋል" ብሏል። "የድልድዩ ሁለት አውራ ጎዳናዎችም በከፊል ወድመዋል።"

የክሬሚያ ፓርላማ አፈ-ጉባኤ ቭላድሚር ኮንስታንቲኖቭ ፍንዳታውን "የዩክሬን አጥፊዎች በመጨረሻም ደም የተቀባ እጃቸውን ወደ ክሬሚያ ድልድይ ለማድረስ ችለዋል" ሲሉ ወቅሰዋል።

የሩስያው ፕሬዝዳንት ቭላድሚር ፑቲን በድልድዩ ስለደረሰው "ድንገተኛ አደጋ" ገለጻ የተደረገላቸው ሲሆን ምርመራ እንዲደረግ ትዕዛዝ ሰጥተዋል ሲሉ የክሬምሊን ቃል አቀባይ ዲሚትሪ ፔስኮቭ ተናግረዋል። ምርመራም በመካሄድ ላይ ነው።

2.7 ቢሊየን ፓውንድ የፈጀው 19 ኪሎ ሜትር የሚረዝም ድልድይ የተከፈተው ሞስኮ ክሬሚያን በሕገ-ወጥ መንገድ ወደ ራሷ ከቀላቀለች ከአራት ዓመታት በኋላ ነው።

በሩሲያ መገናኛ ብዙሃን "የክፍለ ዘመኑ ግንባታ" ተብሎ ተወድሷል። የሩሲያ ባለሥልጣናት ቀደም ሲል ከአየር፣ ከመሬት ወይም ከውሃ ላይ ጥቃቶች ስጋት በደንብ የተጠበቀ ነው ብለው ነበር።

ድልድዩ ከዩክሬን ከወሰደው ግዛት ከ100 ማይል በላይ ይርቃል። አንድ የፍንዳታ ባለሙያ ለቢቢሲ እንደተናገሩት እሳቱ የተነሳው በሚሳኤል ምክንያት አይደለም። "በመንገድ ላይ ግልጽ የሆነ ፍንዳታ /የመበታተን ጉዳት አለመኖሩ ከአየር የተተኮሰ መሳሪያ ጥቅም ላይ እንዳልዋለ ያሳያል" ብለዋል። "በጥሩ ሁኔታ የታቀደ ጥቃት መንስኤ ሊሆን ይችላል" ሲሉም ተናግረዋል።

"በመኪና ድልድዩ እና በባቡር መስመር ላይ ፈንጂዎች በሬድዮ ትዕዛዝ በአንድ ጊዜ ጥቅም ላይ ውለዋል ብዬ እጠራጠራለሁ" ሲሉ አክለዋል።

ኪዬቭ በዚህ ግጭት ጥሩ መነሳሳት ላይ ትገኛለች። ሠራዊቱ ሰፊ ቦታዎችን ያስመለሰ ሲሆን የሩሲያ ወታደሮች ለረዥም ጊዜ ከያዟቸው ቦታዎች ጭምር እየለቀቁ ነው።

ሞስኮ የተመሰቃቀለ ወታደራዊ ቅስቀሳ ጀምራለች። ይህም ሩሲያ ውስጥ ያልተለመደ የፀረ-ጦርነት ተቃውሞዎችን ሲያስነሳ በወታደራዊ ዕድሜ ክልል ያሉ ወንዶች ሀገር ለቀው እንዲወጡ አድርጓል።

በሩሲያ የቴሌቪዥን አቅራቢዎች እና እንግዶች ስለ ሁኔታው ጥፋት እና ጨለማው እየጨመረ ስለመሆኑ እየተናገሩ ነው ።

ጥቃቱ በዩክሬን ከተፈፀመ ክሬሚያን ዒላማ ያደረገችበት የመጀመሪያ ጥቃቷ አይሆንም።

ባለፈው ወር በሩሲያ ሳኪ የጦር ሰፈር ላይ የደረሰውን ጥቃት ጨምሮ ዩክሬን በክሬሚያ በተከታታይ ለተፈጸሙ የአየር ጥቃት ኃላፊነቱን ወስዳለች።

**ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር**
**በየሳምንቱ ሰኞና ዓርብ የሚታተም**

## በአራት ክልሎች የሚገነቡት 16ቱ ትምህርት ቤቶች

**እየሩስ ተስፋዬ**



ባለፉት ሁለት ዓመታት በጦርነት እና በግጭት ምክንያት በአፋር፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በኦሮሚያ እና በደቡብ ክልሎች ከአንድ ሺህ ሦስት መቶ በላይ ትምህርት ቤቶች ሙሉ በሙሉ መውደማቸው ይታወቃል፡፡ እነዚህን ትምህርት ቤቶችንም የኢትዮጵያ አርክቴክት ማህበር ባዘጋጀው አዲስ የኢትዮጵያ ትምህርት ቤት ዲዛይን ለመገንባት በትምህርት ሚኒስቴር በኩል የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ፡፡ በያዝነው ዓመት ለመገንባት ከታቀዱት 200 ትምህርት ቤቶች የስድስቱ የመሠረት ድንጋይ የተቀመጠ ሲሆን፤ በኢትዮጵያ ዲያስፖራ ትረስት ፈንድ እና በሰዎች ለሰዎች ድርጅት ባደረጉት ድጋፍ ግንባታቸው ተጀምሯል፡፡

የሰዎች ለሰዎች ድርጅት ድጋፉን አጠናክሮ የቀጠለ ሲሆን፤ ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበርም በሦስት መቶ ሚሊዮን አራት መቶ ሺ ብር ወጪ በመመደብ በአራት ክልሎች ላይ 16 ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን ትምህርት ቤቶችን ለመገንባት ከስምምነት ላይ ተደርሷል። ስምምነቱም በትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ እና በሰዎች ለሰዎች ድርጅት ሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ በዶክተር ሰባስትያን ብራንዲስ ተፈራርመዋል፡፡

ከአንደኛ ደረጃ እስከ መካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ድረስ 16 ትምህርት ቤቶች የሚገነቡትም በአፋር፣ በሶማሌ፣ በአማራ እና በኦሮሚያ ክልሎች ሲሆን፤ በዓመት በአማካይ ስምንት ሺ የሚጠጉ ተማሪዎች የትምህርት ዕድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያርጋቸዋል ተብሏል። የግንባታ ሥራው በኦሮሚያ እና በሶማሊያ ክልሎች የአዳዲስ ትምህርት ቤቶች መገንባት ያካተተ ሲሆን፤ በአፋር እና በአማራ ክልሎች ግን ኣዳዲስ ከሚሠሩ ትምህርት ቤቶች በተጨማሪ በጦርነት የተጎዱ የትምህርት ብሎኮችን በአዲስ የመተካት ሥራንም እንደሚያካትት በፊርማ ሥነ ሥርዓቱ ላይ ተመላክቷል፡፡

የሰዎች ለሰዎች ድርጅት ሥራ አመራር ቦድር ሰብሳቢ ዶክተር ሰባስቲያን ብራንዲስ በፊርማ ሥነ ሥርዓቱ ላይ እንደተናገሩት፤ ሰዎች ለሰዎች ድርጅት የሚገነባቸው ትምህርት ቤቶች አብዛኛዎቹ የግንባታ ግብዓታቸው ከአውሮፓ የሚገቡ እና ከፍተኛ ጥራት ያላቸው ናቸው፡፡ በዚህ ዓመት ግንባታቸው የሚጀመረው 16ቱም ትምህርት ቤቶች በአማካይ ከሃምሳ እስከ ሰባ ዓመት እንዲያገለግሉ ታስበው የሚሠሩ ሲሆን ግንባታቸው በያዝነው ዓመት ተጠናቆ ለአግልግሎት የሚበቁ መሆናቸውን ይገልጻሉ፡፡

ድርጅቱ እስካሁን በኢትዮጵያ በሁሉም ክልሎች አስቸጋሪ የሚባሉ ቦታዎችን ጨምሮ አራት መቶ 64 አንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን እና ሰባት ቴክኒክ እና ሞያ ማሰልጠኛ ተቋማትን መገንባቱን የጠቆሙት ዶክተር ብራንዲንስ፤ እነዚህን ትምህርት ቤቶች በአማካይ በየዓመቱ እስከ ግማሽ ሚሊዮን የሚገመቱ ተማሪዎችን በማገልገል ላይ መሆናቸውንም ያስረዳሉ። ይህ አይነቱ ድጋፍ ቀጣይነት እንዳለው በመግለጽም ሁሉም በሚችለው መንገድ ድጋፉን እንዲያደርግም ጥሪያቸውን አቅርበዋል፡፡

የትምህርት ሚኒስትር ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ በበኩላቸው፤ የወደሙ ትምህርት ቤቶችን የመገንባቱ ሥራ የሁሉንም ማሕበረሰብ ትብብር የሚጠይቅ መሆኑን ጠቁመው፤ የሚገነቡት ትምህርት ቤቶችም በአዲስ ዲዛይን እና ጥራታቸውን በጠበቀ መልኩ እንሚገነቡም ይገልጻሉ፡፡ የሰዎች ለሰዎች ድርጅት እንዲህ ዓይነቱ ድጋፍ ሲያርግ የመጀመሪያው እንዳልሆነ በመግለጽም ላደረጉት ትብብር እና ቀጣይ ለሚያደርጉት ትብብርም ምስጋናቸውን አቅርበዋል፡፡

ፕሮፌሰር ብርሃኑ እንደገለጹት ከሆነም፤ የ12ተኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ሲጠናቀቀም ሚኒስትሩ ትኩረቱን ትምህርት ቤቶች የመገንባቱ ሥራ ላይ ያደርጋል። እንዲሁም ትምህርት ቤቶችን ለመገንባትም በአገር ውስጥ እና ውጭ የሚኖሩ ባለሃብቶች እንዲሁም ትውልደ ኢትዮጵውያን በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተቀመጡ የተለያዩ የእገዛ አማራጮችን በመጠቀም አስተዋጽኦ ማድረግ ይችላሉ፡፡

የሰዎች ለሰዎች ድርጅት አምባሳደር ሻለቃ አትሌት ኃይሌ ገብረ ሥላሴ በስምምነቱ ወቅት እንዳለው፤ ከሰዎች ለሰዎች ድርጅት ጋር መሥራት ከጀመረ ቆየት ብሏል፡፡ ድርጅቱም በአገር ውስጥም ትምህርት ቤቶችን፣ ክሊኒኮችን በመገንባት እና በተለያዩ ዘርፎች ላይ ድጋፉን እያረገ ያለ ድርጅትም ነው፡፡

እንደ አትሌቱ ገለጻ፤ በአሁን ወቅት በአገራችን በተለያዩ ክልሎች በተለይም በሰሜኑ ክልል በርካታ ትምህርት ቤቶች ውድመት ደርሶባቸዋል፤ ትምህርት ቤቶችን ለመገንባትም የሁሉንም ርብርቦሽን የሚጠይቅ ጉዳይ ነው፡፡ እንዲሁም በአማራ፣ በትግራይ፣ በአፋር እና ጦርነት ባለባቸው አካባቢዎች ብዙ ህጻናት ከትምህርት ገበታቸው ርቀው እንደሚገኙ በመገንዘብ ርብርቦሹ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡

አትሌት ኃይሌ እንደሚለው፤ የትምህርት ቤቶች ጉዳይ ለባለሃብቱ፣ ለምሁራን እና ለሌሎች ብቻ የምንተወው ጉዳይ አይደለም፤ የሁሉም ርብርብ ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህም ገንዘብ ያለው በገንዘቡ፤ ጉልበት ያለው በጉልበቱ እና በቻለው ሁሉ መርዳት መቻል አለበት፡፡ በአሁን ወቅት በሺዎች የሚቆጠሩ ትምህርት ቤቶች ወድመዋል፤ ይህን በማሰብም ሥራን ለአንድ አካል ብቻ ከመስጠት ወይም ከአንድ አካል ብቻ ከመጠበቅ ይልቅ ሁሉም የበኩሉን ሊወጣ ይገባል፡፡ ምንም እንኳን አትሌቱ በጻግብጂ ያስገነባው ትምህርት ቤት ውድመት እንደደረሰበት ይግለጽ እንጂ ዛሬም ቢሆን ትምህርት ቤቶችን በማደስም ይሁን በመገንባቱ በኩል የድርሻው እንደሚወጣም ይጠቁማል፡፡

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሒታ
BAKKALCHO
ዘመን

የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

# አዲስ ዘመን ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

## ባለ ራእዩ የፍሪስታይል ጥበበኛ

**ቦጋለ አበበ**

ፍሪ ስታይል በዓለም ላይ ቀልብ ከሚስቡ የስፖርት እንቅስቃሴዎች አንዱ ነው። የፍሪ ስታይል ስፖርታዊ ትእይንት በተለያዩ የስፖርት አይነቶች ቢተገበርም የፉትቦል ፍሪ ስታይል እግር ኳስን በመጠቀም ማራኪ ጥበብ ታክሎበት የሚሰራ ተወዳጅ እንቅስቃሴ ነው። በበርካታ አገራትም እውቅ የእግር ኳስ ተጫዋቾች ይህን እንቅስቃሴ ህዝብ በተሰበሰበበት ወይም በተንቀሳቃሽ ምስል ለእይታ ሲያቀርቡ ማየት የተለመደ ነው። ከዚህ ባለፈም የስፖርቱን እንቅስቃሴ በቋሚነት በመስራት በበርካታ አገሮች ታዋቂና ፕሮፌሽናል ግለሰቦች በርካታ ናቸው። ወደ ኢትዮጵያ ስንመጣ ግን ይህን ስፖርት ጥቂት ግለሰቦች ብቻ ስራዬ ብለው የሚያዘወትሩትና እድገቱም እዚህ ግባ የማይባል ሆኖ እናገኘዋለን።

በኢትዮጵያ ይህን ተወዳጅ ስፖርት በማዘውተር እውቅና እያገኙ ከመጡ ግለሰቦች መካከል ወጣት ምንተስኖት ነጋሽ (ምንቴ ካርሎስ) ዋነኛው ነው። ስፖርቱን በትልቅ አላማና ራእይ ስራው አድርጎ እየተንቀሳቀሰ የሚገኘው ይህ ወጣት የፍሪስታይል ጥበበኛ ከዚህ በፊት የተሳካ ባይሆንም በተለያዩ ክለቦች እግር ኳስን ተጫውቷል። ገና በታዳጊነት እድሜው ወደ ዋና ቡድኖች አድጎ መጫወት ቢችልም ከቡድን ይልቅ ወደ ግል ክህሎት የሚያደላ በመሆኑ በተጫዋችነት ብዙ መግፋት አልቻለም። ብራዚላዊው የኳስ ጥበበኛ ሮናልዲኒሆ ጎቾ ከኳስ ጋር በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎችና በሚያሳየው ጥበብ እየተማረከም ወደ ግል ጥበብ ያደላ ነበር። እግር ኳስ ደግሞ የቡድን ስራ ስለሆነ የእሱ እንቅስቃሴና ከኳስ ጋር ቄንጥ ማብዛቱ በአሰልጣኞች እንደማይወደድ ይናገራል።



“ፍሪስታይል ፉትቦል እግር ኳስ ላይ ጥበብን መጨመር ነው” የሚለው ይህ ወጣት እንቅስቃሴውን ያዩ ሰዎች ከእግር ኳስ ይልቅ ወደ ፍሪ ስታይል ቢገባ እንደሚሻለው በሚሰጡት አስተያየት ከዚያም በፊት ስፖርቱን በቅርበት ስለሚከታተለው ኳስ ገዝቶ ሙሉ በሙሉ ገባበት።

ምንቴ ካርሎስ ወደዚህ ስፖርት ሲገባ ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙም ስላተለመደ ከሰራሁበት አዋጭ ይሆናል ብሎ በማሰብ እንደነበር ያስታውሳል። እግር ኳስ መጫወት አቁሞ ይሄንን ጥበብ በጎዳናዎች ላይ ማሳየት ሲጀምርም ከተመልካች ጥሩ ምላሽ ይሰጠኝ ነበር። “አድናቆትን እያገኘሁ ስመጣም ሙያውን ከፍ አድርጌ ተንቀሳቃሽ ምስሎች (ቪዲዮዎችን) መስራት ጀመርኩ፣ በዚህም አሁን ጥሩ ደረጃ ላይ እገኛለሁ” ይላል።

በሌላው ዓለም ይህ ስፖርት ብዙ ገንዘብ የሚያስገኝና እንደ አንድ ስራ ጥበበኛውን ማኖር የሚችል ነው። በእኛ አገር ግን እዚያ ደረጃ ላይ ለመድረስ ብዙ እንደሚቀረው ምንቴ ይናገራል። በእርግጥ በእኛ አገር ብቻም ሳይሆን እንደ አፍሪካም ስፖርቱ ያለበት ደረጃ ገና ነው፣ ስፖርቱ በፕሮፌሽናል ደረጃ አድጎ ወደ ቢዝነስ የመቀየር እድሉ ግን ሰፊ እንደሆነ ያምናል። “እኔ አሁን በአጭር ጊዜ ወደ ቢዝነስ ቀይሬዋለሁ ማለት እችላለሁ፣ ይሄንን ስፖርት በተመለከተ በተለያዩ ሚዲያዎች ቃለመጠይቅ የሰጠሁትም እኔ ነኝ፣ ጥራት ያላቸው ቪዲዮዎች እየሰራሁ ለማህበረሰቡ እያደረስኩም ነው” የሚለው ምንቴ ይሄ ስፖርት ኢትዮጵያ ውስጥ ፕሮፌሽናል ደረጃውን ጠብቆ እንዲያድግ ትልቅ ፍላጎት አለው። ይህን እንቅስቃሴ ከሚሰሩ ካንዳንድ ልጆችም ጋርም በጋራ በመስራት ሙያውን ለማሳደግ ጥረት እያደረገ ነው። ለዚህ ደግሞ ውድድሮችን መፍጠር እንደሚያስፈልግ ያስረዳል። ውድድሮች ካሉ ስፖርቱን ወደ ቢዝነስ መቀየር እንደሚቻልም ያምናል።

እንደ ወጣቱ ገለጻ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ይህን ስፖርት የሚያዘወትሩ ግለሰቦች በዓለም ፍሪስታይል ፌዴሬሽን እውቅና እንዲያገኙ በአገራችን አቻ ፌዴሬሽን ያስፈልጋል። ይህ ከሆነ አገርን ወክለው በዓለም መድረኮች የሚወዳደሩ ስፖርተኞችን ማፍራ ይቻላል። ከስር የሚሰለጥኑ ስፖርተኞችም ያንን አላማ አድርገው ለመስራት ይነሳሳሉ። እንዲህ አይነት እድሎች ሲገኙ ወደ ገበያው የመግባት አጋጣሚውም ይሰፋል፣ እይታዎችም ይጨምራሉ። ይህ እድል ባለመኖሩ ግን ከዚህ በፊት በዚህ ስፖርት ውስጥ የነበሩ ሰዎች ሙያውን በትርፍ ሰዓታቸው ለመስራት ይገደዱ እንደነበር ያስታውሳል። “እኔ የሙሉ ሰዓት ስራዬ ይሄ ነው፣ ሙያውን ከፍ አድርጌ በተለያዩ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ለመምጣት ጥረት እያደረኩ ነው፣ በስፖርቱ ተሰጥኦ ያላቸው ልጆችን አሰልጥኖ የማውጣት ሃሳብም አለኝ፣ ነገር ግን ልጆቹን አሰልጥኜ አንድ የሚያርፉበት አላማና ግብ ከሌለ ቤተሰብም ፍቃደኛ አይሆንም” ይላል። ስፖርቱ ብዙ ቦታ አይፈልግም በየትኛውም ቦታ ላይ ሊሰራ ይችላል። አንዱ ችግር አንድ ልጅ ቢያንስ መለማመጃ አንድ ኳስ የሚያስፈልገው መሆኑ ነው። በእኛ አገር ደግሞ ያለው የኳስ እጥረት ይታወቃል። እንደ አማራጭ ግን ወጣቱ ጥበበኛ በማህበራዊ ሚዲያዎች አማካኝነት ፍላጎት ላለው ሁሉ በያለበት አጫጭር ስልጠናዎችን የመስጠት ሃሳብ አለው።

እንደ አገር ፌዴሬሽን ለመመስረት በቅድሚያ ውድድሮች የሚካሄዱባቸው መድረኮች ሊኖሩ እንደሚገባ የሚጠቁመው ምንቴ፣ ለዚህ ብዙ ሂደቶችን ማለፍ እንደሚያስፈልግ ያስረዳል።

“በአገራችን አሁን ላይ በዚህ ስፖርት ውስጥ ያሉ ሰዎችን ማሰባሰብ አንዱ ፈተና ነው፣ የት እንዳሉ አይታወቅም” የሚለው ይህ ወጣት፣ ስፖርቱ በጣም ተወዳጅ እንደመሆኑ በደንብ ቢሰራበት ማደግ እንደሚችል እምነት አለው።

ይህ ስፖርት ከእግር ኳስ በተለየ አንድ ሰው አገርን ወክሎ በአለም ዓቀፍ መድረኮች መሳተፍ የሚቻልበት ቢሆንም እዚያ ደረጃ ላይ ለመድረስ ብዙ ፈተናዎች እንዳሉ ያስረዳል። “በዚህ ስፖርት ኢትዮጵያ ውስጥ የራሴን አሻራ ማሳረፍ እፈልጋለሁ” የሚለው ምንቴ አርቆ በማሰብ በትልቅ አላማና ራእይ ጥረቱን ቀጥሏል። በዚህ ስፖርት ተሰጥኦው ያላቸው ታዳጊዎችን በማፍራት አገርን እንዲወክሉ በሚያደርገው ጥረት የኢትዮጵያና የአዲስ አበባ እግር ኳስ ፌዴሬሽኖች ከቁሳቁስ ጀምሮ የተለያዩ ድጋፎችን እንዲያደርጉለት ይጠይቃል።

## ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

## ሦስተኛው አገር አቀፍ የሳይበር ደህንነት ወር

**ይበል ካሳ**

### መግቢያ

አገራችን ኢትዮጵያ የዓለማችን ሁለንተናዊ መወዳደሪያ መድረክ እየሆነ የመጣውን የሳይበር ምህዳር ከስጋና ከጥቃት አስጠብቃ ደህንነቱ በተጠበቀ መንገድ ለዕድገቷና ለብልጽግናዋ ጥቅም ላይ ለማዋል ለሳይበር ደህንነት ቅድሚያ ሰጥታ እየሠራች ትገኛለች። በተለይም ለሳይበር ደህንነት የማይመጥን የአስተሳሰብ፣ የአመለካከትና የተግባር ዝግጁነትና የሳይበር ደህንነት ንቃተ ሕሊና ያለው፣ ሙያዊ ክህሎት የተላበሰ ተወዳዳሪ የሰው ኃይል አለመኖር ለሳይበር ስጋት ጥቃት ከሚያጋልጡ መንስኤዎች መካከል ዋነኛው በመሆኑ ይህንን ችግር ለመቅረፍና የአገርን ብሔራዊ ጥቅም ለማስጠበቅና ሉዓላዊነትን ለማረጋገጥ ለንቃተ ህሊና ግንባታ ልዩ ትኩረት ተደርጎ እየተሠራ ይገኛል።

ለዚህም ባለፉት ሦስት ዓመታት የሳይበር ማህበረሰቡንና አጠቃላይ የዜጎችን የሳይበር ደህንነት ንቃተ ህሊና ማሳደግን ዋነኛ ዓላማቸው ያደረጉ ተከታታይ አገር አቀፍ የሳይበር ደህንነት ወር እየተዘጋጁ ይገኛሉ።

ሦስተኛው አገር አቀፍ የሳይበር ደህንነት ወር ዘንድሮም “የተቀናጀ የሳይበር ደህንነት ለአገር ሉአላዊነት” በሚል መሪ ሃሳብ ከጥቅምት 1 ቀን እስከ ጥቅምት 30 ቀን 2015 ዓ.ም ይከበራል። የዘንድሮው የሳይበር ደህንነት ወር እንደተለመደው ለአንድ ወር የሚቆይ ሲሆን በዋናነት በአራት መስኮች ላይ የሚያተኩሩ በአራት ሳምንታት የተከፋፈሉ መርሃ ግብሮችን አካትቷል። የትኩረት መስኮቹም አገራዊ የሳይበር ደህንነት ንቃተ ህሊናን ማሻሻል፣ የተቋማት የሳይበር ጥቃት ተጋላጭነትን መቀነስ፣ የግሉን ዘርፍ ለሳይበር ደህንነት መጠበቅ የሚኖረውን ሚና ማሳደግና በሳይበር ደህንነት ዘርፍ የሰው ሃብት ልማትን ለማሻሻል የሚያስችል አገራዊ ንቅናቄ የመፍጠር ዓላማን አንግበው የሚተገበሩ ናቸው።

ለአንድ ወር በሚዘልቀው ሦስተኛው አገር አቀፍ የሳይበር ደህንነት ወር የማህበረሰቡን የሳይበር ደህንነት ንቃተ ህሊና ለማሳደግ የሚያስችሉ አገራዊ ንቅናቄዎች፣ የተቋማትን የሳይበር ደህንነት ንቃተ ህሊና የሚያጎለብቱ መርሃ ግብሮች፣ አገራዊ የሳይበር ደህንነት ቴክኖሎጂ ምርቶችንና አገልግሎቶችን የሚያስተዋውቁና ከተቋማት ጋር ትስስር ለመፍጠር የሚያግዙ የተለያዩ ዝርዝር ተግባራት ይከናወናሉ።

በዚህም ወሩን ሙሉ በየሳምንቱ የተለያዩ ጭብጦችን የሚያስተላልፉ መልዕክቶች እየተነሱ ግንዛቤ ይፈጠርባቸዋል። የማህበራዊ ሚዲያ ንቅናቄዎች፣ የተንቀሳቃሽ ምስል ማሳያዎችና ሌሎች በየድረ ገጾች የሚለቀቁ አንቂ መልእክቶች የሚተላለፉበት ይሆናል። የተለያዩ የዘርፉ ባለድርሻዎችና አጋር አካላት ተጋባዥ ይሆናሉ። ሚናዎቻቸውንም እንዲወጡ ይደረጋሉ። በሚዲያዎች ብቻ ሳይሆን ልዩ ልዩ መድረኮችን በማዘጋጀት የሳይበር ደህንነት የንቃተ ህሊና ሥራዎች በአካል የሚከናወኑ ይሆናሉ።

ከዚህም በአሻገር ከተለያዩ ተቋማት የተውጣጡ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች፣ የፋይናንስ ተቋማት፣ የግል ተቋማት፣ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ዓለም አቀፍ ተቋማት የሚሳተፉባቸው መድረኮችም ይዘጋጃሉ። ለዚህም የተቋማትን የሳይበር ጥቃት ተጋላጭነት ለመቀነስ ምን መሰራት አለበት፤ የግሉ ዘርፍ ለሳይበር ደህንነት መጠበቅ የሚኖረው ሚና፣ እንዲሁም የሳይበር ደህንነትን ለማስጠበቅ የሚያስችል የሰው ኃይል እንዴት ማልማት ይቻላል በሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በወሩ ውስጥ ሦስት ትላልቅ ኮንፈረንሶች የሚካሄዱ ይሆናሉ። ከኮንፈረንሶቹ በተጨማሪም በልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ አውደ ርዕዮችም ጎን ለጎን ለተመልካቾች የሚቀርቡባቸው መድረኮች ተዘጋጅተዋል። አውደ ርዕዮቹ የሚካሄዱበት ቀንና ቦታም እንደሚከተለው ተገልጿል።

- ጥቅምት 1 ቀን 2015፡- ከቀኑ 6፡00 እስከ ምሽቱ 11፡00 ሰዓት
- ጥቅምት 2 ቀን 2015፡- ከጠዋቱ 2፡30 እስከ ምሽቱ 11፡00 ሰዓት
- ጥቅምት 7 ቀን 2015፡- ከቀኑ 6፡00 እስከ ምሽቱ 11፡00 ሰዓት
- ጥቅምት 8 ቀን 2015፤ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ ምሽቱ 11፡00 ሰዓት

ሁሉም አውደ ርዕዮች የሚካሄዱበት ቦታም በኢትዮጵያ ስካይ ላይት ሆቴል ይሆናል።

### ሦስተኛው የሳይበር ደህንነት ወር ከቀደምቶቹ የሚለይባቸው ጉዳዮች

ከላይ በመግቢያችን እንዳመላከትነው ከዚህ በፊት እንደተካሄዱት ሁለት አገር አቀፍ የሳይበር ደህንነት ወሮች ሁሉ የዘንድሮው የሳይበር ደህንነት ወርም ዋነኛ ዓላማው የሳይበር ማህበረሰቡንና አጠቃላይ የዜጎችን የሳይበር ደህንነት ንቃተ ህሊና በማሳደግ ሊደርሱ የሚችሉ የሳይበር ጥቃቶችን አስቀድሞ በመከላከልና በብቃት በመመከት የአገርን ብሔራዊ ጥቅምና ሉዓላዊነት ማስጠበቅ ነው። ይህ እንዳለ ሆኖ ሦስተኛው አገር አቀፍ የሳይበር ደህንነት ወር የግሉን ዘርፍ በሳይበር ደህንነት አጠባበቅ ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆንና የሳይበር ደህንነትን ለማስጠበቅ የሚያስችል የሰው ኃይል እንዴት ማልማት ይቻላል የሚሉት ጉዳዮች ልዩ ትኩረት የተሰጠባቸው መሆኑ የዘንድሮውን ከቀደምቶቹ ለየት ያደርገዋል። ለዚህም የግልና ሌሎች የመንግሥት ተቋማት በሳይበር ደህንነት ዙሪያ ተሳታፊና ዋነኛ ተዋንያን መሆናቸውን አውቀው በአግባቡ ተሳታፊ መሆን ይችሉ ዘንድ በወሩ ውስጥ የሚከናወኑት ኮንፍረንሶችና አውደ ርእዮች በአብዛኛው በነዚህ አካላት እንዲቀርቡና እነዚህን አካላት በስፋት እንዲያሳትፉ ተደርጓል። የተመረጡና የደህንነት ተጋላጭነት የለባቸውም ተብለው የተለዩ አገራዊ የሳይበር ደህንነት ቴክኖሎጂ ምርቶችና አገልግሎቶችን በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር አማካኝነት የሚቀርቡ ይሆናል፡

በአጠቃላይ በዘንድሮው የሳይበር ደህንነት ወር በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ብዙ ተደራሾችን ለመድረስና በሳይበር ደህንነት ላይ የሚሰሩ የተለያዩ አካላትን በማገናኘት በዘላቂነት በጋራ ሊሰሩ የሚችሉበትን እድል በመፍጠር ብሎም ማህበረሰቡን ያካተተ ጠቅላላ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች በመሥራት የሳይበር ማህበረሰቡን፣ የተቋማትንና አጠቃላይ የዜጎችን የሳይበር ደህንነት ንቃተ ህሊና ለማጎልበት ታቅዷል። ይህም ከጊዜ ወደጊዜ በከፍተኛ ፍጥነት እየጨመረ የመጣውን አውዳሚውን የሳይበር ጥቃት በብቃት ለመከላከልና አጠቃላይ የአገርንና ሕዝብን ብሔራዊ ደህንነትና ሉዓላዊነት ለማስጠበቅ ፋይዳው የጎላ በመሆኑ ሕብረተሰቡ በንቃት እንዲሳተፍ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ጥሪውን ያቀርባል።